

«ሁሉም የራሱን ጉዳይ ብቻ ለማስፈፀም መሯሯጡን የሚቀጥል ከሆነ ነገ ቁጭ ብለን የምንነጋገርባት ሃገር አትኖረንም»

- ኡስታስ ሃሰን አሊ
የአፍሪካ ሚዲያ ቴሌቪዥን ጣቢያ መስራች

ገጽ 6

ለሕግ መከበር ቅድሚያ ይሰጥ

ገጽ 15





# አዲስ ዘመን

አንድ

81ኛ ዓመት ቁጥር 211 ሚያዝያ 1 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10.00

ቅዳሜ

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!





# ‹‹መጽሐፍ መስጠት ለትውልድ የእውቀት ብርሃን ማካፈል ነው››

## - ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ


ፎቶ - ገበዮ ገብሬ

አዲስ አበባ፡- መጽሐፍ መስጠት ለትውልዱ የእውቀት ብርሃን ማካፈል መሆኑን የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ገለጹ።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ትናንት ለአብሮኘት ቤተ መጽሐፍት ከበጎ ፈቃደኞች መጽሐፍት በስጦታ ሲበረከትለት ተገኝተው እደገለጹት፤ መጽሐፍ በመስጠትና በማካፈል ትውልድን በእውቀት መስራትና ማነጽ ነው። ለትውልድም የእውቀት ብርሃን ማካፈል ነው። ከጨለማና ከኋላ ቀርነት ለመላቀቅና ሀብታችንን በአግባቡ ለመጠቀም በእውቀት መበልጸግ እንደሚያስፈልግ አመልክተው፤እውቀትን መስጠት የሚያትርፍ እንጂ ኪሳራ የለውምና መጽሐፍትና ዕውቀትን ማካፈል ያስፈልጋል ብለዋል።

‹‹መጽሐፍ መስጠት ለትውልድ... ወደ ገጽ 4

# የጋምቤላ ክልል የሕዝብ ጥያቄዎችን ለመመለስ ተግባራዊ እንቅስቃሴ መጀመሩን ገለጸ

## - ሠላምና ፀጥታን ለማረጋገጥ ከአጎራባች ክልሎች ጋር በትብብር ይሰራል

**ገመቹ ከድር**

አዲስ አበባ፡- ብልፅግና ፓርቲ የሕዝብ ጥያቄዎችን ለመመለስ በጉባኤው ያስቀመጣቸውን አቅጣጫዎችና ያሳለፋቸውን ውሳኔዎች ተግባራዊ ለማድረግ እንቅስቃሴ መጀመሩን የጋምቤላ ክልላዊ መንግሥት አስታወቀ። ክልሉ ሠላምና ፀጥታን ለማረጋገጥ ከአጎራባች ክልሎች ጋር በትብብር እንደሚሰራም አመልክቷል።

የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር አቶ ኡመድ ኡጁሉ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የጋምቤላ ክልላዊ መንግሥት ብልጽግና ፓርቲ በጉባኤው ባስቀመጠው አቅጣጫና ውሳኔ መሰረት የሕዝብ ጥያቄዎች ለመመለስ የአጭርና ረጅም ጊዜ ዕቅድ በማውጣት ወደ ተግባር ገብቷል።

የክልሉን ሕዝብ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማሕበራዊ ችግሮችን ለመፍታት ዕቅድ በማዘጋጀት ወደ ትግበራ ምዕራፍ መሸጋገር ተችሏል ያሉት አቶ ኡመድ፤ በክልሉ በተለያዩ አካባቢዎች 14 ሕዝባዊ መድረኮች ከተደረጉ በኋላ ከመጋቢት 29 ጀምሮ እስከ ሐምሌ 2014ዓ.ም


ርዕሰ መስተዳድር አቶ ኡመድ ኡጁሉ

አንገብጋቢ የሕዝብ ጥያቄዎች ምላሽ የሚሰጥበት መሆኑን አመልክተዋል።

በትግበራው ምዕራፍ በፓርቲው የተቀመጡ ግቦችን መሠረት በማድረግ እያንዳንዱ መስሪያ ቤት በሚመለከተው ልክ የራሱን መሪ ዕቅድ በማዘጋጀት ወደ ትግበራ እንዲገቡ አቅጣጫ ተቀምጦ የሕዝብ ጥያቄዎችን ለመመለስ ተግባራዊ እንቅስቃሴ መጀመሩንም አስታውቀዋል።

እንደ ርዕሰ መስተዳድሩ ገለጻ፤ በሚቀጥሉት ሶስት ወራትም በክልሉ መልካም አስተዳደር በማስፈን፣ ዘላቂ ሠላም በማረጋገጥ ፣ ኑሮ ውድነትን በማረጋጋት፣ በሕብረ ብሔራዊ አንድነት በማጠናከርና ሌብነትን የሚጠየፍ ማሕበረሰብ በመፍጠር ጉዳዮች ላይ ትኩረት ይደረጋል።

በክልሉ የሚታየው የዋጋ ንረት ዓለምአቀፋዊ ምክንያት እንዳለው ርዕሰ መስተዳድሩ አመልክተው፤ ሕገ ወጥ ነጋዴዎች በሸቀጦች ላይ ያደረጉትን ከፍተኛ ዋጋ ጭማሪ ከንግዱ ማህበረሰብ ጋር በመወያየትና መንግሥት በወሰደው ሕጋዊ እርምጃ እንዲሻሻል ማድጉን ጠቅሰዋል።

በመጪዎቹ ሶስት ወራትም በየመሥሪያ ቤቶች እየተንሰራፋ ያለውን ሌብነት ማጋለጥ ፣ ዘላቂ ሠላምና ፀጥታ ማረጋገጥ ፣ ሰብዓዊ መብቶች ማስከበር ፣ በአግልግሎት አሰጣጡ ግልጽነት መፍጠር በከተማና

የጋምቤላ ክልል... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


አቶ እንዳለ ንጉሴ
በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ የዲፕሎማሲና ዓለም አቀፍ ግንኙነት መምህር

# ኢትዮጵያ ላይ ማዕቀብና ጫና ለማሳረፍ የቀረበው ረቂቅ ሕግ እስኪወገድ ትግሉ መቀጠል እንዳለበት ተጠቆመ

**ፍቃዱ ዴሬሳ**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ ላይ ተገቢ ያልሆነ ማዕቀብና ጫና ለማሳረፍ የቀረበው ረቂቅ ሕግ ሙሉ በሙሉ እስኪወገድ ትግሉ መቀጠል እንዳለበት በኢትዮጵያ

ኢትዮጵያ ላይ ማዕቀብና... ወደ ገጽ 4

# የነባር እሴቶቻችን መሸርሸር ለሥነ-ምግባር ብልሹነት መስፋፋት ዋነኛ ምክንያት መሆናቸው ተገለጸ

ገጽ 4






# የፈጠራ ባለቤቶችን «የጋን ውስጥ መብራት» ያደረገው አሰራር

**ዳግማዊት ግርማ**

ቴክኖሎጂ ሁሉም ነገር መሆን ከጀመረ ሰነባብቷል። በአካል ሰፍታ በምናብ ለጠበበችው ዓለም መግባቢያ ቋንቋዋ ቴክኖሎጂ ነው። የሰው ልጅ ቁርስ ምሳ እራቱ ሁሉ ቴክኖሎጂና ውጤቶቹ ሆነዋል።

ኢትዮጵያም ዚህች ዓለም አንድ አካል ናትና ይኸው እውነታ ይገልጻታል። ከዚህም ከዚያም የፈጠራ እጆች የተቸሯቸው ዜጎች ብቅ ብቅ በማለት ላይ ይገኛሉ።

የኮምቦልቻ ልጅና የአስራ ሁለተኛ ክፍል ተማሪ የሆነው ኑሩ ጀማልም የልባቸውን እንቁ አውጥተው ማብራት ከቻሉ ኢትዮጵያውያን መሀል ነው። ከትምህርቱ ጎን ፈጠራ ስራውን ለሚከውነው ወጣት ኑሩ የፈጠራ ስራዎች መነሻ የሚሆኑት በአካባቢው የሚመለከታቸው ችግሮች ናቸው። ወጣት ኑሩ ችግርን በችግርነቱ ብቻ ሳይሆን የሚያየው ለመፍትሄ እንደ መቅረቢያ መንገዱም ጭምር ነው።


የድምፅ መሰለያ ድሮን፣ የትራፊክ አደጋን መቆጣጠር የሚችል መሳርያ፣ የአንበጣ መከላከያ ቴክኖሎጂ ስራ ከወጣት ኑሩ የፈጠራ ውጤቶች መሀል የተወሰኑት ናቸው። ወጣት ኑሩ ከአራተኛ ክፍል ጀምሮ የፈጠራ ስራዎችን ይሰራ እንደነበር ይናገራል።

ከወጣት ኑሩ የፈጠራ ስራዎች መሀል በአገራችን ላይ ሰውን ተክቶ ድምፅን ከሩቅ ቦታ ላይ ጠልፎ የሚያመጣ ሰላይ ራዳር ቴክኖሎጂ አንዱ ነው። አጠቃቀሙም በቀላሉ አንድ ቦታ ላይ በመግጠም ከሆነ ቦታ ላይ ሆኖ በተንቀሳቃሽ ኮምፒውተር መረጃን መሰብሰብ ነው።

ወጣት ኑሩ ይህ ፈጠራው ለአገራችን ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ እንዳለው ተናግሯል። አብዛኛውን ጊዜ አገራችን ኢትዮጵያ መረጃን የምንሰበስበው በሰው ሃይል ነው።



ወጣት ኑሩ ጀማል



ወጣት ሸሀቡዲን ሱሌይማን

ይህ ቴክኖሎጂ ግን ከርቀት ያለን መረጃ አንድ ቦታ ላይ ሆኖ በቀላሉ መሰብሰብ ማስቻሉ ልዩ እንደሚያደርገው አብራርቷል ። ወጣቱ ራዳሩን የሰራው ከአካባቢ በወዳደቁ ቁሳቁሶች እንደሆነም ተናግሯል። ወጣት ኑሩ የፈጠራ ስራዎቹን ብቻውን ከመስራት ይልቅ ከሶስት ወር በፊት ስድስት ልጆችን በመሰብሰብ የራሱን የፈጠራ ቡድን መመስረት ችሏል።

ሌላኛው የፈጠራ ባለሙያ ደግሞ ወጣት ሸሀቡዲን ሱሌይማን ይባላል፤ ወጣት ሺሀቡዲን ራሱን ከሚያውቅበት እድሜው ጀምሮ ነገሮችን የመነካካት አዲስ ነገርን የመሻት ፍላጎት የነበረው ሲሆን፤ የ21 ዓመቱ ሸሀቡዲን በኦሮሚያ ክልል ባሌ ዞን የተገኘ ሲሆን በሚያስተዳድረው ድርጅት ውስጥ ለብዙ ሰዎች የስራ እድል መፍጠር የቻለ እንዲሁም የቴክኖና ሳምሰንግ ስልኮች ተወዳዳሪ መሆን የሚችል ስልክ መፍጠር የቻለ ወጣት ነው።

በወጣት ሸሀቡዲን አማካኝነት የተመሰረተው አይስታር (Istar) ቴክኖሎጂ የተለያዩ የኤሌክትሮኒክስ ቴክኖሎጂ ውጤቶችን እየሰራ እንደሚገኝ ወጣቱ ተናግሯል። ከእነዚህ መካከልም የኤሌክትሪክ ምድጃ (ኡቭን ስቶቭ) እና በምስጢር ቁልፍ (በፓስወርድ) የሚከፈትና የሚቆለፍ በሮችን መስራት ይገኙበታል።

ወጣት ሸሀቡዲን፤ ኢትዮጵያን በቴክኖሎጂው ዘርፍ እንድትጠራ የማድረግ የረጅም ጊዜ ምኞት እንደነበረው የገለጸ ሲሆን፤ ምኞቱ ወደ ተግባር ተለውጦ አይስታር (Istar) የተሰኘውን አዲስ ተንቀሳቃሽ የስልክ ቀፎ በማምረት በቅርቡ ለገበያ ለማቅረብ መዘጋጀቱ ከፈጠራ ሃሳብ በዘለለ ምርቱን ለአገሩ ማበርከቱ ደስታና ኩራት እንደተሰማው ተናግሯል።

ወጣት ሸሀቡዲና ወጣት ኑሩ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚስተዋለው የፈጠራ ባለሙያዎችን ያለመደገፍ ችግር እንዳሳዘናቸው ይገልፃሉ። የፈጠራ ባለሙያዎችን ግኝት የሆነ ሰሞን ርዕስ ከማድረግ በዘለለ የሚሰሩት ስራ የሚደገፉበት ስርዓት እንደሌለም በክፍተትነት ይናገራሉ።

እንደ ወጣቶቹ ንግግር፤ ባለብቶችም ዘርፉን ለመደገፍ ፍላጎት ያለመኖር ችግር ይስተዋልባቸዋል። በቴክኖሎጂው ዘርፍ ኢዮጵያን ተወዳዳሪ ማድረግ የሚቻልበት እድል ቢኖርም ባለሙያዎችን እንዲበረቱና በፈጠራ ስራቸውም እንዲቀጥሉበት የሚያደርግ አሰራር አለመኖሩ ቅሬታ ውስጥ ከቷቸዋል። በመንግሥትም በኩል ተቀናጅቶና ተናቦ የመስራት ክፍተት መኖሩንም ይናገራሉ።

የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር ዶክተር ሹመቴ ግዛውም ኢትዮጵያ ውስጥ የፈጠራ ባለሙያዎችን መደገፍ ላይ የሚስተዋሉ ችግሮች መኖራቸውን ገልጸዋል።

በመንግሥት በኩልም ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው መሆኑን የሚናገሩት ዶክተር ሹመቴ፤ በእርሳቸው የስራ መስክ ላይ ፍላጎት ያላቸውን በየትኛውም የትምህርት ደረጃ ላይ ያሉትን ወጣቶች በማሰልጠንና በማስተማር የማበረታታትና የመደገፍ ተግባራትን መጀመሩን ተናግረዋል።

# «የምርመራ ጋዜጠኝነት በሚዲያ ተቋማት ጥሩ ጅምር እያሳየ ነው»

- የሚዲያ ተቋማት

**ሙሳ ሙሐመድ**




አዲስ አበባ፡- የምርመራ ጋዜጠኝነት ዘገባ በሚዲያ ተቋማት ጥሩ ጅምር እያሳየ መሆኑን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ሃሳባቸውን የገለጹ አንዳንድ የሚዲያ ተቋማት ተናገሩ።

የኦሮሚያ ብሮድካስቲንግ ኔትወርክ ዋና ዳይሬክተር አቶ ዝናቡ አስራት እንደተናገሩት፣ የምርመራ ጋዜጠኝነት ዘገባ ስራ ጥሩ ጅምር እያሳየ ነው። የኦሮሚያ ብሮድካስቲንግ ኔትወርክ ለምርመራ ዘገባ ትኩረት በመስጠት የተለያዩ ስራዎችን እየሰራ ይገኛል።

እንደ አቶ ዝናቡ ገለጻ፣ የምርመራ ዘገባ በኦቢ ኤን "ጫያ" በሚል ለሕዝብ እየተላለፈ ነው። ስራውም ገና ከመጀምሩ በአመራሩ፣ በነዋሪዎች፣ በሸማች ማሕበራት፣ ምርት በሚሰውሩ ነጋዴዎችና ባለሀብቶች ላይ ትኩረት አድርጎ በመስራት መሰረታዊ ለውጥ እያመጣ ነው።

የጫያ ሥርጭትን ለሕዝብ በማድረስም በማሕበረሰቡ ቅሬታ እየቀረበባቸው ያሉ አመራሮች፣ ባለሀብቶች፣ የሸማች ማሕበራትና ኃላፊዎች፣ አስመጪዎች፣ ላኪዎችና አከፋፋዮች በምርመራ ጋዜጠኞች ትኩረት ተሰጥቶ እየተሰራባቸው ነው።

በጉብኝቱም ግለሰቦቹና አመራሮቹ ቀርበው ከማሕበረሰቡ የተነሱ ጥያቄዎች ይቀርቡላቸውና መልስ ይሰጣሉ፣ ስህተታቸውን ያመኑትና ማስረጃ የተገኘባቸው ተጠያቂ እንዲሆኑ ይደረጋሉ ብለዋል።

በጫያ የኦሮሚያ ከተሞች በባሌና በአሰላ ይስተዋሉ የነበሩ የተቋማትና አመራሮች ክፈተቶችን አጋልጧል። ሕብረተሰቡን የሚያጉላሉና የሚያንገላቱ የተንዛዙ አሰራሮች እንዲስተካከሉ ተደርገዋል ብለዋል አቶ ዝናቡ።

ዘገባውን እየሰሩ ያሉት ጋዜጠኞቻችን ዘርፈ ብዙ ጫናዎች ደርሶባቸዋል ያሉት አቶ ዝናቡ ፣ በአመራሮች፣ በባለሀብቶች፣ ነጋዴችና ነዋሪዎችን ጭምሮ ከስደብ እስከ አካላዊ ድበደባ መድረሱን ገልጸዋል።

የፋና ብሮደካስቲንግ ኮርፖሬሽን የዶክመንተሪና ምርመራ ዘገባ ቡድን ዋና አዘጋጅ አቶ ሺበሺ አለማየሁ በበኩላቸው፣ ፋና በሬዲዮ፣ ቴሌቪዥንና ዲጂታል ሚዲያው የምርመራ ዘገባውን ቀደሞም እየሰራ ነበር። አሁንም በሁሉም አጠናክሮ ቀጥሏል፣ ጥሩ ለውጦችም እየታዩ ነው ብለዋል።

በመንግሥት ተቋማት ዘንድ ስራው የመንግሥት አጀንዳ መሆኑን ስላወቁ ሲጠየቁ እሺ ይላሉ። ጥሩ ፊት እያሳዩ ነው። መረጃውን ለመስጠት ግን የተለያዩ ሰበቦችን በማቅረብ የማጓተትና ስራውን የማዘግየት ሁኔታዎች ይስተዋላሉ ሲሉ ይናገራሉ አቶ ሺበሺ ።

አመራሮች፣ ባለሥልጣናት በምርመራ ዘገባ ስራዎች ሲጋለጡ ሲያይ አመራሩ ከእኩይ ተግባሩ ይቆጠባል። ሕዝቡም ያለምንም ፍራቻ መጋለጥ ይጀመራል። ሴራዎች በይፋ ሲጋለጡ አስተማሪ ይሆናሉ ብለዋል አቶ ሺበሺ።

በዘገባ የተጋለጡ ወንጀለኞች ሲቀጡ፣ ለሰሩት ስራ ተጠያቂ ሲሆኑ መታየት መቻሉ ሕዝቡ መረጃን የመስጠት ባህል ያድጋል። በማዘግየታቸው ሲጠየቁ መረጃዎችን ማዘግየት ይቀራል፣ ለነገ ያጠቃኛልና ያቄምብኛል የሚል ፍራቻ በሕዝቡ ዘንድ ይቀራል ብለዋል።

የሁሉም ሚዲያ ተቋማት የምርመራ ዘገባ ዓላማውና ጥቅሙ ለአገር ነው። ብልሹ አሰራሮች፣ ግፎችን በማጨናገፍ መልካም ስራዎች እንዲሰፉ ለማድረግ እንደሆነም ሁሉም ሊረዳው ይገባል ብለዋል አቶ ሺበሺ።

የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ጋዜጠኝነትና ሥነ-ተግባቦት ትምህርት ቤት ረዳት ፕሮፌሰር፣ ዶክተር ተሻገር ሺፈራው እንደገለጹት፣ የምርመራ ዘገባ ተግዳሮት አሉበት። ምንጮቹ መረጃን ይደብቃሉ። የደበቁትን መረጃ ማውጣት የዘገባ ጋዜጠኛው ታታሪነት ይወስነዋል። ጋዜጠኛው ዜናውን ለማግኘት ብዙ መድከምና መልፋት ይጠበቅበታል።

‹‹የምርመራ ዘገባ ስራ የተሳሳተ አመለካከት ሲሰጠው ይስተዋላል። ትልልቅ ባለሥልጣናትን ከሥልጣን ማውረድ አድርገው የሚያስቡት አሉ።›› ስራ ከዚህ ለየት እንደሚል ደክተር ተሻገር ይናገራሉ።

የምርመራ ጋዜጠኝነት የሕብረተሰቡን ኑሮ የሚያውኩ፤ ብልሹ አሰራሮች፤ ሙስናና ሌብነት፤ ማጭበርበር የመሳሰሉት ሁሉ በምርመራ ጋዜጠኝነት ሊሰሩ እንደሚችሉ ዶክተር ተሻገር ይገልጻሉ።

እንደ ዶክተር ተሻገር ገለጻ፣ የመገናኛ ቡዙሃን የስራውን ተገዳሮት ተረድተው ቁርጠኛነት ሊኖራቸው ይገባል። ለጋዜጠኞች ተቋማዊ ድጋፎች እንደ የሕግ ከለላና ጥበቃ መስጠት ያስፈልጋል። ተቋማትና ባለሥልጣናት ለጋዜጠኞች ጭምር ጉቦ በመስጠት ዘገባውን ሊያስቆሙ ይችላሉ ብለዋል።

የተዋጣለት የምርመራ ዘገባ እንዲሰራ ከተፈለገ ለጋዜጠኞች ጊዜ መስጠትና ማገዝ ያስፈልጋል። ባለስልጣናትና ተቋማት ለመገናኛ ቡዙሃን መረጃ እንዲሰጡ በማድረግ ተቋማዊ ድጋፍ ማድረግ ያስፈልጋቸዋልም ሲሉ ዶክተር ተሻገር ተናግረዋል።

# «አምንስቲ ኢንተርናሽናልና ሂውማን ራይትስዎች በኢትዮጵያ ላይ ያወጡት ሪፖርት የምዕራባውያን ተጽዕኖ አንዱ ማሳያ ነው»

-ምሁራን

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- አምንስቲ ኢንተርናሽናልና ሂውማን ራይትስ ዎች በኢትዮጵያ ያወጡት ሪፖርት የምዕራባውያን ተጽዕኖ አንዱ ማሳያ ነው ሲሉ ለኢትየጵያ ፕሬስ ድርጅት አስተያየታቸውን የሰጡ ምሁራን ገለጹ።

የታሪክ ምሁሩ ረዳት ፕሮፌሰር አደም ካሚል በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ አምነስቲ ኢንተርናሽናልና ሂውማን ራይትስዎች በኢትዮጵያ ያወጡት ሪፖርት የምዕራባውያንን ተጽዕኖ ጉልበት ለመስጠት በሚል ታስቦ የወጣ ነው።

ከ80 ሺህ በላይ የግብጽ ምሁራን በአምነስቲ ኢንተርናሽናል፣ በዓለም ባንክ፣ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅትና በመሳሰሉት የዓለም ተቋማት ይሰራሉ። ስለሆነም በየጊዜው ከምዕራባውያን ጋር በመሆን ኢትዮጵያን ለመበታተንና ለማንበርከክ ይሰራሉ ብለዋል።

ለአንድ አገር ጥንካሬ መለኪያው የአንድ አገር ኢኮኖሚ ማደግ ነው ያሉት ምሁሩ፤ ኢትዮጵያ የኢኮሚ አቅሟን በማሳደግ በየጊዜው ከሚደረጉባት ጫናዎች ማምለጥ ይኖርባታል። ባለፉት ሁለት ዓመታት ኢትዮጵያ በርካታ ችግሮች ገጥመዋታል፤ ነገር ግን በጥበብ አልፋቸዋለች።

በተለይ የግድቡ ጉዳይ ከፍተኛ ስጋት ቢሆንም ግብጽ ባላሰበችበት መንገድ የኢትዮጵያ ሕዝብ ተባብሮ በመስራት ግድቡ ኃይል ማመንጨት ደረጃ እንዲደርስ አስችሎታል ብለዋል።

በሰሜኑ የአገራችን ክፍል በነበረው ጦርነት ምዕራባውያንም ይሁን ግብጾች እጃቸው አለበት ያሉት ምሁሩ፤ የነሱ አባሪዎች ደግሞ በውሸት በኢትዮጵያ የሰብአዊ መብት ጥሰት ደርሰዋል በማለት ድጋፍ ያደርጋሉ። ኢትዮጵያ በጦርነት ታመሰች እያሉ የሀሰት ዜና



ረዳት ፕሮፌሰር አደም ካሚል



አቶ ዮናስ መኮንን

በማሰራጨት በኢንቨስትመንትና በቱሪዝም ተጠቃሚ እንዳትሆን ሲሰሩ ነበር። ሁሉም ነገር ሲከሽፍባቸው ኤች አር 6600 እና ኤስ 3199 የሚሉ ሪቂቅ ሕጎችን በማንሳት ጫና ለማድረግ እየሰሩ ነው።

አምንስቲ ኢንተርናሽናል ያወጣው ሪፖርትም ይህን ሕግ ለማጽደቅ የሚደግፍ ነው። ኢትዮጵያውያን በአንድነት በመቆምና ያሉ ቀዳዳዎችን በመዝጋት እንዳለፈው ጊዜ ሃሳባቸውን ማክሸፍ እንደሚያስፈልግ ገልጸዋል።

በወሎ ዩኒቨርሲቲ የፍልስፍና መምህር የሆኑት አቶ ዮናስ መኮንን በበኩላቸው፤ አምነስቲ ኢንተርናሽናል እና ሂዩማን ራይትስ ዎች በወልቃይት ላይ ያወጡት ሪፖርት ተአማኒነት የለውም። በኢትዮጵያ ላይ ጫና ለማድረግ ያለመ ሪፖርት ነው፤ የምዕራባውያን ፖሊሲ አስፈጻሚ መሆናቸውንም በግልጽ አሳይተዋል ብለዋል።

እንደ ሙሁሩ ገለጻ፤ ቢያንስ የጎንደር ዩኒቨርሲቲ የጥናት ቡድን ያወጣውን መረጃ እንደ ግብአት መጠቀም ነበረባቸው፤ ነገር ግን ፍላጎታቸው ለአንድ ወገን ድጋፍ ማድረግ በመሆኑ መንግሥት የሚያደርገውን የሰላም ጥረትም ከግምት አላስገቡትም ብለዋል።

ሪፖርቱ የተቋሞቹ ተአማኒነት ላይ ጥያቄ ያስነሳል ያሉት ምሁሩ፤ ተቋሞቹ የሚሰሩት በግልጽ በምዕራባውያን ፍላጎት ተመስርተው ነው። ዋና ፍላጎታቸውም የምዕራባውንያንን ጥቅም ማስጠበቅ ነው። በሌላ በኩል ኤች አር 6600 ረቂቅ ሕግ እንዳይጸድቅ በዘገየበት ማግስት ሪፖርቱ መውጣቱ ትልቅ መልዕክት አለው።

የኢትዮጵያ መንግሥት የምዕራባውያንን ፖሊሲ የማይቀበል ከሆነ እንደ ጫና ማድረጊያ አድርገው በማሰብ ያወጡት ነው ብለዋል።



## የሩሲያ- ዩክሬን ጦርነት በሸቀጦች አቅርቦት ሰንሰለት ላይ የጋረጠው ፈተና ለአፍሪካ የማንቂያ ደወል ነው

አዲስ አበባ፡- የሩሲያ- ዩክሬን ጦርነት በሸቀጦች አቅርቦት ሰንሰለት ላይ የጋረጠው ፈተና ለአፍሪካ የማንቂያ ደወል ነው ሲሉ የፕላን እና ልማት ሚኒስትር ዶክተር ፍጹም አሰፋ አስታወቁ።

የኢፌዴሪ ፕላን እና ልማት ሚኒስትር ዶክተር ፍጹም አሰፋ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን ባዘጋጀው የበይነ መረብ ስብሰባ ላይ ተሳትፈዋል።

ስብሰባው "የአፍሪካ ነጻ ገበያ ቀጠና ይዞ የመጣውን ጥቅም የትራንስፖርት ወጪን በመቀነስ ማሳደግ" በሚል ርዕስ የተዘጋጀ ነው።

ዶክተር ፍጹም በዚህ ወቅት እንዳሉት፥ የአፍሪካ አህጉራዊ ነጻ የንግድ ቀጠና በትክክለኛው መንገድ ከተተገበረ በአህጉሪቱ ያለውን የንግድ እንቅስቃሴ የመለወጥ አቅም እንዳለው ተናግረዋል።

ከቀጣናዊ ንግድ ጋር በተገናኘ በቅርብ ጊዜያት ለውጥ አለ ያሉት ሚኒስትሯ ፤ ከሌሎች ዓለማት ጋር ሲነጻጸር ግን አፍሪካ ወደ ኋላ መቅረቷን በማመልከት፣ የአፍሪካ አህጉራዊ ነጻ የንግድ ቀጠና ትግበራ ስኬታማነት ይህን ክፍተት የሚሞላ እንደሚሆን ጠቁመዋል።

የአፍሪካ አህጉራዊ ነጻ የንግድ ቀጠና በመላው አህጉሪቱ ኢኮኖሚውን በማሳደግ፣ የንግድ እና ሥራ ፈጠራን በማሻሻል ለሸቀጦች እና አገልግሎቶች አንድ የንግድ ማዕከል በመገንባት ድህነትን በመቀነስ ረገድ ለውጥ ያመጣል ተብሎ እንደሚጠበቅም አመላክተዋል።

ሆኖም አገራት የአፍሪካ አህጉራዊ ነጻ የንግድ ቀጠናን በመቀላቀል ከትሩፋቱ እንዳይቋደሱ እንቅፋት መሆኑንና ይህም የሆነበት በትራንስፖርት መሠረተ ልማት እና በሎጂስቲክስ አለመሟላት ምክንያት መሆኑን ነው ሚኒስትሯ የገለጹት።

የታሪፍ ቅናሽን ጨምሮ ከአፍሪካ አህጉራዊ ነጻ የንግድ ቀጠና የሚገኙ ትሩፋቶችን በሚገባ ለመጠቀም ይኸው ደካማ የትራንስፖርት መሠረተ ልማት ያላቸው አገራት ማሻሻያ ማካሄድ፣ ለግጭቶች መፍትሔ ማበጀት፣ ሙስናን መዋጋት እና የጉምሩክ አሰራራቸውን ማሻሻል እንደሚኖርባቸውም አስገንዝበዋል።

በተጨማሪም የመሠረተ ልማቶችን ከማሻሻል እኩል ዘመናዊ አሰራሮችን መዘርጋት አስፈላጊ እንደሆነም ዶክተር ፍጹም በስብሰባው ላይ ገልጸዋል።

ሚኒስትሯ በዚሁ ስብሰባ ከሦስት ዓመት በላይ የዘለቀው የኮሮና ቫይረስ እና በአሁኑ ወቅት እየተካሄደ የሚገኘው የሩሲያ እና ዩክሬን ጦርነት በሸቀጦች እና አገልግሎቶች አቅርቦት ሰንሰለት ፈተና መጋረጡን አስታውሰው ፤ እነዚህ ክስተቶች ለአህጉራችን አፍሪካ የማንቂያ ደወል መሆናቸውንና የአፍሪካንም አቅም ማጋለጡን አመልክተዋል።

በመሆኑም በቀጣይ አፍሪካ በአህጉሩ የዳበረ እና የተሳለጠ ንግድ እንዲኖር በማድረግ ከአፍሪካ ውጭ የሚገቡ ምርቶችን መቀነስ እንደምትችል ያመለከቱት ዶክተር ፍጹም ፥ ሆኖም ግን ይህ እውን እንዲሆን አገራት ምርታቸውን ከጎረቤቶቻቸው ጋር ተናበው ማስኬድ እንደሚኖርባቸው አስገንዝበዋል።

የአፍሪካ አህጉራዊ ነጻ የንግድ ቀጠና ከአፍሪካ ሕብረት አጀንዳ 2063 ዋነኛ ፕሮጀክቶች መካከል ሲሆን ፤ በንግድ እና ኢኮኖሚ ትስስር ሁሉን አካታች እና ዘላቂ እድገትን ለማምጣት የሚሠራ ነው።

ከኤርትራ በስተቀር ሁሉም አገራት የፈረሙት የዚህ ፕሮጀክት ስምምነት፣ ኢትዮጵያን ጨምሮ በ42 አገራት የጸደቀ መሆኑ ፋና በሪፖርቱ ገልጿል።





# በክልሉ በተወሰኑ አካባቢዎች ተፈጥሮ የነበረው የጸጥታ ችግር መቀረፉን የደቡብ ክልል አስታወቀ

**መዓዛ ማሞ**

አዲስ አበባ፡- በክልሉ በተወሰኑ አካባቢዎች ተፈጥሮ የነበረው የጸጥታ ችግር ተቀርፎ አንጻራዊ ሰላም መፈጠሩን የደቡብ ክልል መንግሥት አስታወቀ።

የደቡብ ክልል የመንግሥት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ቢሮ ኃላፊ ወ/ሮ ሰናይት ሰለሞን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት በክልሉ በአሌ ልዩ ወረዳ እና በኮንሶ ዞን መካከል እንዲሁም በደራሼ ልዩ ዞን የጸጥታ ችግሮች ተፈጥረው ነበር።

በአሌ ልዩ ወረዳ እና በኮንሶ ዞን መካከል ተፈጥሮ የነበረው ግጭት መነሻው የወሰን ማካለል ችግር ነው። በደራሼ ልዩ ወረዳ የነበረው ችግር በዞን ከመደራጀት ጥያቄ ጋር የተያያዘ ነው። ችግሩን የፈጠረው የሕዝቡን ጥያቄ በሃይል አስመልሳለሁ በሚል የተነሳ ቡድን እንደሆነ የኮሙኒኬሽን ኃላፊዋ ጠቁመዋል።

ይህ አጥፊ ቡድን በአጎራባች አካባቢዎች በኮንሶ ዞን፤ በሰገን ዙሪያ ወረዳ የተለያዩ ቀበሌዎች የሚኖሩ ነዋሪዎችን የማፈናቀል፣ የተለያዩ ግለሰቦችን የመግደል፣ ቤቶችን የማቃጠል እኩይ ተግባራትን ፈጽሟል። ግጭቶች በነበሩባቸው አካባቢዎች በርካታ ጥፋቶች ደርሰዋል።

የክልሉ መንግሥት የጸጥታ አካላትን ወደ አካባቢዎቹ በመላክ ከሕዝቡ እና ከአካባቢው የመስተዳድር አካላት ጋር በመወያየት እና በመነጋገር ማረጋጋት መቻሉን የቢሮ ኃላፊዋ ገልጸዋል። በቀጣይም አጥፊዎችን ለሕግ የማቅረብ ስራ እንደሚሰራ አክለው ገልጸዋል።

የክልሉ መንግሥት በአሌ ልዩ ወረዳ እና በኮንሶ ዞን ያለውን የወሰን ማካለል ጥያቄ በዘላቂነት ለመፍታት ሁለቱንም አካላት ያካተተ ከፍተኛ የባለሙያዎች ቡድን አደራጅቶ ቦታው ድረስ በመላክ ስራው ወደ መጠናቀቁ እየደረሰ እንደሆነ የገለጹት ወይዘሮ ሰናይት በደራሼ ልዩ ወረዳም ዞን የመሆን የሕዝቡን ዴሞክራሲዊ የአደረጃጀት ጥያቄን በሕግ እና በሥርዓት ለመመለስ እየተሰራ በመሆኑ ሕዝቡ እራሱን ከአጥፊ ቡድኖች በመጠበቅ ምላሹን በትዕግስት መጠባበቅ እንዳለበት ገልጸዋል።

እንደ ወይዘሮ ሰናይት አገላለጽ የብልጽግና ፓርቲ የሕዝቡን ችግር ለመፍታት እና ጥያቄዎቹን ለመመለስ ሕዝቡን አወያይቷል። የአካባቢዎቹ ጥያቄዎችም በፊትም የነበረ በውይይት ወቅትም የተነሳ ነው። የአደረጃጀት ጥያቄዎች በክልሉ በተለያዩ አካባቢዎች እንደሚነሳ አመልክተው ጥያቄዎችን ሰብሰብ አድርጎ ሁሉንም ባማከለ መልኩ ለመመለስ የክልሉ መንግሥት እየሰራ እንደሆነ ተናግረዋል።

ወይዘሮ ሰናይት እንደገለጹት በክልሉ አማሮ አካባቢ እና በጌዲኦ ዞን የተወሰነ የጸጥታ ስጋት አለ። አካባቢው ከኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ጉጂ ዞን ጋር የሚዋሰን በመሆኑ የሸኔ ቡድን ሕብረተሰቡ ላይ በከፍተኛ ሁኔታ ጥቃት እያደረሰ እንደሆነ ገልጸው በቡርጂ አዋሳኝ አካባቢዎችም ቡድኑ በከፍተኛ ደረጃ ሕዝቡን በማፈናቀል በተለያየ ጊዜያት ጥቃት እያደረሰ ነው።

የክልሉ መንግሥትም የአካባቢውን የጸጥታ ኃይል በማንቀሳቀስ እና ከሕዝቡ ጋር ተቀናጅቶ ማሕበረሰቡን ከጥቃት የመከላከል እርምጃ እየወሰደ መሆኑን ጠቁመው ከኦሮሚያ ክልል እና ከፌዴራል መንግሥት ጋር በመነጋገርም የቡድኑ እንቅስቃሴ በዘላቂነት በሚገታበት ሁኔታ ላይ እየተሰራ እንደሆነ ተናግረዋል።

ማሕበረሰቡ የአካባቢውን ሰላም ከጸጥታ ሃይሎች ጋር በመሆን መጠበቅ እንዳለበትም መይዘሮ ሰናይት አሳስበዋል።

ዜና

# የነባር እሴቶቻችን መሸርሸር ለሥነ-ምግባር ብልሹነት መስፋፋት ዋነኛ ምክንያት መሆናቸው ተገለጸ

**ማህሌት አብዱል**

አዲስ አበባ፡- ባለፉት 30 ዓመታት ውስጥ ነባር እሴቶቻችን መሸርሸራቸው ለሙስናም ሆነ ለስነ-ምግባር ብልሹነት መስፋፋት ዋነኛ ምክንያት መሆናቸውን ኡስታስ ሀሰን አሊ ገለጹ። ይህ ደግሞ እንደሃገር ዋጋ እያስከፈለን እንደሆነም ጠቁመዋል።

የአፍሪካ ሚዲያ ቴሌቪዥን መስራች እና የተለያዩ ሃይማኖታዊ ትምህርቶችን በመስጠት ሙስሊሙ ሕብረተሰብን የማነፅ ሥራ በስፋት እያከናወኑ የሚገኙት ኡስታዝ ሀሰን አሊ በተለይ ከአዲስ ዘመን ጋር በነበራቸው ቆይታ እንደገለጹት፤ በውግንና የተዘረጋው የ27 ዓመታት የኢህአዴግ ሥርዓት እስካሁን ብዙ ዋጋ እያስከፈለን ይገኛል።



አሁን ላይ ትውልዱ የሃይማኖት አባቶችን የመስማት ፍላጎቱ በመቀነሱ መክሮ የመመለሱ ጉዳይ ጊዜ የሚወስድ ሆኗል የሚሉት ኡስታስ ሀሰን፤ በመሆኑም ለዚህ ችግር ሁነኛ መፍትሔ የሚሆነው የሕግ የበላይነትን ማስፈን ነው ብለዋል።

በሌላ በኩል የኢኮኖሚው ችግር እየተባባሰ በመምጣቱ አፋጣኝ እርምጃ መውሰድ ካልተቻለ እየቀማ የሚኖር ዜጋ እየተበራከተ ይመጣል ሲሉ ኡስታዝ ሀሰን አሳስበዋል።

ኡስታዝ ሀሰን እንደገለጹት፤ ባለፈው ሥርዓት ሁሉም ሰው በተለያዩ ጉዳዮች ሲበደል ቆይቷል፤ ግን ደግሞ ከራሱ በላይ አገርንና ሕዝብን ማስቀደም ካልቻለ ኢትዮጵያን ካለችበት ችግር ሊያወጣትም ሆነ ሊያሻግራት አይችልም። ዛሬ እኔ ልጎዳ አገር ትዳን ማለት መቻል አለብን። ይህንን ማድረግ ካልቻልን ቁጭ ብለን የምንጨቃጨቅበት አገር እንኳን ይናፍቀናል።

ያለፈው ሥርዓት ትልቁ ችግር የሃይማኖት ሰዎችን ሰብስቦ ማሰሩ ነው የሚሉት ኡስታዝ ሀሰን፤ ይህ ብቻ አይደለም ቁጭ ብሎ ለመነጋገርና ችግሩን ለመፍታት ፍላጎት ያለመኖሩ ለዚህች አገር ከፍተኛ ኪሰራ አስከትሏል ብለዋል።

ያለፈው መንግሥት አክራሪነትና ጽንፈኝነት አለ ብሎ ራሱ ብዙ የሽብር ስራዎችን ሲሰራ ነበር። አለፍ ሲልም የአልቃአይዳ ክንፍ አለ የሚል ሃሳብ በምክር ቤት ሳይቀር የተናገሩበት ሁኔታ ነበር። ግን በዚህ ሰበብ የታሰሩት ሰዎች ማንነት ይታወቅ ነበር ብለዋል።

የ27ቱ ዓመታት ሥርዓት ብዙ ነባር እሴቶቻችንን እየሸረሸረ ስለመጣ ከሥልጣን ከወረደም በኋላ እስከዛሬ አይተናቸው የማናውቃቸው ችግሮች እንዲከሰቱ ሆኗል ያሉት ኡስታስ ሀሰን፤ ያም ቢሆን መፍትሔ የሌለው ነገር የለም ብለዋል።

"ኢትዮጵያ ይህንን ችግር ለመፍታት የተማረ ሰው እጥረት የለባትም። እኛ አገር ያለው ችግር ሌሎች አገሮች ያለፉበት ነው። በርካቶች በዚህ ሁኔታ ውስጥ አልፈዋል፤ አሁንም በዚያ ውስጥ ያሉ እንዲሁም ብትንትናቸው የወጣ አገራት አሉ። ስለዚህ በይቅርታ መሻገር ይገባል ብለዋል"።

ይህ ማለት ግን በጅምላ ይቅርታ ማለት ሳይሆን ችግሮችን በመለየት እና ለተፈፀሙ በደሎች የሚመለከታቸው አካላት ይቅርታ በመጠየቅ ወደፊት መራመድ እንደሚገባም ጠቁመዋል።

እንደ ኡስታስ ሀሰን ገለፃ፤ እንደእብድ ገላጋይ በማንኛውም ጉዳይ እየገቡ ሊያፋጁን የተዘጋጁ በርካታ ሃይሎች አሉ። ለእነሱ ህልውና መቀጠል የእኛን መጋደል የሚፈልጉ አሉ። በአንጻሩ ብዙ ጎሳ፤ ብዙ ሃይማኖት፤ ብዙ የፖለቲካ አመለካከት ነው ያለው። ከዚህ ሁሉ አንፃር በዚህ ዘመን ላይ ያለ የመንግሥት ባለሥልጣን፤ የሃይማኖት መሪ እና ምሁር ከሌላው ጊዜ በተለይ ድርብ ሃላፊነት አለበት ብለዋል።

የእኔ ጉዳይ ይቆይ የሚል አመራር ካልፈጠርን አገርን ማሻገር አንችልም ያሉት ኡስታስ ሀሰን፤ ሁሉም የራሱን ጉዳይ ብቻ ለማስፈፀም መሯሯጡን የሚቀጥል ከሆነ ነገ ቁጭ ብለን የምንነጋገርባት አገር አትኖረንም ሲሉም የችግሩን አሳሳቢነት ጠቁመዋል።

## የጋምቤላ ክልል...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

በገጠር የሥራ ዕድል መፍጠር የሚጠበቁ ውጤቶች ናቸው ብለዋል።

ክልሉ ከውስጥና ከውጭ ከሚያጋጥመውን ፀጥታ ችግር በዘላቂነት ለመፍታትም የክልሉ መንግሥትና ሕዝብ ከአዋሳኝ ክልሎች ጋር ተቀናጅቶ ለመስራት አቅጣጫ መቀመጡን አመልክተው፤ የጋምቤላ ነጻ አውጪ ግንባር ነኝ ብሎ ራሱን የሚጠራውንና ሸኔ ላይ የአካባቢው ስጋት እንዳይሆኑ አስፈላጊው እርምጃ ይወሰዳል ሲሉ ገልጸዋል።

በተለይ ክልሉ እነዚህን ጽንፈኞች ለማስወገድ ከኦሮሚያና ከቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልሎች ጋር በጋራ በመስራት የክልሉን አስተማማኝ ዘላቂ ሠላም ለማረጋጋጥ እንደሚሰሩ ገልጸዋል።

የጋምቤላ ክልል ከደቡብ ሱዳን ጋር በስምንት አዋሳኝ ድንበር አካባቢዎች እንደሚዋሰን ገልጸው፤ በሙርሌ ጎሳዎች ወደ ክልሉ ሰርገው በመግባት አልፎ አልፎ ጉዳት እያደረሱ በመሆናቸው ሕብረተሰቡ ከመሰል ጥቃቶች ራሱን እንዲጠብቅ እየተሰራ ነው ብለዋል።

የፌዴራል መንግሥትም ከደቡብ ሱዳን መንግሥት ጋር በመነጋገር ችግሩ በዘለቄታዊ መንገድ እንዲፈታ የዲፕሎማሲ ስራዎች እየተሰሩ መሆናቸውን ጠቅሰዋል።

ሁለቱም መንግሥታት የሁሉቱ አገራት ሕዝቦች በጋራ የሚተሳሰሩባቸውን መሠረተ ልማት ስራዎች በአዋሳኝ ድንበሮች በመስራት ችግሩን በዘላቂነት መፍታት ያስፈልጋል ያሉት ርዕሰ መስተዳድሩ፤ እስከአሁን ድረስ የተሰሩ ስራዎችና ወደፊት ለሚተገበሩ የልማት ፕሮጀክቶች ክልሉ በየጊዜው የቅርብ ክትትልና ድጋፍ እንደሚያደርግ ገልጸዋል።

ክልሉ የሕዝብ ጥያቄዎች ለመመለስ የጀመረውን ተግባራዊ እንቅስቃሴ ስኬታማ እንዲሆንም ሕዝቡን ጨምሮ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ጥሪ አቅርበዋል።

## ኢትዮጵያ ላይ ማዕቀብና ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ የዲፕሎማሲና ዓለም አቀፍ ግንኙነት መምህሩ አቶ እንዳለ ንጉሴ ተናገሩ።

አቶ እንዳለ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት በአሜሪካውያን ሁለቱ ምክር ቤቶች የቀረበው H.R.6600 ና S.3199 የተባለው ረቂቅ ሕግ መነሻው አይን ያወጣ የኒዎኮሎኒያሊዝም አስተሳሰብ በመሆኑ አዋጁን የሚያዘጋጀው ቡድን በኢትዮጵያውያን ዘንድ አንድነት እንዳይኖርና ሕዝቦቿን የመከፋፈል አጀንዳ የያዘ ነው ብለዋል።

በመሆኑም በአገር ውስጥም ሆነ ከአገር ውጭ ያለ ኢትዮጵያዊ ረቂቅ ሕጉ ላይ ትግሉንና ተቃውሞውን መቀጠል እንዳለበትና ይህን ረቂቅ ሕግ የሚያዘጋጅ አካል ከኢትዮጵያውያን ላይ እጁን እንዲያነሳ አበክሮ መታገል እንደሚጠይቅ አሳስበዋል።

ረቂቅ ሕጉ "ኢትዮጵያ ውስጥ መረጋጋት፣ ሰላምና ዴሞክራሲን ለማስፈን የሚደረገውን ጥረት ለመደገፍ" በሚል ሽፋን በዜጎች ብርቱ ትግል የወደቀውን የሽብር ቡድን እንደገና እንዲያንሰራራ በማድረግ አገሪቱን የመከፋፈል አጀንዳ እንደያዘ ጠቁመዋል።

በሌላ በኩል ሚዲያው በዚህ ረቂቅ ሕጉ ዙሪያ ለማሕበረሰቡ በቂ ግንዛቤ ከመስጠትም በላይ ይህ ሕግ እስከመጨረሻው ድረስ ተቀባይነት እንዳይኖረውና ሙሉ በሙሉ ውድቅ እንዲደረግ በትኩረት መስራት እንዳለበት ተናግረዋል።

መንግሥት በዲፕሎማቶቹ በኩል ለመላው አፍሪካውያንና ወዳጅ አገራት አሜሪካ አፍሪካን በእጅ አዙር ቅኝ ለመግዛት የምታደርገውን እንቅስቃሴና የዚህን ረቂቅ ሕግ አደገኝነት ግልፅ በማድረግ ትግል ማድረግ እንደሚገባ የዲፕሎማሲና ዓለም አቀፍ ግንኙነት መምህሩ አቶ እንዳለ አብራርተዋል።

በአሜሪካ በ2ቱ ምክር ቤቶች እየታዩ ያሉት H.R.6600ና S.3199 ረቂቅ ሕጎች ለጊዜው ባሉበት እንዲቆዩ የሚል ሃሳብ መንፀባረቁ በኢትዮጵያውያን ብርቱ ርብርብ በመሆኑ፤ የሚደረገው ሁሉ አቀፍ ትግል መቀጠል እንዳለበት ተናግረዋል።

ነገር ግን ይህ ጉዳይ ሙሉ በሙሉ ያልተቋጨ በመሆኑ አገሪቱ ኢኮኖሚያዊ ማሻሻዎችን በማድረግ፣ የንግድ አቅጣጫዎች ላይ ማስተካከያ በማድረግና ከረቂቅ ሕጎቹ መፅደቅ ጋር ተያይዘው ሊከሰቱ የሚችሉ ጫናዎችን ለመቋቋም በቂ ዝግጅት ማድረግ ይጠበቅባታል ብለዋል።

እንደ አቶ እንዳለ ገለፃ በአሜሪካኖቹ ቡድኖች የተዘጋጀው ይህ ረቂቅ ሕግ የአገሪቱን ሰላምና ዴሞክራሲን ለማስፈን በሚል ሽፋን አገሪቱን እንዲሁም እያንዳንዱን ኢትዮጵያውያን የሚጎዳ ፖሊሲ ነው።

## ‹‹መጽሐፍ መስጠት ለትውልድ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

በመንግሥት ደረጃ ብዙ መጽሐፍትን በማሰባሰብ ለአብሮኖት ቤተ መጻሐፍት ለማስረከብ ኮሚቴ ተቋቁሞ ስራ ተጀምሯል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ በውጭ ያሉ ወንድምና እህቶች እንዲሁም በአገር ውስጥ ያሉ መጽሐፍ ያላቸው ግለሰቦች ትውልድን ለማነጽ መጽሐፍ ሰብሰብ አድርገው በተቋቋመው ኮሜቴ አማካኝነት ማስረከብ እንደሚችሉ ተናግረዋል።

የአብሮኖት የቤተ መጽሐፍት ሕንጻ በጣም የሚያምርና ማራኪ መሆኑን ገልጸው፤ ቤተ መጽሐፍቱ በውስጡ መጽሐፍት ከሌለው ግንባታው ብቻውን ምሉዕ አያደርገውም። መጽሐፍ ለማሟላትም ሁላችንም መተባባር እንዳለብን መልዕክት አስተላልፈዋል።

ይህ ቤተ መጽሐፍት ቤት በመጽሐፍ ሲሞላ ደግሞ ሌላ እንሰራለን ያሉት ዶክተር ዐቢይ፤ በዚሁ እሳቤና እምነት መጽሐፍ ያላችሁ እውቀትን ለትውልድ ማካፈል አትራፊ መሆኑን ተገንዝባችሁ ሰዎችን በእውቀት አንጹ ብለዋል።

በርካታ እውቀትና መረጃ የሚገኘው መጽሐፍ በማንበብ እውቀትን እያሳደጉና እየላቁ ሲሄዱ መሆኑን ጠቁመው፤መጽሐፍ መስጠት በርካታ የእውቀት ብርሃን ያላቸውና ለአገር የሚበጁ ሰዎችን ማፍራት እንደሚያስችል አስታውቀዋል።

መጽሐፍ መስጠት፤ ያለንን ማካፈልና እውቀትን ማስረጽ ለትውልድ የሚተርፍ ተግባር ነው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ሁሉም ያለውን መጽሐፍ ፣ ዕውቀትና ሃሳብ ቢያበረክት በመላ አገሪቱ ሰዎች እውቀት የሚገበዩበትን ማዕከል መፍጠር እንደሚያስችል አስገንዝበዋል።

ሁሉም ኢትዮጵያውያን ሃሳብምና መጽሐፍም እየሰጡ አብሮኖት ቤተ መጽሐፍትን ሙሉ እንዲያደርጉትም ጥሪ አቅርበዋል። በቅርቡም ሌላ የሳይንስ ዕውቀት የሚገበይበት ዘመናዊና በአይነቱ ልዩ የሆነ የሳይንስ ሙዚየም ከተወሰኑ ወራቶች በኋላ ግንባታው ተጠናቆ እንደሚከፈትም ጠቁመዋል።

በትናትናው ዕለትም ቤተልሄም ሰለሞን የተባለች ግለሰብ አምስት ሺህ 200 የተለያዩ መጽሐፍቶችን ከእንግሊዝ አገር በማሳባሰብ ለቤተ መጽሐፍቱ በስጦታ ያበረከተች ሲሆን ማይክሮሊንክ የኢንፎርሜሽንና ቴክኖሎጂ ኮሌጅ 287፣ አምባሳደር ማርቆስ የተባሉ ግለሰብም 904፣ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መመህር የነበሩና ህይወታቸው የለፈ ግለሰብ በቤተሰቦቻቸው 997 መጻሐፍትን በጥቅሉ ከሰባት ሺህ በላይ መጻሐፍቶችን ለአብሮኖት ቤተ መጻሐፍት በስጦታ አስረክበዋል። በዕለቱም ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ በስፍራው በመገኘት ለበጎ ፈቃደኞቹ የተዘጋጀላቸውን የምስክር ወረቀት ሰጥተዋል።

የአብሮኖት ቤተ መጽሐፍት ባለፉት ሶስት ወራት ከበጎ ፈቃደኞች ከ12 ሺህ በላይ መጽሐፍት በስጦታ እንደተበረከተለት ለማወቅ ተችሏል።

የቅዳሜ መጽሄት

# አገልግል



## ከ120 ብር ደመወዝ ተከፋይነት ወደ ሚሊየነርነት

- አቶ ሰለሞን ጌታቸው

ገጽ 13

## «ሁሉም የራሱን ጉዳይ ብቻ ስማስፈፀም መሯሯጡን የሚቀጥል ከሆነ ነገ ቁጭ ብለን የምንነጋገርባት ሃገር አትኖረንም»

- ኡስታስ ሃሰን አሊ
የአፍሪካ ሚዲያ ቴሌቪዥን ጣቢያ መስራች



ገጽ 6



## ትኩረት የሚሻው የምግብና ስረዓት ምግብ ጉዳይ

ገጽ 8

ከአ.አ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ቢሮ ጋር በመተባበር በየ15 ቀኑ የሚታተም

# በታክስ ከፋዮች መካከል አዎንታዊ የውድድር ስሜት መፍጠር - ብልጽግናን ማጠናከር

**ሶሎሞን በየነ**

ግብር በአገራችን ኢኮኖሚ፣ ፖለቲካና ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ ከፍተኛ ድርሻ ያለውና የታሪካችን አንድ አስኳል ነው ማለት ይቻላል። ግብር ከጥንታዊ ታሪክነቱ ባሻገር በአሁኑ ጊዜ የአንድ አገር ኢኮኖሚ፣ ሰላምና ሉዓላዊነት የጀርባ አጥንት ነው። በልመና፣ በብድርና በእርዳታ የምትኖር አገር በሚመፀውቷት፣ በሚያበድሯትና በሚረዷት አገሮች ተፅእኖ ስር ስለምትወድቅ ሉዓላዊነቷ ያለጦር መሳሪያ ይደፈራል። ዜጎች በራሳቸው ማንነት የማይተማመኑና በአገራቸው የማይመኩ የሰው አገር ቀላዋጭ እንዲሆኑ ይገደዳሉ።

በመሆኑም አንድ ኢኮኖሚዋ ያበበ፣ ሰላሟና ሉዓላዊነቷ የተጠበቀች አገር እንድትኖር እንዲሁም በአገሩና በራሱ ማንነት የሚኮራ ትውልድ ለማፍራት በራሱ ገቢ የራሱን ወጪ የሚሸፍንበት አስተማማኝ የገቢ ምንጭ ሊኖረው ይገባል። በአገራችን ብሎም በመዲናዋ ተጨባጭ ሁኔታ ደግሞ አስተማማኝ የመንግስት የገቢ ምንጭ ከታክስ የሚሰበሰበው ገቢ ነው።

ስለዚህ መንግስት ለታክስ ህጉ ተገዥ ሆነው በታማኝነት ግብራቸውን አሳውቀው በወቅቱ ለሚከፍሉ ግብር ከፋዮች እውቅናና ሽልማት መስጠት፤ በተቃራኒው ደግሞ ለታክስ ህጉ ተገዥ ያልሆኑ ግብር ከፋዮች ላይ እርምጃ የመውሰድ ኃላፊነት አለበት። ከዚህ አኳያ የአዲስ አበባ ገቢዎች ቢሮ ለታክስ ህጉ ተገዥ ሆነው በታማኝነት ግብራቸውን አሳውቀው በወቅቱ ለከፈሉ 47 ግብር ከፋዮች በፕላቲኒየም፣ 168 ግብር ከፋዮች በወርቅ እና 84 ግብር ከፋዮች ደግሞ በብር ደረጃ በጥቅሉ ለ299 ግብር ከፋዮች የእውቅና ሽልማት ከሰሞኑ ሰጥቷል።

በእውቅናና ሽልማት ስነ ስርዓቱ ወቅት የቢሮው ኃላፊ አቶ ሙሉጌታ ተፈራ እንደገለጹት፤ የዕውቅና መድረኩ ዋነኛ ዓላማ ለከተማዋ ልማትና ብልፅግና በሚደረገው ርብርብ ግዴታቸውን ከመወጣት አንፃር የላቀ አስተዋፅኦ ለነበራቸው ግብር ከፋዮች እውቅና ለመስጠትና ለማበረታታት፤ ሌሎች ግብር ከፋዮችም ከእነዚህ በአርአያነት የሚጠቀሱ ታክስ ከፋዮች በመማር በቀጣይ በተሻለ ሁኔታ የግብር ግዴታቸውን እንዲወጡ ለማስቻልና በታክስ ከፋዮች መካከል አዎንታዊ የውድድር ስሜት እንዲፈጠር ለማስቻል ነው።

ስለዚህ ባላቸው ከፍተኛ የህግ ተገዥነት ቢሮው ለ299 ግብር ከፋዮች እውቅና የሰጠ ሲሆን፤ ከነዚህ ውስጥ 78ቱ ሴት ግብር ከፋዮች ናቸው። ለነዚህ ግብር ከፋዮች ከዕውቅናው በተጨማሪ የቅድሚያ አገልግሎት ልዩ ተጠቃሚ እንደሚሆኑ ተናግረዋል።

አያይዘውም የመዲናዋ ታክስ ከፋዩ ኅብረተሰብ ለከተማችን ብሎም ለአገራችን እድገትና ብልፅግና ለማረጋገጥ ከሚያደርጉት ግብርን የመክፈል ግዴታዎች በተጨማሪም በተለያየ መልኩ ለከተማችን ነዋሪዎች እና በአገር አቀፍ ደረጃ ድጋፎችን በማድረግ ወገንተኝነታቸውን እያረጋገጡ እንደሚገኙ ጠቁመው፤ በአገራችን ብሎም በዓለም አቀፍ ደረጃ ስጋት የሆነው የኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝን ለመከላከል፣ እንደአገር ተደቅኖብን የነበረው የህልውና አደጋ ለመከላከል፣ በጦርነቱ ምክንያት ለተፈናቀሉና በድርቅ ለተጎዱ ወገኖች በገንዘብና በዓይነት ያደረጉትን ድጋፎች ለአብነት ጠቅሰዋል።

ቢሮው ከታክስ ከፋዩ ኅብረተሰብ ጋር ያለው ግንኙነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ በመምጣቱ ግብርን አሳውቆ በወቅቱ ከመክፈል አንፃር ያለው ተሳትፎ ከቀን ወደ ቀን እየተሻሻለ መምጣቱን የገለጹት የቢሮው ኃላፊ፤ በዚህ አስቸጋሪ ወቅት ዕቅዱን ከመቶ በላይ ማሳካት ችሏል። ከገቢ አሰባሰብ ጋር በተያያዘ ቢሮው ባለፉት ስምንት ወራት ሊሰበስብ ካቀደው 34 ነጥብ 06 ቢሊዮን ብር ውስጥ 39 ነጥብ 5 ቢሊዮን ብር ወይም የዕቅዱን 116 በመቶ መሰብሰብ ተችሏል። ይህ አፈጻጸም ከባለፈው ተመሳሳይ ወቅት ከተሰበሰበው 29 ነጥብ 4 ቢሊዮን ብር ጋር ሲነጻጸር የ34 በመቶ ብልጫ አለው። እንዲሁም በ2014 በጀት ዓመት 48 ነጥብ 8 ቢሊዮን ብር ለመሰብሰብ ከተያዘው እቅድ ውስጥ 81 ነጥብ 4 በመቶውን በስምንት ወር ውስጥ ማሳካት ተችሏል።

እንዲሁም ባለፉት ስምንት ወራት ውስጥ ከቀረበው 6ሺ 537 የታክስ ውሳኔ ቅሬታ ውስጥ 6 ሺ 299 ወይም 96 በመቶ ምላሽ እንዲያገኙ ተደርጓል። በአንጻሩ 353 ተጠርጣሪዎች ያለደረሰኝ ግብይት ሲፈጽሙ በመገኘታቸው በፖሊስ እጅ ከፍንጅ ተይዘው ምርመራ እየተደረገባቸው ይገኛል ብለዋል።

ቢሮው የግብር ከፋዩን ጉልበት፣ ጊዜና ወጪ ሊቀንሱ የሚችሉ አዳዲስ አሠራሮችን ሥራ ላይ እያዋለ እንደሚገኝ ኃላፊው ጠቅሰው፤ በ2013 ዓ.ም የግብር ማሳወቂያ ወቅት አዲስ አሠራር በማልማት ሥራ ላይ እያዋለ በሚገኘው "የኢቲ ታክስ" የቴክኖሎጂ ውጤት 213ሺ 523 የደረጃ "ሐ" ግብር ከፋዮች በአጭር የጽሁፍ መልዕክት ግብራቸውን በማሳወቅ እንዲከፍሉ ማድረግ ተችሏል። በቀጣይ የደረጃ "ሀ" እና "ለ" ግብር ከፋዮችም በሚለማው ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ በማድረግ አገልግሎቱን ፈጣንና ቀልጣፋ ለማድረግ አቅጣጫ መያዙን ገልጸዋል።

በዕውቅና አሰጣጥ መድረኩ የክብር እንግዳ የነበሩት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክትል ከንቲባና የሥራ፣ ኢንተርፕራይዝና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ ኃላፊ አቶ ጃንጥራር ዓባይ በበኩላቸው፤ በአገራችን ሕዝቦች መካከል የነበረው የእርስ በርስ የመከባበር፣ የመቻቻልና የመረዳዳት እሴቶቻችንን በማዳበር ያሉንን ሀብቶች (እውቀት፣ ጉልበትና ገንዘብ) የማስተባበር ሂደት የመደመር እሳቤ፣ የብልጽግና ጉዞ መሆኑን ገልጸው፤ በመደመር እሳቤ እንደከተማም ሆነ እንደአገር ተስፋ ሰጪ ውጤቶችን ማስመዝገብ መጀመሩንና እሳቤውን ሙሉ ለሙሉ ወደ ተግባር ከቀየርነው አገራችንን የስልጣኔ ማማ ላይ እንደሚያደርሳት ባሳካናቸው ጅምር ውጤቶች ማየት ይቻላል ብለዋል።

ግብርን በወቅቱ በመክፈል አገራዊ ግዴታን ለመወጣት ሌት ተቀን የሚጥሩ ታክስ ከፋዮችን እውቅና በመስጠትና በማመስገን መልካም አርአያቸውን ወደ ሌሎች ማስፋት እንደሚገባ ገልጸው፤ ለአገር እና ወገን ግድ የማይሰጣቸው ጥቂት አጭበርባሪ ታክስ ከፋዮችን ማጋለጥ እንደሚገባና እንዲህ አይነት ነጋዴዎች በወገን እና አገር ላይ እየቀለዱ እና ለእድገት እንቅፋት መሆናቸውን ሊገነዘቡና ሊስተካከሉ እንደሚገባም ምክትል ከንቲባው አሳስበዋል::

**አድራሻ፡-**

ስልክ የቢሮ ኃላፊ 0115575790
የጽ/ቤት ኃላፊ 0115575741
የሞ/ኮ/ስ/ዘ/ም/ቢ/ኃላፊ 0115575748
የታ/ጉ/ዘ/ም/ቢ/ኃላፊ 0115575608
የህግ ማ/ዘ/ም/ቢ/ኃላፊ 0115575604
Facebook page: Addis Ababa revenue bureau
Web site: http//aarevenue.gov.et
P.O. Box 27400 code 1000

**የላቀ ገቢ ለአዲስ አበባችን ብልፅግና!**

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ

## «ሁሉም የራሱን ጉዳይ ብቻ ለማስፈፀም መሯሯጡን የሚቀጥል ከሆነ ነገ ቁጭ ብለን የምንነጋገርባት ሃገር አትኖረንም»

- ኡስታስ ሃሰን አሊ
የአፍሪካ ሚዲያ ቴሌቪዥን ጣቢያ መስራች

ማህሌት አብዱል

የተወለዱትና ያደጉት አዲስ አበባ ከተማ ልዩ ስሙ መሳለሚያ በሚባለው አካባቢ ነው፡፡ ቤተሰቦቻቸው ሙስሊሞች ቢሆኑም ቄስ ትምህርት ቤት አስገብተዋቸው ፊደል ቆጥረዋል፡፡ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን ደግሞ በዝብዝ ካሳ፣ ኢኑሪትማን፣ ብላታ አየለ፣ ሸኖ እና የካቲት 23 በተባሉ ትምህርት ቤቶች ተዘዋውረው ነው የተማሩት፡፡ በመድኃኒዓለም ትምህርት ቤት ደግሞ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ተከታትለዋል፡፡ በመቀጠልም ሃረማያ ዩኒቨርሲቲ ተመድበው መማር ቢጀምሩም በጤና ማጣት ምክንያት ትምህርታቸውን አቋርጠው ወደ አዲስ አበባ ተመለሱ፡፡ ሊኩል ቴክኒክ በተባለና በፈረንሳይ መንግሥት ድጋፍ በተቋቋመ ኮሌጅ ገብተው ለሁለት ዓመት በኢንጅነሪንግ ዘርፍ ከተማሩ በኋላም በተመሳሳይ ይህንንም ትምህርት አቋረጡ፡፡ በዚህ ግን ተወስነው አልቀሩም፤ አዲስ አበባ ንግድ ሥራ ኮሌጅ (ኮሜርስ) ገብተው በፐርቼዚንግና ሰፕላይ ማኔጅመንት ተምረው ዲፕሎማቸውን አገኙ፡፡

ይሁንና በተማሩበት ሙያ ገፍተው አልሄዱም፤ የቤተሰብ ንግድ ሥራ ላይ ለጥቂት ጊዜ ብቻ ተሰማሩ።የንግዱን ዘርፍ ባህሪ መረዳት ባለመቻላቸውም ከቤተሰብ ጋር ተስማምተው መስራት ተሳናቸው። ለሃይማኖታቸው ቀናዊ አሳቤ ያላቸው እኚሁ ሰው ሙሉ ለሙሉ ትኩረታቸውን የእስላምና አስተምህሮዎችን ወደ ማጥናት አደረጉ፡፡ የተለያዩ ሃይማኖታዊ ይዘት ያላቸውን ትምህርቶችና ፅሁፎችን መፃፍና የኦዲዮ-ቪዥዋል ሥራዎችን እያዘጋጁ ለምዕመኑ ማድረስ ጀመሩ፡፡ እንዲሁም በርካታ መንፈሳዊና ዓለማዊ የትርጉም ሥራዎችን በጋዜጦች ላይ ይፅፉም ነበር፡፡ እንግዳችን 130 የሚደርሱ የቪሲዲ ሥራዎች በህትመት መልክ አቅርበዋል፡፡ ሥርጭታቸውም ጥሩ የሚባል ነበር። በትርጉም ሥራ ለህትመት ካበቋቸው ፅሁፎች መካከልም «ሲሲሲያዊው» የተሰኘው መፅሐፍ ተጠቃሽ ነው፡፡



ፎቶ፡- በኣይ አበራቸው

የሚፅፏቸው ፅሁፎች መንፈሳዊ ቢሆኑም ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍልን ጭምር የሚያናግሩ ናቸው፡፡ በተለይም ስነ-ምግባር የሚባለው ነገር ሃይማኖታዊ ምንጫቸው አንድ መሆኑ ሙስሊሙንም ሆነ ሌላውን የእምነት ተከታይ ትኩረት የሚስቡ፤ የሚያወያዩ ነበሩ፡፡ በተለይ 1983 ዓ.ም አካባቢ በኢትዮጵያ ውስጥ የትርጉም ሥራ በእጅጉ የተስፋፋበት ወቅት ስለነበር የእሳቸውም ሥራዎች ከፍተኛ እውቅና አግኝተው ነበር፡፡ በጋዜጦችና መፅሔቶች ላይ በሚያቀርቧቸው ሥራዎች ጥሩ ተቀባይነትም ያገኙሁበት ወቅት መሆኑ ደግሞ የራሳቸውን ኦዲዮቪዧል ተቋም ለመክፈት እንዳስቻላቸው ያነሳሉ፡፡ በዚህም አሳበቁ አፍሪካ ሚዲያ የተባለ የሃይማኖት ቴሌቪዥን ጣቢያ እስከመመስረት ደረሱ፡፡ በአሁኑ ወቅት ደግሞ የቴሌቪዥን ጣብያውን በማማከር ድጋፍ የሚሰጡ ሲሆን የተለያዩ ሃይማኖታዊ ትምህርቶችን በመስጠት ሙስሊሙ ህብረተሰብን የማነፅ ሥራ በስፋት እያከናወኑ ይገኛሉ፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ከዛሬ አስር ዓመት በፊት ከአወሊያ ትምህርት ቤት ጋር የተነሳውን አለመግባባት ለመፍታት የሙስሊም መፍትሔ አፈላላጊ ኮሚቴ እንዲመሰረትና ችግሩ ዘላቂ እልባት እንዲያገኝ ያደርጉት በነበረው ትግል ይታወቃሉ፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በቀደመው መንግሥት ታስረው በወህኒ ቤት ሲንገላቱ ከነበሩ ሙስሊም ወገኖች መካከልም አንዱ ነበሩ፡፡ በዚህና በሌሎችም ሃገራዊ ጉዳዮች ዙሪያ አዲስ ዘመን ጋዜጣ ሑስታስ ሀሰን አሊን የዛሬው የዘመን እንግዳ አድርጎ እንደሚከተለው ይዟቸው ቀርቧል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- 2003 ዓ.ም ሙስሊሞች ያነሱት ጥያቄ በተለይ የአወሊያ እንቅስቃሴ ውስጥ የእርሶ ተሳትፎ ምን እንደነበር ያስታውሱንና ውይይታችን እንጀምር?**

**ሑስታስ ሃሰን፡-** እንደሚታወቀው በአወሊያ የመጀመሪያውን እንቅስቃሴ ያነሱት ተማሪዎች ነበሩ። ትንሽ በሃይማኖታዊ ሥራዎች ወጣ ያልን ሰዎች ይህ ሁኔታ በዚህ መቀጠል የለበትም በሚል በተደራጀ መልኩ ከስሜታዊነት ወጥቶ ለመንግሥት ቀርቦ መፍትሔ የሚገኝበት ነገር ነበር አስበን ስንሰራ የነበረው፡፡ በተለይም ህብረተሰቡ ጋር ፊት ለፊት የነበርን ሰዎች ሰብሰብ ብለን ያንን እንቅስቃሴ ወጥ በሆነ መልኩ ለመንግሥት የሚደርስበትን መንገድ ስንቀይስ ነበር። በዚህ መሰረት መፍትሔ አፈላላጊ ኮሚቴ ከተዋቀረ በኋላ ጥያቄዎቻችንን ለመንግሥት አቀረብን፡፡ ጥያቄዎቹ በዋናነት ሶስት ናቸው፤ አወሊያ የሚባል ትልቅ ተቋም አለ፤ ይህ ትምህርት ቤት ለበርካታ ዓመታት የህዝበ-ሙስሊሙ ልጆች የሚማሩበት መንፈሳዊም፤ አካዳሚም፤ የእርዳታ ሥራዎችን አካቶ የሚሰራ ትልቅ ተቋም ነው፡፡ ያንን ተቋም ይደግፉት የነበሩት አካላት በሚሄዱበት ወቅት መንግሥት አንስቶ ለመጅሊሱ ሰጠው፡፡ አንዱ ጥያቄ መጅሊሱ ሊያስተዳድረው አይገባም የሚል ሲሆን ከዚያ ይልቅ ከህብረተሰቡ የተውጣጡ የሕብረተሰብ ክፍሎች ሊያስተዳድሩት ይገባል የሚል ነበር፡፡ ምክንያቱም በወቅቱ የነበረው መጅሊስ አንደኛ በህዝብ አልተመረጠም፤ ጊዜውም አብቅቷል፤ የአወሊያ ጉዳይ ከተነሳ በኋላ የሚወስዷቸው አንዳንድ እርምጃዎች ህዝቡን ለቁጣ በጣም አነሳስቶት ነበር፡፡ በመሆኑም በዋናነት የህዝቡ ጥያቄ የነበረው አወሊያ ህዝቡ በሚመርጠው አካል ይተዳደር የሚል ነበር፡፡

ሁለተኛ ‹‹አህባሽ ›› የሚባል የሃይማኖት ክፍል በመንግስት ጭምር መደገፉ ተገቢ አይደለም የሚል ቅሬታ የነበራቸው አካላት ነበሩ፡፡ ይህ ድጋፍና ጣልቃ ገብነት ሊቆም ይገባል የሚል ሃሳብ አንስተውም ነበር፡ ፡ ሶስተኛው ደግሞ ህዝበ-ሙስሊሙ በአጠቃላይ ራሱ በመረጣቸው አካላት ሊተዳደር ይገባል የሚል ጥያቄ ነው ለመንግሥት የተነሳው፡፡ ይሁንና እነዚህ ጥያቄዎች ሊፈቱ የሚችሉበት አግባብ በጣም ቀላል ሆኖ ሳለ፤ በወቅቱ መንግሥት ሊፈታው አልፈለገም፡፡ እኛ ከመታሰራችን በፊት ጉዳዩ በሰላም እንዲፈታ ሽማግሌዎችን አዋቅረን ለሁለት ተከታታይ ዓመታት ስንንቀሳቀስ ነበር፡፡ በእነዚህ ሂደቶች ሁሉ እጅግ የሚያሳዝን ሁኔታ ነበር ይፈፀም የነበረው፡፡ አንዱ ችግር በሃገሪቱ የሚሰማ መንግሥታዊ አካል ባለመኖሩ አዘቅት ውስጥ እየገባች መሆኑን ነው፡፡ የነበረው ችግር በይፋ እንዲታወቅም አልተፈለገም ነበር፡፡

በነገራችን ላይ ሽምግልና ኢትዮጵያን ካቆያት ባህላዊ እሴቶች አንዱና ዋነኛው ነው፡፡ በተለይም ሃይማኖትና ባህል በሽምግልና መልክ ተገልፀው ነው ይህችን ሃገር ያሸጋገሯት እንጂ ዘመናዊ የተባለው ህግ ለሁሉም ተደራሽ ሆኖ አይደለም፡፡ ከ85 በመቶ በላይ የሚሆነው ህዝብ ባህላዊ በሆነ ሽምግልና ነው ነገሮችን ሲፈታ የነበረው። ተመሳሳይ ጥያቄዎች በ1957 ዓ.ም ባሌ ላይ እኛ በተከሰስንበት መንገድ የተከሰሱ ሰዎች ንጉሱ ጋር ቀርበው ችግሩ በሽምግልና የተፈታበት ታሪካዊ ገጠመኝም አለ፡፡ ድሮም ቢሆን በጎሳና በሃይማኖት ውስጥ ግጭት ነበር፤ ባለፉት 27 ዓመታት የመጣ አይደለም፡፡ ግን ችግሮቹ የሚፈቱበት መንገድ ነው ሃገሪቱን ምስቅልቅል ውስጥ የከተታት፡፡ የኢህአዴግ ትልቁ ስህተት ነባር እሴቶችን ገንድሶ አለመተካቱ ነው፡፡ ህጉ ተደራሽ ሆኖ ፍትህ ይሰፍናል ብለን እንዳናምን በትክክል አይተገበርም፤ ይልቁንም ከነአካቴው ተጨመላልቆ የባሰ የሆነበት ሁኔታ ነው ያለው፡፡ እንዳውም ህግ አስፈፃሚ አካላት ራሳቸው ህጉን እንዳሻቸው የሚበዘብዙት ነው የሆነው፡፡ ህጉ ተጠናክሮ መውጣት አልተቻለውም፡፡ እዚህ ሃገር የሆነው ህጉ የፖለቲካ ማስፈፀሚያ ነው፡፡

እኔ በታሰርኩበት ጊዜ በቦረና ፤ በሱማሌና በተለያዩ አካባቢዎች ሰዎች በጅምላ ይታሰሩ ነበር፡፡ እነዚህ ሰዎች ጋር በቅርበት ስንነጋገር የተረዳሁት ነገር ገጠር ያለው ማህበረሰብ ከዚህ ቀደም ሲገዛበትና ሲተዳደርበት የነበሩበት እሴቶች ሁሉ እየተሸረሸሩ መምጣታቸውን ነው፡፡ በህብረተሰቡ ዘንድ ትልቅ ከበሬታ የነበራቸው የሃገር ሽማግሌዎችና የእምነት አባቶች ተቀባይነት እየጠፋ መጥቷል፡፡ መንግሥት እነዚህን የሃገር ሽግሌዎችና አባቶች ወደፊት ሲያመጣቸው የነበረው ችግሮችን ለመፍታት አይደለም የተጠቀማቸው፤ የፖለቲካ የበላይነት ለማግኘት እንጂ፡፡ በዚህ ምክንያት በሂደት ከህብረተሰቡ ነጠሏቸው። ጥቅመኛ ሆኑ፤ ህብረተሰቡ እዳውም ይህን በደምብ በመገንዘቡ አገለላቸው፡፡ ትልቁ ኪሰራ የሆነው ህብረተሰቡ በጣም የሚያከብራቸውን ሰዎች እዚህ አምጥተሽ በጥቅማ ጥቅም በመደለል ጥሩ ፊት እንዳይኖራቸው ማድረግ ነው፡፡ የሃይማኖት አባቶች ላይም የሚታየው ችግር ተመሳሳይ ነው፡፡ አሁን ላለንበት ችግርም ነፀብራቁ እነሱ ናቸው፡፡ እነዚህ የሃይማኖት አባቶች ከፖለቲካ ካድሬ ምንም የማይለዩበት ሁኔታ ነው ያለው፡፡ ህብረተሰቡ ውስጥ የነበራቸው ተቀባይነት እየተመናመነ ሄዷል፡፡ የነበራቸውን ተሰሚነት ለራሳቸው ጉዳይ ማስፈፀሚያ ነው ያደረጉት፡፡ ስለዚህ አሁን የሃይማኖት አባት የሚለውን ማንም የሚሰማ የለም፡፡ ምክንያቱም ለህዝቡ አርዓያ መሆን አልቻሉም፡፡ በተለይ ከህግ ስርዓቱ መላሸቅ ጋር ተያይዞ አሁን ላይ እጅግ ልንወጣ የማንችልበት ሁኔታ ውስጥ ነው ያለነው፡፡ እነዚህ እሴቶች ሃገሪቱን እንደካስማ ይዘውት የቆዩ ነበሩ፡፡

**አዲስ ዘመን፡- መንግሥት በሃይማኖት ተቋማት ውስጥ የሚያደርጋቸው ጣልቃ ገብነቶች የራሱን እድሜ ለማራዘም ነው ሲሉ የሚተቹ ሰዎች አሉ። እርሶ በዚህ ሃሳብ ይስማማሉ? መነግሥት በተለይ ይህንን የሚያደርገው አክራሪና ፅንፈኛ የሚላቸው ሰዎች ስለነበሩ ወይስ ከበስተጀርባ ድብቅ አላማ ስለነበረው ነው?**

**ሑስታስ ሃሰን፡-** እንዳልሽው ያለፈው መንግሥት አክራሪነትና ፅንፈኝነት አለ ብሎ ራሱ ብዙ የሽብር ሥራዎችን ሲሰራ ነበር፡፡ አለፍ ሲልም የአልቃይዳ ክንፍ አለ የሚል ሃሳብ በምክር ቤት ሳይቀር የተናገሩበት ሁኔታ ነበር፡፡ ግን በዚህ ሰበብ የታሰሩት ሰዎች ማንነት ይታወቅ ነበር፡፡ይህንን ስል በደምሳሳው ፅንፈኛ አመለካከት ያላቸው ፖለቲከኞችና የሃይማኖት ሰዎች የሉም በሚል አይደለም፡፡ ፅንፍ የወጡ የፖለቲካ አቋሞች፣ የሃይማኖት አስተሳሰቦች፣ የጎሰኝነት አመለካከቶች አሉ፡፡ የሌለ ነገር አይደለም፡፡ እንግዲህ ፅንፈኝነቱ ከነበረ ታዲያ ይህንን ለማስወገድ መንግሥት ከማን ጋር ተነጋገረ? ብለሽ ብትጠይቂ መልስ አታገኚለትም፡፡ በተመሳሳይ ያ ወቅት ለምን እንደመረጠም ጥያቄ የሚፈጥር ነገር ነው፡፡ ለ30 ዓመታት ሙሉ ፅንፈኝነት እየተስፋፋ ከነበረ መንግሥት ምንም አይነት መፍትሄ ለምን መውሰድ እንዳልቻለም ግልፅ አይደለም፡፡ ከህብረተሰቡም ጋር ለመወያየት የተደረገ ጥረት የለም፡፡ ከነአካቴውም ጉዳዩም አልነበረም።

እኛ ፅንፈኛ የምንላቸው ነገሮች ባሉበት ጊዜ ሁሉ አሳሳቢ በመሆኑ ለመንግሥት ጥቆማ ሰጥተን ነበር። ለምሳሌ የ‹‹ሃዋሪጅ›› እንቅስቃሴ አደገኛ በመሆኑ ቶሎ መፍትሔ እንዲፈለግ ተናግረን ነበር፡፡ ግን መንግሥት ጆሮውን ሊሰጠን አልፈለገም፡፡ እንዳውም የእነዚህ ነገሮች መኖራቸው በራሱ የመንግሥት ሰዎች ይፈልጓቸው ነበር። እንዲኖሩም ከለላና ድጋፍ ይሰጣቸው ነበር፡፡ ጉዳዩ ግን በወቅቱ ከነበሩ የሃይማኖት አባቶችና አመራሮች ሊያልፍ የማይገባው ነበር፡፡ ግን እንዲፈታ አይፈልጉም ነበር።፡ ከዚያ ይልቅ የአልቃይዳ ሴል ታይቷል አሉ። እነሱ እንደሚሉት እዚህ ሀገር አልቃይዳ ካለ በተለይ ለምን ላለፉት ሰባት ዓመት ሙሉ ራሱን አልገለፀም?።ይልቅ ያሉ ጥናቶች እንደሚያሳዩት ‹‹ሱፊያ›› የተባለው እንቅስቃሴ ጎልቶ የሚታይበት ባሌ አካባቢ እንኳን የዚህ እምነት ተከታዮች እምነታቸውን በቀናዊነት ከመከተል ባለፈ ሰላማዊ ኑሮ የሚኖሩ ሰዎች መሆናቸውን ነው፡፡ ይህ እንቅስቃሴ ሌሎች ሃገር ላይ በሚታይ መልኩ ኢትዮጵያን አደጋ ላይ የሚጥል አይነት እንቅስቃሴ አያደርጉም፡፡

በመሰረቱ የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ የአልቃይዳ ሴል ኢትዮጵያ ውስጥ ታይቷል ብለው ያሰሯቸው ሰዎች ፈፅሞ እንዲህ አይነት እንቅስቃሴ ውስጥ ያልነበሩ ናቸው፡፡ ይልቁንም አስቀድሜ እንዳልኩሽ የፖለቲካ ጥቅም ለማግኘት ተብሎ የተደረገ ነው፡፡ በወቅቱ ደግሞ በዓለም አቀፍ ደረጃ አክራሪነት መዋጋት ፋሽን ስለነበር ዓለምአቀፍ ተቀባይነት ለማግኘት ተብሎ ነው፡፡ እንደተባለው ደግሞ የራስን ስልጣን ማራዘሚያ ከመሆን ውጭ ሌላ አላማ አልነበረውም፡፡ እውነት እሱ እንዳሉት አልቃይዳ ቢኖር ኖሮ በተለይ በዚህ ወቅት ሃገራችን ያለችበት ሁኔታ ራሱን እንዳሻው የሚገልበት እድል ነበረው፡፡ አበድኩ ያለ ሁሉ ሊተኩስ የሚችልበት ጊዜ ላይ ነው ያለነው፡፡ ዙሪያችን ያሉት ሃገራት አብጃለሁ ብትዪ ሳያቅማሙ ነው መሳሪያ የሚሰጡሽ፡፡ በተለይ እነግብፅ እና ሱዳን ቀጥታ ጥቅማችን ላይ ቆማችኋል ብለው ነው የሚያስቡት፡፡ ስለዚህ ማንኛውንም ተቃዋሚ

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ

ኃይል ከመርዳት አይቦዝኑም፡፡ በመሆኑም በዚያ መልኩ የተደራጀ ካለ ራሱን የማይገልፅበት ምክንያት ይኖራል ብዬ አላስብም፡፡ ግን ደግሞ አሁን ላይ የኢትዮጵያ ችግር ይህ ነው ብዬ አላስብም፤ ከዚያ በላይ የባሰ ሁኔታ ውስጥ ነው ያለነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- እርሶ ያነሱት በቀድሞው ስርዓት ውስጥ የነበሩ ችግሮች አሁን በየእምነት ተቋሙ ለሚታየው ግጭትና ምስቅልቅል ምክንያት ነው ብለው ያምናሉ?**

**ኡስታስ ሃሰን፡-** እኔ አሁን ያለው ሁኔታ በጣም እንዲጎላ ያደረገው የፖለቲካው ጣልቃ ገብነት ነው። ምክንያቱም ችግሩ ሃይማኖታዊ ከሆነ መፈታት ያለበት በሃይማኖት ተቋማቱ ነው፡፡ ደግሞም ከተቋማቱ በላይ የሆነ ችግር አለ ብዬ አላምንም፡፡ ሚዛናዊ የሆኑ የሃይማኖት አባቶች እርስበርስ ባላቸው ግንኙነትም ሆነ ከሌሎች ሃይማኖት ተከታዮች ጋር የሚፈጠሩ ግጭቶች በውይይት መፈታት የሚችሉ ናቸው፡፡ ደግሞም ተፈትቶ ያውቃል። ግን አሁን ፖለቲከኞቹ እጃቸው ገብቷል። አሁን ትልቁ ችግር ፖለቲከኞቹ እጃቸውን በመከተት የራሳቸውን ተቀባይነት ማሳደግ ነው አላማቸው፡፡ ለምሳሌ አንቺ ያነሳሽው የኢህአዴግ ፓርቲ በሁሉም አደረጃጀት ውስጥ ገብቶ የሚፈተፍትበት ሁኔታ በጣም ሰፊ ነበር፡፡ እነዚህ ተቋማት ራሳቸውን በሌላ መልኩ እንዲገልፁ አይፈልግም፤ ምክንያቱም በራሱ ጨቋኝ ስለሆነ ነው፡፡ አስቀድሜ እንዳልኩሽ በ27 ዓመታት ብዙ ነባር እሴቶቻችንን እየሸረሸረ ስለመጣ ከስልጣን ከወረደም በኋላ እስከዛሬ አይተናቸው የማናውቃቸው ችግሮች እንዲከሰቱ ሆኗል። ያም ቢሆን መፍትሔ የሌለው ነገር የለም፡፡

ኢትዮጵያ ይህንን ችግር ለመፍታት የተማረ ሰው እጥረት የለባትም፡፡ እኛ ሃገር ያለው ችግር ሌሎች ሃገሮች ያላለፉበትም አይደለም፡፡ በርካቶች በዚህ ሁኔታ ውስጥ አልፈዋል፤ አሁንም በዚያ ውስጥ ያሉ እንዲሁም ብትንትናቸው የወጣ ሃገራት አሉ፡፡ ትልቁ ችግር ተማረ የሚባለው ሰው ራሱ የጥፋቱ አካል መሆኑና ምሁርነቱን ክዶ በዚህ ችግር ውስጥ ተዘፍቆ የሚታይበት ሁኔታ መኖሩ ነው፡፡ የሆነ ፖለቲካ ወይም ጎሳ ውግንና ይዞ ነው የሚወጣው፡፡ እንደመፍትሔ ይሄ ነው ብለው የሚያቀርቡት ነገር የለም፡፡ *እኔ በይቅርታ አምናለሁ፤ ያለይቅርታ ችግሮችን መሻገር እንደማይቻል እረዳለሁ፤ ግን ደግሞ በጅምላ ይቅርታ መጠየቅ መፍትሔ ነው ብዬ አላምንም፡፡ ለምሳሌ ዶክተር ዐቢይ እንደመጡ በፓርቲያቸው ስም ይቅርታ መጠየቃቸው መልካም ሆኖ ሳለ ግን ደግሞ ያጠፋው አካል ራሱ ጉዳት ያደረሰበትን የህብረተሰብ ክፍል ፊት ለፊት ወጥቶ ይቅርታ ቢጠይቅ የተሻለ ውጤት ያመጣል ብዬ አምናለሁ፡፡ ልክ ደቡብ አፍሪካ እንደተደረገው የይቅርታ ዋስትና ተሰጥቶ አጥፊው ወጥቶ የሚናገርበት እድል መፈጠር ነበረበት፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ግን እኮ አጥፊዎቹ አሁንም ድረስ ጥፋታቸውን አምነው ባልተቀበሉበት ሁኔታ ይህ እርሶ የሚሉት ነገር እውን ይሆናል ተብሎ እንዴት ይታሰባል?**

**ኡስታስ ሃሰን፡-** ልክ ነው፤ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ኢህአዴግ ላጠፋው ጥፋት ይቅርታ መጠየቃቸው ትክክል ነው፡፡ ግን ደግሞ በ27 ዓመታት ውስጥ በደል የደረሰባቸውን የህብረተሰብ ክፍሎች ቅሬታቸውንና ሃሳባቸው መጠየቅ ነበረበት ባይ ነኝ፡፡ ምክንያቱም የተፈፀሙት በደሎች መልካቸውም ሆነ ባህሪያቸው ፈፅሞ የተለያየ ነው፡፡ ይቅርታ ሲጠየቅም እንዳው ሁሉንም በደምሳሳው ሳይሆን ያለበት በተጨባጭ ስለተፈፀሙት በደሎች መሆኑን ማንሳት ያስፈልጋል፡፡ ለምሳሌ የህዝቡን ችግር መፍቻ የሆነውን የኖረ እሴት የሸረሸሩት ሰዎች አሁንም በሕይወት አሉ፤ በዚያ ስርዓት ተጠቅመዋል፤ ግን እስቲ ይቅረቡና በደላቸውን አምነው ይቅርታ ህዝቡን ይጠይቁ፡፡ ይህንን ማድረጋቸው ደግሞ ጥፋቱ እንዳይደገም ከፍተኛ አስተዋፅኦ አለው ብዬ አምናለሁ። አዲሱ ዓመራር ሲመጣ ጉዳዩ ተመሳሳይ መንገድ ውስጥ እንዳይሄድ ያስተምረዋል፡፡

እንዳልሽው አጥፊዎቹ አሁንም ድረስ ስለጥፋታቸው አምነው አልተቀበሉም፡፡ እንዳውም የ27 ዓመቱ አልበቃ ብሏቸው ነፍጥ አንስተው በመዋጋት ሃገርና ህዝብን ምንአይነት ችግር ውስጥ እንደከተቷት የሚታይ ነው፡፡ ግን እነሱ ብቻ አልነበሩም ጥፋተኞቹ፤ አሁንም ጉያችን ተሸሽግው የተቀመጡ አሉ፤ አንዳንዶቹ አቅም አንሷቸውና ተገደው መፈፀማቸውን ሲያወሩ ይደመጣሉ፡፡ ግን እነዚህ ሰዎች በይፋ ስለጥፋታቸውም ሆነ ላጠፉት ነገር ይቅርታ ሲጠይቁ አላየንም፡፡ ዝም ብለው መቀመጣቸው የሚቀጥለውን ትውልድ ጭምር ይጎዳል የሚል ስጋት አለኝ፡፡ ይህንን የምለው እነዚህን ሰዎች ይታሰሩ ከሚል አይደለም፤ ግን ደግሞ በቀጣይ በኃላፊነት የሚመጣው ሰው ተመሳሳይ ጥፋት እንዳያጠፋ ማስጠንቀቂያ ይሆነዋል፡፡ ትልቁ የእኛ ሃገር ችግር ግልፀኝነት የለም እንጂ የምንቧደናቸው ቡድኖች ጥሩ ለመስራት ሳይሆን ሌሎችን ለማጥቃት እንደሆነ እሙን ነው፡፡ አሁን ላይ በጎሳ ተቧድነን የምናጠቃቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ነገ እኛ ላይ መነሳታቸው አይቀርም፡፡ በመሆኑም ያለፈውን በግልፅ ኮንነን እንዳይደገም ካላደረግን በስተቀር ዘላቂ የሆነ ሰላም ማምጣት አይቻለንም፡፡ እነሱማሌና ሶሪያ ከእኛ በተሻለ የሚያመሳስሏቸውና የሚያስማማቸው ነገር ቢኖርም ሃገራቸውን ከመበታተን ማዳን አልቻሉም። ይህም የሆነው ያጠፋው ጥፋቱን አውቆ በመመለስና በይቅርታ ችግራቸውን መሻገር ባለመቻላቸው ነው፡፡

እኛን እንደእብድ ገላጋይ በማንኛውም ጉዳይ እየገቡ ሊያፋጁን የተዘጋጁ በርካታ ኃይሎች አሉ። ለእነሱ ህልውና መቀጠል የእኛን መጋደል የሚፈልጉ አሉ፡፡ እነዚህ ሁሉ ባሉበት ኢትዮጵያ ከሌሎች ሃገራት የተለየች አይደለችም፡፡ ብዙ ጎሳ፤ ብዙ ሃይማኖት፤ ብዙ የፖለቲካ አመለካከት ነው ያለው፡፡ በዚያ ላይ በጣም አደገኛ የሚባሉ ጎረቤቶች ነው ያሉን፡፡ ጠዋት ከእኛ ሆነው ከሰዓት ከሌላ ጋር የሚያወሩ ናቸው፡፡ ከዚህ ሁሉ አንፃር በዚህ ዘመን ላይ ያለ የመንግሥት ባለስልጣን፤ የሃይማኖት መሪ እና ምሁር ከሌላው ጊዜ በተለይ ድርብ ኃላፊነት አለበት፡፡ የእኔ ጉዳይ ይቆይ የሚል አመራር ካልፈጠርን ሃገርን ማሻገር አንችልም፡፡ ሁሉም የራሱን ጉዳይ ብቻ ለማስፈፀም መሯሯጡን የሚቀጥል ከሆነ ነገ ቁጭ ብለን የምንነጋገርባት ሃገር አትኖረንም፡፡ አሁን ላይ እኮ ከግማሽ በላይ የሚሆነው ሶሪያዊ በሃገሩ አይኖርም።

ዛሬ እነዚህ ሰዎች ወደሃገራቸው መመለስ ቢፈልጉ እንኳን የእኔ የሚሏት ሃገር የላቸውም፡፡ ሊብያውያን «ሀገራችን እንደምትፈርስ አስቀድመን መገመት ብንችል ኖሮ መሃመድ ጋዳፊ እስከልጅ ልጆቹ ለዘላለም እንዲነግስ እንፈቅድ ነበር» ነው ያሉት፡፡ ስለዚህ አሁን ያለው የመንግሥት አመራርና ዜጋ ከሌላው ጊዜ በተለየ ኃላፊነቱን መወጣት መቻል አለበት፡፡

አሁን ላይ የኢኮኖሚው ችግር እየተባባሰ ከመምጣቱ የተነሳ ብዙ ሰው የሌላው እጅ ጠባቂ ሆኗል፡፡ አፋጣኝ እርምጃ መውሰድ ካልተቻለ ሲርበው እየቀማ የሚኖር ዜጋ እየተበራከተ ይመጣል፡፡ በእስልምና ለምሳሌ «የሰረቀ እጁ ይቆረጣል» ይላል፤ ግን ደግሞ ይህ ህግ ተግባራዊ የማይሆንበት አጋጣሚ አለ፤ ከእነዚህም መካከል በድርቅና በርሃብ ጊዜ ሰርቆ የበላ ሰው እንደሃጥያተኛ ላይታይ ይችላል፡፡ ስለዚህ ባለሃብቶች የሚኖሩትን ማህበረሰብ ማዕከል ያደረገ ሥራ መስራት ይገባቸዋል፡፡ ይህች ሃገር እንድትቀጥል ከተፈለገ በተለይ ባለሃብቱ እነዚህን ወገኖች መደገፍ አለባቸው፡፡ አለበለዚያ ግን ያከማቸውን ሃብት የሚበላበት ሃገር አትኖረውም፡፡ ሁሉም ሰው በተለያየ ነገር ሊበደል ይችላል፤ ተበድሏልም፤ ግን ደግሞ ከራሱ በላይ ሃገርንና ህዝብን ማስቀደም ካልቻለ ኢትዮጵያን ካለችበት ችግር ሊያወጣትም ሆነ ሊያሻግራት አይችልም። ዛሬ እኔ ልጎዳ ሃገር ትዳን ማለት መቻል አለብን፡፡ ይህንን ማድረግ ካልቻልን ቁጭ ብለን የምንጨቃጨቅበት ሃገር እንኳን ይናፍቀናል፡፡

ያለፈው ስርዓት ሌላው ትልቁ ችግር የሃይማኖት ሰዎችን ሰብስቦ ማሰሩ ነው፤ ይህ ብቻ አይደለም ቁጭ ብሎ ለመነጋገርና ችግሩን ለመፍታት ፍላጎት ያለመኖሩ ለዚህች ሃገር ከፍተኛ ኪሰራ አስከትሏል ባይ ነኝ፡፡ የሃይማኖት አባቶች ችግሩ እንዲፈታ ሲሉ በገቡበት ቢሮ ሁሉ ሞራላቸውን ነክተው ነው የመለሷቸው፡፡ አንዳንድ ምሁራንና የሃይማኖት አባቶችም በመንግሥትና በእምነት ተቋማት መካከል የተፈጠረውን አለመግባባት ከመፍታት ይልቅ ለራሳቸው ጥቅም ያደሩ ሆነው ነው የተገኙት። እውነታውን መናገርና ፊት ለፊት ለመጋፈጥ ደፋሮች አይደሉም፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ትውልዱን ከመታደግ አኳያ የሃይማኖት ተቋማት ቀጣይ የቤት ሥራ ምን መሆን አለበት?**

**ኡስታስ ሃሰን፡-** አሁንም ቢሆን ትክክለኛ የሆኑ የሃይማኖት አባቶች የሚሰብኩት ሰላምን ነው፡፡ በተለይ በቀደሙት ዓመታት ህዝቡ መረጃ የሚያገኝበት እድል ስላልነበረው የሃይማኖት አባቶች ተሰሚነት ከፍተኛ ነበር፡፡ በአሁኑ ወቅት ደግሞ ብዙ ተወዳዳሪ አለባቸው። ኢትዮጵያ የሃይማኖት ሃገር ናት፤ ሃይማኖተኞች ግን አይደለንም፡፡ ምክንያቱም የአንድ ሃይማኖት ተቋም ተከታይ መሆንና እምነትን በህይወት መተግበር የተለያዩ ነገሮች በመሆናቸው ነው፡፡ አሁን ላይ በቁጥር ብዙ የሚባለው ወጣት ሃይማኖት ውስጥ ቢኖሩም ሃይማኖታዊ መርሆን ተከትሎ የሚንቀሳቀስ አይደለም፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት የሃይማኖት አባቶቹ ዘመኑን በዋጀ መልኩ ባለማስተማራቸው ነው፡፡ በመሰረቱ ትውልዱ በአደገኛ ሁኔታ በመበላሸቱ ጥሩ ለሆኑት አባቶች እንኳን ፈታኝ እየሆነ ነው ያለው፡፡

ስለዚህ መጀመሪያ መደረግ ያለበት ብዬ የማስበው የሃይማኖት ተቋማቱ ከስልጣን ሽሚያ አስተሳሰብ ወጥተው ተቀባይነት ላላቸው የእምነት ሰዎች እድሉን ሊሰጡ ይገባል፡፡ ለምሳሌ በእኛ ቤተ-እምነት ሁሉም በየጎራው የተከፋፈለበት ሁኔታ አለ፡፡ አንዱ አንዱን መስኪድ ይዞ ሌላውን እንዳያስተምር ይከላከላል፤ ያኛውም ተመሳሳይ ድርጊት ሲፈፅም ይስተዋላል፡፡ ይሄ ተገቢ አይደለም። ለሁሉም እድል መስጠት ያስፈልጋል። ለምዕመኑንም ሁሉንም የሚያደምጥበት እድል ሊኖረው ይገባል፡፡ ማንም ሰው በየመስኪዱ እየመሸገ እገሌ አትድረስብኝ ማለት አይገባውም፡፡ በነገራችን ላይ ይህ የሚሆንበት ምክንያት ደግሞ በምእመኑ ዘንድ ተቀባይነት የማግኘትና የጥቅም ግጭት በመኖሩ ነው፡፡ ለሁሉም እኩል መድረክ በመስጠት በሚያስተምረው ነገር እንዲመዘን ማድረግ ይቻላል፡፡ ነፃነት በሰጠን ቁጥር ህዝቡ ራሱ ያሻውን ይመርጣል፡፡ በከለከልን ቁጥር ግን ግጭቱ እየተባባሰ በመሄድ ሃገራዊ አደጋ ይዞ ሊመጣ ይችላል። መስኪዶች የሰላም ቦታ እንዲሆኑ ከተፈለገ በግልፅ መነጋገር ብቻ ነገሩን ይፈታዋል ብዬ አምናለሁ፡፡ አንድ መስኪዶች ላይ ይህ ተሞክሮ በተጨባጭ ለውጥ አምጥቶ አይተናል። በፊት የፀብ መነሻና የፍትጊያ ቦታ የሚባሉት እነዚሁ መስኪዶች ሁሉንም ያሳተፈ ስርዓት መዘርጋት በመቻላቸው ችግሮች ተፈተዋል፡፡ አለበለዚያ ግን ሁሉም እጁን ያስገባበታል፡፡



**አዲስ ዘመን፡- በሃገር አቀፍ የተስፋፋው የሙስና አስተሳሰብና ድርጊት በእምነት ተቋማት ውስጥም ጎልቶ የወጣበት ሁኔታ መኖሩን እንሰማለን፡፡ ለመሆኑ የዚህ ምክንያት ምንድን ነው ይላሉ?**

**ኡስታስ ሃሰን፡-** ለዚህ አንድ ምሳሌ ላንሳልሽ፤ በመንግሥት የኃላፊነት ቦታ የሚመደበው ሰው በመጀመሪያ ለቦታው መመጠኑንና ብቁ መሆኑን ከማረጋገጥ ይልቅ የመጣበት ጎሳ ወይም ሃይማኖቱ ነው የሚታየው።፡ ይህ የሚደረገው የራሳቸውን ጥቅም ለማስቀጠልና በሌላው ላይ ጫና ለመፍጠር በማለም ነው። ለእኔ የጥቅም መስመሩ በዚህ 30 ዓመታት ውስጥ በውግንና በተዘረጋው ስርዓት መምጣቱ ነው ለሙስና መስፋፋት ምክንያት ነው ብዬ የማስበው። ሁሉም ጥቅሙን ለማስጠበቅ ሲል ብቻ የሚከፈለውን ሁሉ ዋጋ ከፍሎ የራሱን ሰው ማሾም ነው የሚፈልገው። በሌላ በኩል ደግሞ አስቀድሜ እንዳልኩሽ ነባር እሴቶቻችን መሸርሸራቸው ለሙስናም ሆነ ለስነ-ምግባር ብልሹነት መስፋፋት ምክንያት እየሆነ ነው ያለው። አሁን ላይ ትውልዱ የሃይማኖት አባቶችን የመስማት ፍላጎቱ በመቀነሱ መክሮ የመመለሱ ጉዳይ ጊዜ የሚወስድ ይመስለኛል፡፡ በመሆኑም ለዚህ ችግር ሆነኛ መፍትሔ ነው ብዬ የማስበው የህግ የበላይነትን ማስፈን ነው፡፡

አሁን ላይ እኮ አብዛኛው የመንግሥት ሹመኛ ሥራውን እያበላሸ «አቅቶኛል» ብሎ የሚለቅበት ሁኔታ አናይም፡፡ የሚመለከተው አካልም ያንን ሰው ሲያባርረው አናይም፡፡ ምክንያቱም በተቆጠረ ሥራ አይመዘንም፡፡ እዚህ ሃገር ህዝብን መበደልና መበዝበዝ እንደሙብት ነው የሚቆጠረው፡፡ የጃፓን ጠቅላይ ሚኒስትር ሙብራት ለ20 ደቂቃ ጠፋ ብሎ 20 ደቂቃ አጎንብሶ ህዝቡን ይቅርታ ጠይቋል፡፡ አሁን እኮ ወደ ጎንም ወደ ታችም ተቧድነው ነው ህዝብን የሚበዘብዙት፡፡ ቅሬታ ብታቀርቢ እንኳን በጥቅም ሰንሰለት የተሳሰሩ በመሆኑ የሚሰማሽ አታገኚም። አሁን በየወረዳው የምንሰማው ነገር በጣም አሳፋሪ ነው። ሰዎች ገንዘብ ከፍለው ስልጣን የሚያገኙበት ሁኔታ መኖሩን እንሰማለን፡፡ ይህ ለቀጣዩ ትውልድ ጭምር የሚተርፍ አደገኛ ደረጃ ላይ ደርሷል፡፡ ሌሎች ሃገራት እንዲህ አይነቱን ችግር የፈቱት ህብረተሰቡን በማንቃትና የጋዜጠኝነት ባህል በማጎልበታቸው ነው፡፡ በተጨማሪም ግልፀኝነትና ተጠያቂነት ያለው አሰራር በሁሉም መልኩ መዘርጋት ያስፈልጋል፡፡ ይህ ችግር ደግሞ በመንግሥት ብቻ የሚፈታ አይደለም፤ የሃይማኖት አባቶችና የማህበረሰብ አንቂዎች ትልቅ ትኩረት ሰጥተው ሊሰሩበት ይገባል። የሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት በተለይ የህዝብ ተወካዮች ለህዝቡ የቀረበ ሥርዓት መፍጠር የህዝብ የልብ ትርታ ማዳመጥ መቻል አለባቸው፡፡

የእምነት ተቋማት ውስጥም ሙስና እንዲስፋፋ ያደረገው በሃገር ደረጃ ያለው ብልሹ አሰራር ነው። የቀደሙት የመንግሥት ኃላፊዎች በእምነት ተቋማት ውስጥ ያለው ጥቅም ተካፋዮች ናቸው፡፡ ስለዚህ የእምነት ሰዎች ለሚያጠፉት ጥፋት ከለላ የሚሰጣቸው የመንግሥት አካል አለ፡፡ በአንድ ወቅት ከሃጂና ኡምራ ጋር ተያይዞ ግጭት ተፈጠረና እኛ እንፍታ ብለው የገቡ የመንግሥት ሰዎች በትክክል የሚገኘውን ጥቅም ሲያውቁ ችግር ሲፈጥሩ ከነበሩት የሃይማኖት አባቶች ጋር የጥቅም ድርድር ውስጥ ገቡ፡፡ ችግሩን ከመፍታት ይልቅ የድርሻቸውን ተደራድረው አስጨምረው ወጡ፡፡ እኛም ዳግመኛ በዚህ ጉዳይ ላይ ጥያቄ እንዳናነሳ አስፈራርተው ነው የመለሱን፡፡ ስለዚህ የሙስና ሰንሰለቱ እዚህም ሆነ እዚያ የተዘረጋ ነው። በመሆኑም ችግሩ መፈታት የሚችለው ከመንግሥት በኩል ብቻ ሳይሆን በሃይማኖት ተቋማት ውስጥ ያለውን የጥቅም ሰንሰለት ማቋረጥ ሲቻል ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ ዋናው መፍትሔ የሚሆነው የህግ የበላይነትን በተጨባጭ ማስፈን ስንችል ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ስለነበረን ቆይታ በአንባቢዎቻችና በዝግጅት ክፍሉ ስም ከልብ አመሰግናለሁ፡፡**

**ኡስታስ ሃሰን፡-** እኔም አመሰግናለሁ፡፡

# ማህደረ ጤና

## ትኩረት የሚሻው የምግብና ስረዓተ ምግብ ጉዳይ

**አስናቀ ፀጋዬ**

ኢትዮጵያ ሁሉን አይነት ሰብል ለማብቀል የሚያስችላት የአየር ፀባይ የታደለች ሀገር ናት። ከጤፍ እስከ ስንዴ፣ ከስንዴ እስከ ገብስ፣ ከገብስ እስከ ጥራጥሬ እህሎች፣ ከጥራጥሬ እህሎች እስከ ቅባት እህሎች ድረስ ምድሯ ያበቅላል። አያሌ አትክልትና ፍራፍሬዎችም በኢትዮጵያ ምድር ይበቅላሉ። ለምግብነት የሚውለው የእንስሳት ሀብቷም ቀላል የሚባል አይደለም። እንደውም በቀንድ ከብት ብዛት ከአፍሪካ ቀዳሚዋ ናት።

ይህን ሁሉ ሰብል፣ አትክልትና ፍራፍሬ የማብቀል አቅም ያላትና ለምግብነት በሚውሉ የእንስሳት ሃብት የታደለች ሀገር በምግብ እጥረት ዜጎቿ ሲጎዱ ማየት ታዲያ በእጅጉ ያሳዝናል። ህፃናት በተመጣጠነ የምግብ እጥረት ምክንያት ለህልፈተ ህይወት ሲዳረጉ ማየትም ያማል። እናቶች ለጨቅላ ህፃናቶቻቸው አስፈላጊ የሆኑ ምግቦችን አጥተው ጡታቸው ሲደርቅ ማየት ይዘገንናል።

ይሁን እንጂ ሀገሪቱ ወደ ምግብነት ሊቀየር የሚችለውን ሃብቷን በሚገባ ከተጠቀመችበትና በዚህ ላይ ህዝቦቿ ጠንክረው ከሰሩ ከራሷ አልፋ ለሌሎችም እንደምትተርፍ ብዙዎች ይስማማሉ።

ዶክተር መሰረት ዘላለም በጤና ሚኒስቴር የእናቶችና የህፃናት፣ የወጣቶችና አፍላ ወጣቶች ጤና እና የስረዓተ ምግብ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ናቸው። የብሄራዊ የምግብና ስረዓተ-ምግብ ማስተባበሪያ ሴክሬታሪም ሆነው ይሰራሉ።

እርሳቸው እንደሚሉት በአሊያንስ /alliance/ 2015 በተሰኘውና የዘንድሮውን ጨምሮ ላለፉት አስራ ስድስት ዓመታት በተካሄደው ጉባኤ የተለያዩ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ሀገራትን እየደገፉ የምግብና የስረዓተ ምግብን ጉዳይን በመዳሰስ ዓመታዊ ዓለም አቀፍ የምግብ እጥረት ሪፖርት ያወጣሉ።

በዚህ ሪፖርትም ሶስት ዋና ዋና ቁልፍ ጉዳዮች የሚካተቱ ሲሆን እነዚህም ከአምስት ዓመት በታች ያሉ የህፃናት ሞት፣ ከአምስት ዓመት በታች ያሉ ህፃናት የምግብ እጥረትና የምግብ አቅርቦት ናቸው። የተባበሩት መንግሥታት በየዓመቱ የሚያወጣቸውን ሪፖርቶችን፣ የዓለም የህፃናት አድንና የህፃናት አድን ድርጅትና ሌሎችም በሀገር ውስጥ ያሉ ድርጅቶችን ያሚያወጣውን መረጃዎች



ዶክተር መሰረት ዘላለም

ፎቶ፡- በእዮብ ተፈሪ፡፡

ተንተርሰው የሀገራትን ዓመታዊ የምግብ እጥረት ደረጃ ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ ይፋ ያደርጋሉ። ለዚህም የደረጃ መለኪያዎችን ያስቀምጣሉ። በዚህም በርካታ ሀገራት ልኬታቸው ይቀመጣል።

በፈረንጆቹ 2021 መጨረሻ በወጣው ዓለም አቀፍ የምግብ እጥረት ሪፖርት መሰረትም ኢትዮጵያ ሙሉ መረጃ ከሰጡ 116 ሀገራት መካከል በ90ኛ ደረጃ ላይ ተቀምጣለች። በተቀመጠው መስፈርት መሰረትም ኢትዮጵያ 24 ነጥብ 1 ላይ ትገኛለች። ይህም በተቀመጠው አራት የደረጃ መስፈርት ውስጥ ኢትዮጵያ በምግብ እጥረት ከፍተኛ ደረጃ ላይ እንደምትገኝ ያሳያል። ይህ ደረጃ ካለፉት ዓመታት ጋር ሲወዳደር ጥሩ መሻሻሎች እንዳሉ የሚጠቁም ቢሆንም አሁንም ከፍተኛ ሥራ እንደሚጠይቅ ይናገራሉ።

በተለይ ምርታማነትን ከመጨመር፣ ከምርት አቅርቦት ማሻሻልና ከአምስት ዓመት በታች ያሉ የህፃናት የምግብ እጥረትና ሞትን መቀነስ ጋር በተያያዘ፤ የሀገሪቱን የምግብና የስረዓተ ምግብ ማሻሻል እጅግ አስፈላጊ መሆኑን ሪፖርቱ ይጠቁማል።

የምግብና የስረዓተ ምግብ ጉዳይ ለአንድ ሴክተር የሚተው ባለመሆኑ የጤና ሚኒስቴርን ጨምሮ ከግብርና ሚኒስቴርና ከሌሎች አጋር አካላት ጋር በመሆን ሥራዎችን መስራት ያስፈልጋል። አጠቃላይ የሚሰራው ሥራ ደግሞ ከጤና ጋር የሚገናኝ በመሆኑ የሁሉንም ህብረተሰብ ጤና ለማሻሻል የምግብና የስረዓተ ምግብ ጉዳይን ማሻሻል ይገባል።

የምግብና የስረዓተ ምግብ ጉዳይ የጤና ብቻ ሳይሆን የሀገር እድገት፣ የብልፅግናና አጠቃላይ እንደ ሀገር ማምጣት ለሚፈለገው ውጤት ለመድረስ የሚያስችል ጉዳይ በመሆኑ በዚህ ረገድ ሰፊ ሥራዎችን መስራት ይጠይቃል። ከሀገር ባለፈ የምስራቅ አፍሪካ ቀጣናንና የአፍሪካ አህጉርን የስረዓተ ምግብ ጉዳይ ለመለወጥና በዓለም አቀፍ ደረጃም ተወዳዳሪ ለመሆን በዚህ ላይ መስራት በእጅጉ አስፈላጊ ነው።

እንደ ዶክተር መሰረት ገለፃ በአስራ ስድስት ዓመታት ውስጥ ያሉትን መረጃዎች መተንተን ቢቻል የምግብ እጥረትን ከመቀነስ አኳያ በኢትዮጵያ ብዙ መሻሻሎች እንዳሉ ያሳያል። አሁንም ቢሆን ሀገሪቱ ከ116 ሀገራት መካከል 90ኛ ደረጃ ላይ ያለች በመሆኗ ይህን ደረጃ ማሻሻል ያስፈልጋል። ለዚህም በተለይ ምርትና ምርታማነትን ከማሻሻል አንፃር ብዙ መስራት ይጠይቃል። የህፃናትን የምግብ እጥረትና ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚከሰተውን ሞት መቀነስም የግድ ይላል። ይህም ኢትዮጵያን ወደሚፈለገው ደረጃ የሚያደርስ ትውልድ መፍጠር ይቻላል።

የምግብና የስረዓተ ምግብ ችግርን ለመፍታት የኢትዮጵያ መንግሥት በቅርቡ ንቅናቄ ጀምሯል። በተባበሩት መንግሥታት ድርጅትም የተጀመረ ከፍተኛ ንቅናቄ አለ። በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የዓለምን የምግብ ስረዓት ለመቀየር ትልቅ አጀንዳ በመያዙ እ.ኤ.አ በ2022 የአፍሪካ የመሪዎች ጉባኤ ላይም ዓመቱ የምግብና የስረዓተ ምግብ ዓመት እንዲሆን ተወስኗል። ኢትዮጵያም ይህንኑ ንቅናቄ ተቀላቅላለች።

ከዚህ አንፃር የኢትዮጵያን የምግብ ስረዓት ለመቀየር 22 ጌም ቼንጀር የተሰኙ አመላካቾች አሉ። ይህንኑ ለማሳካትም የጤና ሚኒስቴርና የግብርና ሚኒስቴር ከሌሎች አጋር አካላት ጋር ሆነው ሥራውን አስጀምረዋል። ይህንንም በስፋት መስራት ከተቻለ በርካታ ነገሮችን መለወጥ ይቻላል። እንደ ሀገርም ከተረጂነት በማለፍ የተወሳሰበ የምግብ እጥረትና ተያያዥ ችግሮች የኢትዮጵያ መገለጫዎች ሳይሆኑ ኢትዮጵያ እነዚህን ችግሮች ታሪክ አድርጋ ለሌሎች ሀገር የምትተርፍ ትሆናለች ተብሎ ይታሰባል።

ኢትዮጵያ ሰብል ለማምረት የሚያስችል ሰፊ መሬትና ምህዳር አላት። በቀንድ ከብት ሀብቷም ከአፍሪካ ቀዳሚ ናት። ይህን ሀብት ወደ ውጤት ለመቀየር ጠንካራ ሥራዎችን መስራት ከተቻለ ሀገሪቷ በብዙ ነገር ራሷን መቻል ትችላለች። ለዚህም እንደ መንግሥት የኢትዮጵያ የምግብ ስረዓትን የመቀየር ከፍተኛ አጀንዳ ተይዟል። በዚህ ውስጥ ሁሉም ተሳትፎ አድርጎ ውጤት ማምጣት ይቻላል።

# ለጤንነትዎ

## የአትክልት የጤና በረከቶች

**ሠላማዊት ውቤ**

አትክልትና አዘውትሮ መመገብ ለጤናችን ዘርፈ ብዙ ጥቅሞችን ይሰጠናል። የምግብ አፈጫጨትን ቀላል ለማድረግ እና የደም ግፊትን ለመቆጣጠር መርዳታቸው ከሚሰጡን የጤና ጥቅሞች ይጠቀሳሉ። አትክልቶች በውስጣቸው በያዙት ከፍተኛ የአንቲኦክሳይዳንት መጠን እንደ ካንሰር፣ ስትሮክ እና የካርዲዮቫስኩለር ችግሮችን ለመቅረፍ ይረዱናል። የያዙት የአንቲኦክሳይዳንት ንጥረ ነገር እና የአነስተኛ ካሎሪ መጠን የልብ ህመምን እና የስኳር በሽታን ይከላከሉልናል። አትክልቶች በውስጣቸው በያዙት ቫይታሚን A፣ ቫይታሚን K፣ ፎሌት እና ቫይታሚን B6 በሽታን የመከላከል አቅም አላቸው። አትክልት አዘውትረን በመመገባችን በሚይዙት አነስተኛ የካሎሪ መጠን ውፍረታችንን መቀነስ እንችላለን። የተስተካከለ እና ጤናማ የሰውነት አቋም እንዲኖረን ያስችሉናል።

**ቃርያ፡-** የ"ቫይታሚን ኤ"ን ንጥረ ነገር በውስጡ ይዟል። በመሆኑም ለዓይን ጥራት እና ጤናማነት ከፍተኛ ሚና ይጫወታል። በ"ቫይታሚን ሲ" እጅግ የበለጸገ በመሆኑ ቆዳችንን ጤናማና የሚያበራ እንዲሆን ያስችላል። በተጨማሪም የምግብ መፈጨት ሂደትን ያፋጥናል። ለአጥንት ጤናማነት እና ጥንካሬ እጅግ ጠቃሚ ሲሆን ለሰውነታችን ጠቃሚ ያልሆኑ ንጥረ ነገሮችን በማስወገድ እና የፋይበር ምንጭ በመሆን የሆድ ድርቀትን፣ ጉንፋንን፣ ሳልና የሣንባ ካንሰርን ይከላከልልናል። በሽታን የመከላከል አቅምን ያዳብራል። ቃርያን በመመገባችን የቆዳ መሸብሸብ አያጋጥመንም፤ ቶሎ አናረጅም።

**ሎሚ፡-** ጸረ-ባክቴሪያ ባህሪ ያለው ሲሆን በ"ቫይታሚን ሲ" የበለጸገም ነው። የሎሚ ጭማቂ በውሃ ቀላቅሎ መጠጣት ሰውነታችን የአሲድ አልካላይን ሚዛኑን ለመጠበቅ ያግዘዋል። በተጨማሪም የጉበትን ሥራ በማነቃቃት ዩሪክ አሲድና ሌሎችንም ጎጂ ንጥረ ነገሮችን ከሰውነታችን ውስጥ ለማስወገድና የሀሞት ፈሳሽንም የፈሳሽነት ባህሪውን እንዳያጣ የማድረግ ጥቅሞችን ይሰጠናል። የሎሚ ጭማቂ በ"ቫይታሚን ሲ" የበለጸገ እንደመሆኑ በህዋሳት መጎዳትና በዕድሜ መጨመር ሳቢያ የሚከሰቱትን ፍሪ ራዲካሎችን ለማስወገድ ይረዳናል። የሎሚ ጭማቂ ፀረ-ካንሰር ባሕርያት ሲኖሩት ከዕድሜ መጨመር ጋር ተያይዞ የሚመጣውን የመገጣጠሚያ አካላት በሽታን በመከላከል ረገድም ዓይነተኛ መፍትሄ ይሆነናል። በሎሚ ውስጥ ያለው ፔክቲን ፋይበር የመጥፎውን ኮልስትሮል መጠን ከመቀነሱም በላይ የመጥገብ ስሜትን ስለሚፈጥር በብዛት ከመመገብ ያግዳል።

**ቀይ ሽንኩርት፡-** በውስጡ ክሩሚየም የተባለ ንጥረ ነገር ሲኖረው ንጥረ ነገሩ የደም ግፊትንና ስኳርን ይቆጣጠርልናል። ገላን የማሳከክና የማቃጠል



አትክልት

ዓይነት ባህሪ ያላቸውን አለርጂዎች በመቆጣጠሩ ረገድ አስተዋጾው የጎላ ነው። በተለይ ንብ ሲነድፈን ትንሽ የቀይ ሽንኩርት መቀባት ከስቃይ ይታደገናል። በውስጡ የሚገኘው ክዩርስቲን የተሰኘው ንጥረ ነገር ደግሞ ካንሰርን የመከላከል ሚና ይጫወታል። ሰውነትን ከበሽታ የመከላከል አቅም ያሳድጋል። ቀይ ሽንኩርት ጥሬውን መመገብ ኮልስትሮንን ከመቆጣጠሩ ባሻገር የጤናማ ልብ ባለቤት ያደርጋል። ቀይ ሽንኩርትን በየዕለቱ መመገብ ከጨጓራ አልሰርም ይጠብቀናል።

**ድንች፡-** ውፍረትን የሚያመጣ ቢሆንም ለጨጓራ ህመም ፈውስ ነው። ለደም ግፊት ለካንሰር፣ ለኩላሊት ለራስ ምታትና ለሌሎችም በሽታዎች መድሃኒትነት አለው። በተጨማሪም የድንች ጭማቂ በተፈጥሮ በሽታ የመከላከል አቅምን ለማሻሻል፣ በየጊዜው የሚከሰትን የራስ ምታት ህመምና የወር አበባን ተከትሎ የሚከሰቱ ህመሞችን ለማስታገስ ይረዳል።

**ምንጭ፡- ጠቅሳሳ እውቀት ማዕድ**

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



(ጌታቸው በለጠ /ዳግላስ ጴጥሮስ)
gechoseni@gmail.com

የሥነ ጽሑፍና የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ ናቸው። የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በፕሬዚዳንትነት መርተዋል። ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፤ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ታትመው በሚሠራጩ የተለያዩ የኅትመት ውጤቶች ላይ (ዳግላስ ጴጥሮስ) በሚል የብዕር ስሙ በርካታ ጽሑፎችን አስነብበውናል። በግላቸው 12፣ ከሌሎች ጸሐፍት ጋር በርካታ መጻሕፍትን ለአንባብያን አቅርበዋል።

# “ተቀምጠን የሰቀልነውን፤ ቆመን ማውረድ አቃተን!”

ለርዕሱ የሰጠነውን ብሂል እንደተናገሩ የሚታመነው ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ዲነግዴ (ከ144 - 1919 ዓ.ም) ናቸው። ብልህነታቸውና ፍትሕ አዋቂነታቸው ደምቆ የሚመሰከርላቸው እኒህ ታላቅ ኢትዮጵያዊ ጎምቱ አባት ከዳግማዊ አፄ ምኒልክ እስከ ዘመነ ዘውዲቱ ተከብረውና አንቱታን አትርፈው ያለፉ “የአገር አድባር” ይሏቸው ዓይነት የዘመናቸው “የሹሞች ቁንጮ” ነበሩ።

በንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በአልጋ ወራሽ ተፈሪ መኮንን መካከል ተፈጥሮ የነበረው የፖለቲካ ሽኩቻ ግራ ያጋባቸው ሀብቴ አባ መላ፤ የአልጋ ወራሹን ፖለቲካዊ ሴራ አስመልክተው ያንን ዘመን ተሻጋሪ ብሂል ለትዝብታቸው ማዋዣ እንደተጠቀሙበት በታሪክ ድርሳናት ሳይቀር ተመዝግቦ ተላልፎልናል። መቼም ሕዝባዊ ሥነ ቃል “አባ ከና” የሚባል ባለሙብት ባይጠቀስለትም አልፎ አልፎ ግን እንዲህ ጠቋሚ መረጃ ሲገኝ “እከሌ እንደተናገረው” ብሎ ዋቢ ማመላከት አግባብ ስለመሆኑ የዘርፉ ሙያ ይመክረናል። “የለም ይህ አባባል በሌሎችም አንደበት ተነግሯል” የሚል ሞጋች ከቀረበም ለአሜንታው አንከራከርም። ሀብቴ አባ መላን ያስታወስናቸው የርዕሳችን “ባለ ሙብት” መሆናቸውን ለመግለጽ እንጂ ዝርዝር ግለ ታሪካቸውን ለመዘከር ስላልሆነ መንደርደሪያውን እዚህ ላይ ገታ አድርገን ወደ ዋናው ጉዳያችን እናዘግማለን።

**ተቀምጠን ሰቅለናቸው ቆመው የገረፉን አበሳዎቻችን፤**

ሀገራዊ መከራዎቻችንን እንዴት ስናስተናግድ እንደኖርን በውሱን የቃላት ትዝብት እንግለጽ ከተባለ ለውክልና የሚመጥነው አባባል “አታምጣው ነው እንጂ መቼስ ምን ይደረግ” የሚለው የ“ልበ ሰፊነታችን” ዳተኝነት እንደሆነ ጸሐፊው አጠንክሮ ያምናል። ዝርዝሩ በአግባቡ ይብራራል።

“ዳቦ በዋጋም በተደራሽነትም ብርቅ እስከ መሆን ደረሰ፣ ስኳር ለሞት መድኃኒትነት ቢፈለግ እንኳን መገኘት ስለመቻሉ አጠራጠረ፣ የጤፍ ዋጋ ናረ፣ ሽንኩርት ለሽታ እንኳን ጠፋ፣ ዘይት የወርቅ ያህል ተወደደ፣ የአንድ ኪሎ ሥጋ ከጠቦት መግዣ ዋጋ ጋር ተቀራረበ ወዘተ.” እያልን ስንጮኽ “መንግሥታችን” ያለ ዕውቀትና ያለ ብቃት በስልጣን ማማ ላይ አሽቀንጥሮ ያጎናቸው “ፊት አይቶ አደር” ሹሞቻችን አያፌዙ ሲዘባነኑብን ደጋግመን አድምጠናቸዋል።

የዓለም ኢኮኖሚ ሥርዓትን እየጠቀሱ፣ በወቅቱ የምንዛሪ ምንትስ እያመካኙ ፣ የመጓጓዣ ችግርን እያጦዙ፣ የጋራ ተጠቃሚ የሆኑበትን የደላሎች ሴራ እያወገዙ፣ ጉዳዩን ከእነርሱ ራስ ላይ በማውረድ ሌሎች የመንግሥት ሹመኞችን እየወቀሱ ወዘተ. ሕዝብን እየሸነገሉ መደለልን በሚገባ ተክነውበታል። ድርጊታቸውን እያወቅን እንዳላወቅን ስንሆንም “በሕዝባዊ ጅልነታችን” ተሳለቁብን።

መከረኛው ሕዝብ መዘባነናቸውን እየሰማ በሆድ ይፍጀው ትዝብት ቀን የሚገፋው “አያምጣው እንጂ መቼስ ምን ይደረግ” በሚል ቆሽት አብጋኝ ትዝብት ናላው እየዞረ መሆኑ አልገባቸውም። ለስንቱ ሀገራዊ ጉዳዮቻችን “መቼስ ምን ይደረግ!” በማለት ቁዘማ የሰርክ ባህላችን፣ እምባችን ቀለባችን ሆኖ እስከ መቼ እንደምንዘልቅ ግራ ተጋብተናል። ለነገሩ እየኖርን ነው ማለታችን እስትንፋሳችን ስላልወጣ እንጂ “ከቆሙት በታች ከሞቱት በላይ” መሆናችን የብዙኃኑ የኑሮ ገመና በሚገባ ያረጋግጥልናል። ለዚህ ሁሉ ያበቁን አጨብጭበን መርጠን፤ እያለቀስን ማውረድ የተሳነን የቢሮክራሲው ዘዋሪዎች እንደሆኑ በሚገባ ከገባን ሰነባብቷል።

ጽሑፌን ለአፍታ ያህል ገታ አድርጌ የአገሬን “ካብ አይገባ ቢሮክራሲ” በማሰብ እየተብሰለሰልኩ ባለሁበት ቅጽበት የአንድ ዕድሜ ጠገብ እናት እሪታ በእዝነ ህሊናዬ ውስጥ ሲያቃጭል ተሰማኝ። ጉዳዩ ግነት ወይንም ፈጠራ አይደለም። ይህንን ታሪክ ዛሬ አብራርቼ እገልጸዋለሁ እንጂ ከአሁን ቀደም ስሜቱ ትኩስ በነበረበት ወቅት በዚሁ ጋዜጣ ላይ በተሰበረ መንፈስና በሚቃትት ስሜት ጠቀስ አድርጌ ማለፌን ልብ ይሏል።

እኒህ እናት በወንዝ ዳር በሚገኘውና መጠነኛ ስፋት ባለው ጓሯቸው ውስጥ ጎመን እየተከሉ በመሸጥ ኑሯቸውን መደጎማቸውን ሲናገሩ ያደመጥናቸው ከራሳቸው አንደበት ነው። ያችንው ያመረቷትን ጎመን የሚሸጡትም በንፋስ የተበጣጠሰች ሸራ ከልለው ደጃፋቸው ላይ በመቸርቸር እንደሆነ ሲናገሩ የነበረው ከሞጭሟጫ ዓይናቸው ላይ የሚያዣውን እምባ እያበሱ ነበር። ይህ ጸሐፊ ያገኛቸውም ከባለቤቱ ጋር አገልግሎት ለመጠየቅ በሄደበት የወረዳ ጽ/ቤት ውስጥ ነበር።

እኒህ እናት ገርጥተዋል። ከሰውነት ተራ በመውጣትም አጽም መስለዋል። ንግግራቸውም የህመማቸውን ጥንካሬ በሚገባ ይገልጻል። በመስታወት ውስጥ አፍጥጦ ወደሚመለከታቸው የወረዳው ሠራተኛ ቀረብ በማለት፤ “ልጄ! እኔ የምኖረው ጎመን ቸርችሬ ነው። ሰሞኑን የንግድ ግብር ካልከፈልሽ እያሉ ጤና ነስተውኛል። ምኔን ልክፈል? ጦቢያ የምትበለጥገው የጎመን ግብር እየተሰበሰበ ነው? ይኼው ለእናንተ ግብሬን፤ ለፈጣሪ እምባዬን አፍስሼ ሞቴን እጠብቃለሁ።” በእጃቸው የያዟትን የተጨማደደች አስር ብር ወርውረውለት እብስ አሉ። የግብራቸውን እዳ መክፈላቸው መሆኑን ልብ ይሏል።

ይህንን ትዕይንት ያስተዋለውና በዕለቱ “በሥራ ጠል ደመወዝተኞች” ሲጉላላ የነበረው ተገልጋይ እንባውን ያፈሰሰው በገሃድ በሚታየው ዓይኑ ብቻ ሳይሆን በልቡም ጭምር ነበር። የዚህ ጽሑፍ ባለቤት ያንን የክፉ ቀን ክፉ አጋጣሚ ባነሳች ቁጥር ዛሬም ድረስ እምባ ይተናነቃታል። በአንጻሩ ያ “ተቃላቢ” ደመወዝተኛ ተብዬ በአሮጊቷ ድርጊት ተገርሞ ሲገለፍጥ ማስተዋል የትራዤዲው ሁለተኛ ገቢር ነበር። “ጦቢያ የምትበለጥገው በእውነት የጎመን ግብር እየተሰበሰበ ነው?” የእኒያን እናት መሰል ድምጾች ዛሬም አየሩ ላይ ቢፈተሹ ይጠፋሉ ማለት አይቻልም። በግብር ጉዳይ ላይ ጫን ያልኩት “የበጎ ፈቃድ የታክስ አምባሳደር” የሚል አደራና ተቀጥያ በስሜ ላይ የተጫነብኝ መሆኑን በማስታወስ ጭምር ነው።

የንግድ ስርዓቱን የሚያስተዳድሩት መንግሥታዊ ተቋማትና መሪ ተብዬዎቹ ቢሮክራቶች “ቁጭ ብለው ሰቅለው፤ ቆመው ለማውረድ የተቸገሩበትን” ዋና ጉዳይ ላስከትል። ሥጋና ጤፍ ወደፊት መገኛቸው ገበያ ላይ ሳይሆን አንድም ዝርያቸው እንዳይጠፋ ታስቦ በሚቀመጡበት “በዘረ መል” የምርምር ማእከላት ውስጥ ሄዶ መጎብኘት፤ ሁለትም “በዜግነታቸው ክብር” የመጀመሪያው ረድፍ ላይ በተቀመጡና ሀብታቸው ዋስትናቸው በሆነ “ጥቂት ምርጥ ዜጎች” ማዕድ ላይ፣ ሦስትም ፖለቲካው በሚያቀማጥላቸው ሹመኞች ቤቶች ውስጥ ብቻ እንደሚሆን ብንተነብይ አባይ ነብያት ልንባል አይገባም። ለተከራካሪ ተሟጋቾች ማሳያችን የሚከተለው ነው።

ለምሳሌ፤ መንግሥታዊ ተቀራጭ ደመወዙ ሁለት ሺህ ብር የሆነ አንድ ምስኪን ግለሰብ በስድስት ሺህ ብር ጤፍ የሚሸምተው የስንት ወር ደመወዙን ከመስሪያ ቤቱ አስቀድሞ መበደር ቢችል ነው? መልሱን መስጠት ያለባት የደመወዝ ጣራውን እንጂ የኑሮውን ሰማይ እንዳላየ አይታ “የደመወዛችሁ የስኬል ጣሪያ ይህን ያህል ነው” ብላ በሕግ የቀፈደደችው አገር ራሷ መሆኗን አስምረን እናልፋለን።

በክርስትናው ሰፈር ፆም ገድፈውም ሆነ ሃይማኖታዊ ቀኖናው እኛን አይመለከትንም በሚሉ ግለሰቦች በዋናው የኩዳዴ ቀናት ውስጥ አንድን ኪሎ ሥጋ በአንድ ሺህ ብር ከገዙ፤ ነገ ጠዋት ፋሲካ ሲጠባ ዋጋው ስንት ሊደርስ ይችላል? ለሙስሊም ወገኖቻችንም የኢድ አል ፈጥር (ረመዳን) ጨረቃ ብቅ ብላ የሁሉም የሃይማኖት ቤተሰቦች ምዕመናን ከልኳንዳ በራፍ ላይ መኮልኮል ሲጀምሩ ለአንድ ኪሎ ሥጋ ምን ያህል ሺህ ብር ሊጠየቁ እንደሚችሉ መገመት ከባድ አይሆንም። ፆማችንን በምስር እንገድፋለን የሚሉ ዜጎችም የአንድ ኪሎው ስፍር ከመቶ ብር ዘሎ ስንት እንደደረሰ ሁሉም ስለሚያውቀው ብዙ ብንጽፍበት ለቀባሪ የማርዳት ያህል ስለሚያስገምት እናልፈዋለን።

> ገበያውና ኑሯችን አቅሉን ስቶ ሲሰቀል ቁጭ ብለው ያስተውሉ የነበሩና ይመለከተናል ባይ “ምን ግዴዎች” ዛሬ በየሚዲያው “ኡኡታ!” እያሰሙ አድምጡን ቢሉ “ተቀምጣችሁ የሰቀላችሁትን ቆማችሁ ማውረድ ከተሳናችሁ ወንበራችሁን ለቃችሁ ለሌላ አስረክቡ” ብለን ሰላማዊ ሰልፍ ብንጠራ ብሶት የወለደው እርምጃ ስለሚሆን ተቆጭዎቻችን ላያመሩብን ይችላሉ።

ገበያውና ኑሯችን አቅሉን ስቶ ሲሰቀል ቁጭ ብለው ያስተውሉ የነበሩና ይመለከተናል ባይ “ምን ግዴዎች” ዛሬ በየሚዲያው “ኡኡታ!” እያሰሙ አድምጡን ቢሉ “ተቀምጣችሁ የሰቀላችሁትን ቆማችሁ ማውረድ ከተሳናችሁ ወንበራችሁን ለቃችሁ ለሌላ አስረክቡ” ብለን ሰላማዊ ሰልፍ ብንጠራ ብሶት የወለደው እርምጃ ስለሚሆን ተቆጭዎቻችን ላያመሩብን ይችላሉ። ሰሞኑን “የተከበሩ እያልን የምንሸቆጠቆጥላቸው” አንዳንድ የክልልና የፌዴራል ሁነኛ ፖለቲከኞች “ሕዝቡ ምሬት እያሰማበት ያለውን የኑሮ ውድነት በዘጠና ቀናት ውስጥ እናረጋጋለን” እያሉ በጋዜጣዊ መግለጫ ሲረባረቡ እያስተዋልን ነው። ከሆነማ እሰየው! ምን ከፋን። ችግሩ ጸጋዬ ገብረ መድኅን እንደተቀኘው መሆኑ ነው፤

**“ርሃብ ቀጠሮ ይሰጣል?**
**ወይንስ ቀን ቆጥሮ ይፈጃል?**
**“የሆድ ነገር ሆድ ይቆርጣል”**
**ይባላል ድሮም ይባላል፣**
**ይዘለዝላል ይከትፋል፣**
**ብቻ እስከሚጨርስ ድረስ፤ ሆድ ለሆድ ጊዜ ይሰጣል።**
**ስንት ሰዓት ነው የራብ አቅም?**
**ለእኔ ብጤማ ትርጉሙ፣**
**የሁለት ፊደል ድምጽ ነው፤ “ራብ” የሚሉት ከነስሙ።**

“አይነጋ መስሏት…” ይላል ብሂል አዋቂው የሀገሬ ሰው። ከሆነላቸው አሜን! ዕልል በቅምጣችን ብለን “ዘጠና ቀኗን” እንደ ርሃብ ቀን ሰብል ተግተን በጉጉት እንጠብቃለን።

እኒህን መሰል ቁጭ ብለው የተሰቀሉ፤ ነገር ግን ቆመን እናውርዳቸው ቢባል አቅምንም ሆነ ሥልጣንን የሚፈታተኑ አገራዊ ጉዳዮቻችን ብዙ የሚባሉ ብቻ ሳይሆኑ እንደ ባህር አሸዋ ሊቆጠሩ የማይችሉ እንደሆኑ ደጋግመን ጽፈናል፤ በየስብሰባውና በየሚዲያውም የሰሚ ያለህ እያለን ጮኸናል። ሲብስብንም የጥላሁን ገሠሠን ዜማ ተውሰን እያንጎራጎርን መተከዝን ስራችን ብለን ተያይዘነዋል። ካሻቸው አንባቢያንም ሊተክዙበት ይችላሉ።

**“ዘንድሮ፣ ዘንድሮ፣ ዘንድሮ፣ ዘንድሮ፣**
**የስንቱ ተወርቶ የስንቱ ተነግሮ - ዘንድሮ።**
**በዚያኛው ተገርመን ጥቂት ሳንቆይ፣**
**የዚህኛው መባስ አያስቅም ወይ።**
**ብዙ ዓመት በድብቅ ሲጓዝ ከረመና፣**
**ዘንድሮ ላይ ሲደርስ ሸክሙ አጋደለና፣**
**ተዝረክርኮ ወድቆ በግልጽ ብናየው፣**
**የዘንድሮን ነገር ዘንድሮ አወቅነው።**

“ቁጭ ብለን ሰቅለን ቆመን ለማውረድ ያስቸገረን ሌላው እንቆቅልሻችን” ድምጻችንን ሰብስበን በመስጠት ለወንበርና ለከፍተኛ ሹመት ያበቃናቸው “ኃያላን” ተመራጭ ፖለቲከኞቻችን ከመረጣቸው ሕዝብ ርቀውና ድምጻቸውን አጥፍተው የመሰወራቸው ጉዳይ እያሳሰበን ነው። እንደምንሰማው ከሆነማ ከመረጣቸው ሕዝብ ይልቅ የግል ድሎታቸውና ጥቅማቸውን በማስቀደም መንግሥት የትም ይሁን የት መኖሪያ ቤት እንዲሰጣቸው እየተሟገቱ ስለመሆኑ በተሟጠጠ ትዝብታችን “የከሌን ጉድ ሰማህ ወይ? ሰማሽ ወይ?” እየተባባልን ግርምታችንን መገላለጣችን አልቀረም። የደረጃውና የሥልጣኑ ከፍታና ዝቅታ ልዩ ጥቅም እንደሚኖረው ባይጠፋንም፤ “ትንሽ ትልቁ” ወደ ሥልጣን ኮርቻ ጠጋ ባለ ቁጥር የመረጠውን ሕዝብና በቅርበት የሚያውቀውን ወገኑን “አንተ ብትመርጠኝም አላምንህም፤ ለደህንነቴም ስጋት አለብኝ” ብሎ መንግሥት ቤት እንዲሰጠው ሲማጠን መመልከት ብዙ የሚባልለት ነው። አንድም፣ አንድም፣ አንድም … እያልን በአንድምታ የምንዘረዝራቸውን በርካታ ምክንያቶች መጠቃቀስ ቢቻልም ለጊዜው እዚሁ ላይ አቁመን በትዝብት ማለፉ ይበጃል። ሰላም ይሁን!!

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ተናጋሪው ዶሴ

## ታጣፊው ክላሽ

ምሕረት ሞገስ

አርሲ ዞን ጭላሎ ወረዳ ቀበሌ 01 ማሪያም ሰፈር አካባቢ በመሮጥ ላይ የሚገኘው አትሌት የተጋደመ አስከሬን የያል። ኅዳር 14 ቀን 2004 ዓ.ም በዛ ቦታ ላይ የተገኘው አስከሬን መልኩን በውል ለመለየት የሚስቸግር ነበር። አስከሬኑ ትኩስ አይደለም። ጭንቅላቱ ተከስክሷል። አትሌቱ አልዘገየም፤ እንደተመለከተ ‹‹991›› ደውሎ ለአርሲ ዞን ፖሊስ ጣቢያ ስለጉዳዩ ጥቆማ ሰጠ።

የጣቢያ ኃላፊው መረጃውን ተቀብሎ የምርመራ ቡድን ይዞ ቦታው ላይ ሲገኝ፤ አስከሬኑ ተጋድሞ ነበር። ካኪ ሱሪ ሬንጀር ጃኬት እና የወታደር ጫማ አድርጎ የተንጋለለው አስከሬን ማን እንደሆነ በውል ለመለየት የሚያስቸግር ነበር። ጭንቅላቱ ከመከስከሱም በተጨማሪ ሆዱ ላይ ሶስት ቦታ በስለት ተወግቷል። አፍንጫው ላይ ደም የሚታይ ሲሆን፤ ወሬው የደረሳቸው የአካባቢው ሰዎች መሰባሰብ ሲጀምሩ ማንነቱ ታወቀ። የአካባቢው ነዋሪዎች ሰለሞን ተረፈ ነው እያሉ ማልቀስ ጀመሩ።

ሰለሞን ከአካባቢው ሰው ጋር በፍቅር እና በሰላም የሚኖር ተወዳጅ ሰው በመሆኑ ሁሉም ጩኸቱን አቀለጠ። መርማሪዎቹ በለቀስተኞቹ መካከል ሆነው በሚስጥር መረጃ ማሰባሰብ ጀመሩ። የአንዱ ሰው ለቅሶ ግን የተለየ ነበር። ትዳርም ሆነ እናት፣ አባት ወይም ወንድም እና እህት በቅርብ የሌለው መሆኑን በመግለፅ ሁሉም አምርሮ ሲያለቅስ እና እየተያየ ሲላቀስ ፤ አንድ ሰው ግን በጣም እየጮኸ ‹‹ተው እያልኩህ፤ አልሰማ አልከኝ፤ እምቢ አልከኝ። ወዳጄ ጓደኛዬ›› እያለ ሲንፈቀፈቅ በሚስጥር ምርመራ የሚያካሂዱ ፖሊሶች ቀልባቸውን ሳበው። ሁሉም እየተያዩ ወደ እርሱ ተመለከቱ።

ሃምሳ አለቃ ደረጀ ማልቀሱን አላቆመም ‹‹የኔ ታጋሽ፤ የኔ አስተዋይ እያለ›› የሚያወጣቸው ቃላት ሁሉም መርማሪዎች በአንክሮ እንዲከታተሉት አስገደዳቸው። ከመርማሪዎቹ አንዱ ተጠግቶ ሟች ሰለሞን ከሚያለቅሰው ሰው ጋር ያለውን ዝምድና በመጠየቅ የሃምሳ አለቃ ደረጀ እንደሚባል ስሙን መዝግቦ ያዘ። ሰውየው ያለው ግንኙነት ሲጣራ የሟች ሰለሞን የቅርብ ጓደኛ መሆኑ ተረጋገጠ። አስክሬኑ አሰላ ሆስፒታል ደርሶ ሲመረመር ደረቱም ላይ በስለት መወጋቱ ተጠቆመ።

የአርሲ ዞን ፖሊስ መምሪያ የምርመራ ቡድን ሞቶ ተገኝቷል ስለተባለው ሰለሞን መረጃ ማሰባሰብ ቀጠለ። ሟች ከዚህ በፊት እገድልሃለሁ እያለ ይዝትበት ነበረ በማለት በእነ ሃምሳ አለቃ ደረጀ የተጠቆመው ሰው ደምሴ ባንጃው ከነባለቤቱ በቁጥጥር ስር ዋለ። በዕለቱ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ቤቱ ሲበረበር የደም ነጠብጣብ ተገኘ። ከመርማሪዎቹ መካከል የተወሰኑት ወንጀለኛውን በቀላሉ ለማግኘት የሚያስችል ፍንጭ እንዳገኙ በማመን ተደሰቱ። አንደኛዋ መርማሪ ግን መጀመሪያ የተጠረጠረውን እና አምርሮ ሲያለቅስ የታየውን የሃምሳ አለቃ ደረጄን ክፉኛ በመጠርጠሯ የነደምሴ መያዝ የምርመራውን አቅጣጫን እንዳያስት መስጋቷን በመግለፅ ይልቁኑ በተለየ መልኩ ሲያለቅስ የነበረው ጓደኛ የተባለው ሃምሳ አለቃው ላይ ትኩረት ሊደረግ ይገባል አለች።

ምርመራው

ቡድኑ እያንዳንዱን መረጃ በጥንቃቄ በመያዝ መመርመሩን ቀጠለ። መርማሪዎቹ ዘመድ አለው ወይ በማለት ሲያጣሩ አንዲት ዘመዴ ናት የሚላት እና የሚረዳት ሴት እንዳለች አረጋገጡ። ወደ ሰለሞን ቤት በመሔድ በተለይ ቀረቤታ ያላቸው ጎረቤት የሆኑት እና አንዳንዴም የቤቱን ቁልፍ ሳይቀር የሚያስቀምጥባቸው አንዲት አሮጌት ቤት ሔዱ። ሴትየዋ በእርግጥም ሰለሞን አንዳንዴ ቤተሰብ ቢመጣ እንኳ ደጅ ሆኖ እንዳይጉላላ ‹‹እኔን ብሎ ለሚመጣ ሰው ቁልፍ ስጡልኝ›› ብሎ ቁልፍ እርሳቸው ጋር እንዳስቀመጠ ተናገሩ።

አሮጊቷ ከመሞቱ ከሁለት ቀን በፊት ሟች ሰለሞን ተረፈ ‹‹ደክሞኛል ገብቼ ልተኛ›› ብሏቸው እንደነበር ጠቁመው፤ ከዛ በኋላ ግን እንዳላዩት ተናገሩ። ጨዋ፣ ታዛዥ መሆኑን በመግለፅ እንባቸውን አፈሰሱ።

በእዛው ቤት ውስጥ መርማሪዎቹ አሮጊቷን ሲጠይቁ እየሰሙ የነበሩት አዛውንት በበኩላቸው፤ ደክሞኛ ልተኛ ብሎ ከመግባቱ በፊት 11 ሰዓት አካባቢ ከአንዲት ሌላ ጊዜም ዘመዴ ናት ከሚላት ሴት ጋር አብሮ ሲሔድ እንዳዩት ተናገሩ።



### ደምሴ ባንጃው

ደምሴ ባንጃው ‹‹እገድልሃለሁ›› እያለ ይዝት ነበር መባሉን ተከትሎ ከነሚስቱ በቁጥጥር ስር ሲውል፤ ፍፁም የተረጋጋ ነበር። ‹‹ገድለሃል›› ሲባል በልበ ሙሉነት በፍፁም እርሱ ሰለሞንን እንዳልገደለ ይናገር ነበር። ደጋግመህ ትዝትበት ነበር፤ ሲባልም በፍፁም ዝቶበት እንደማያውቅ ተናገረ።

በቤቱ በተካሔደ ምርመራ ልብሱ ላይ የደም ነጠብጣብ እንደተገኘ ሲነገረው ከመደንገጥ ይልቅ በጣም በመሳቅ ደሙም የሟች ሰለሞን ሳይሆን ቀን አንድ ከማያውቀው ሰው ጋር ተደባድቦ የዛ ሰው ደም መሆኑን ተናገረ። ሲደባደብ የተጋጋጠ እጁንም አሳየ። መርማሪዎቹ እርጋታው እና በፍፁም ለሚቀርብለት ጥያቄ ምላሽ አለማጣቱ፤ ድፍረቱን በማሰብ ‹‹ይሔ ሰው ነፍሰ በላ ወንጀለኛ ነው።›› ብለው ገመቱ።

ለመልቀቅ አልደፈሩም፤ ተጨማሪ መረጃ ይሰበሰባል በማለት እዛው ማረፊያ ቤት እንዲቆይ ወሰኑ። ነገር ግን በሌላ በኩል ወንጀሉን ፈፅሞ ላይሆን ይችላል የሚል ጥርጣሬም አድሮባቸው ነበር። ከአርሲ ሆስፒታል የተገኘውን የአስክሬን የምርመራ ውጤት እንዲሁም ሟቹ ከመሞቱ በፊት ባሉ ተከታታይ ቀናት የነበረው የስልክ ልውውጥ መረጃን በመያዝ የምርመራ ቡድኑ ሥራውን ማጠናከር ቀጠለ።

### በሴላ አቅጣጫ ሴላ ምርመራ

ያለፈውን መረጃ መሠረት በማድረግ ከለቅሶ ላይ የቅርብ ጓደኛ የተባለውን እና አምርሮ ሲያለቅስ የነበረውን ሃምሳ አለቃ ደረጄ ብርሃኑና ለመጨረሻ ጊዜ አብራ ታይታለች በሚል በአዛውንቱ የተጠቆመችው እና ዘመድ ነች የተባለችውን ጥሩነሽ ደስታን የአርሲ ዞን የምርመራ ቡድን በጥርጣሬ ይዞ ለመመርመር ወሰነ። ሁለቱም ሰዎች ተይዘው ወደ ፖሊስ ጣቢያው ተወሰዱ። ቅድሚያ ምርመራ የተደረገው የሃምሳ አለቃ ደረጄ ብርሃኑ ላይ ነበር።

ከሃምሳ አለቃ ደረጄ ለመጨረሻ ጊዜ መቼ እና የት እንተደተገናኙ ሲጠየቅ ሟች ሰለሞን ተረፈ እጅግ ጓደኛው መሆኑን እርሱ ሲታመም ሥራውን ሸፍኖ ይሠራለት እንደነበር እንዲሁም ሚስጥሩን በሙሉ እንደሚነግረው እና በተደጋጋሚ ደምሴ ባንጃው እገድልሃለሁ ብሎ ይዝትበት እንደነበረ ገለጸ። መርማሪዎቹ በድጋሚ መቼ እንደተገናኙ ሲጠይቁት በአካል ሳይሆን እርሱ ገጠር እናቱ ጋር ሆኖ ሰለሞን ከመሞቱ በፊት 12 ሰዓት ላይ ደውሎለት እንደነበር። ለሊትም 7 ሰዓት ላይ ሰለሞንን ደውሎ እንዳነጋገረው ገለጸ።

‹‹ለሊት ሰባት ሰዓት እንዴት አልተኛህም›› የሚል ጥያቄ ሲቀርብለት እንደውም እናቱ ጋር እርጎ እየጠጣ እንደነበር እና እንቅልፍ ወስዶት እንዳልነበር ተናገረ። የስልክ ልውውጡ መረጃ ያለው መርማሪ ‹‹ለሊት ደውለህ ዕቃ ይዘህ ና›› ብለኸው ነበር። ለምን ማታ 12 ሰዓት ስትደውል ያንን ዕቃ ይዘህ ና ለምን አላልከም? ሲባል ‹‹በዛ ሰዓት ረስቼው ስለነበረ ነው›› የሚል ምላሽ ሰጠ።

### የስልክ ጥሪው

ሟች ሰለሞን ደክሞት ስለነበር በከባድ እንቅልፍ ውስጥ ሆኖ ለሊት 7 ሰዓት ስልኩ ጠራ። ስልኩን ሲያነሳ ጓደኛው ሃምሳ አለቃ ደረጄ ነበር። በስልኩ ውስጥ ‹‹ጥሩዬ ተዘረፈች ዕቃውን ይዘህ ና ድረስላት›› የሚል መልዕክት አስተላልፎ ስልኩ ተዘጋ። ሰለሞን ጊዜ አላጠፋም፤ ወዳጁ ጥሩዬ ሰው እንደሌለው ሰው እየተዘረፈች ነው ብሎ በማመን ልብሱን ለብሶ ተጣጣፊ ክላሹን ይዞ በር ከፍቶ ወደ ጥሩዬ ቤት ገሰገሰ። መንገድ ላይ ጥሩዬ እና ሃምሳ አለቃን ሲያገኝ መሳሪያውን ለሃምሳ አለቃው ሰጥቶ እሱ ዘራፊዎቹን በእጁ ሊፋለም ሲጣደፍ ጥሩነሽ ደስታ ኋላ ተከተለችው። አንዳች ከባድ ምት ከኋላው ጭንቅላቱ ላይ አረፈ። ሰለሞን አልቻለም ወደቀ። ጥሩነሽ ሆዱን ሶስት ጊዜ በስለት ወጋችው። ሆዱን ብቻ ሳይሆን በጭካኔ ደረቱ ላይም ስለቱን አሳረፈች።

ሁለቱ ነፍሰ በላዎች የወዳጃቸው እጅ ላይ እጃቸውን አሳረፉ። የሰለሞን ሕይወት ማለፉን ሲያውቁ ሃምሳ አለቃ ደረጄ ወደ እናቱ ቤት ሲሔድ ጥሩነሽ ወደ ቤቷ አቀናች። ግን ቀኑ ቀና አልሆነላትም። በአጋጣሚ በጠዋት ለሩጫ ልምምድ የወጣው አትሌት የሰለሞንን አስክሬን አግኝቶ ለፖሊስ ጠቆመ። የሰለሞን የጓደኛቸው የአስተዋዩ፣ ሰዎችን ሁሉ በፍቅር የሚቀርበው እና ከሁሉም ጋር በሰላም የሚኖረው ሰለሞን ሕይወቱ በገዛ እጃቸው አለፈ። ነገር ግን ይህንን ሁሉ መርማሪው ቡድን ሊያገኝበት የሚችልበት ዕድል ዝግ ነበር።

### የጥሩነሽ ቃል

እንደ ሃምሳ አለቃ ደረጄ ሁሉ ጥሩነሽም በአርሲ ዞን መርማሪ ቡድን የተለያዩ ጥያቄዎች ይዥጎደጎዱላት ጀመር። መልሶቿ አጭር እና ድፍን ነበሩ። ከሰለሞን ጋር ከመሞቱ በፊት አብራ እንደነበረች ተናገረች። በመጨረሻ በደንብ የተጠራጠረው የምርመራ ቡድን የተናገረችው ሁሉ ውሸት መሆኑን በመግለፅ ሃምሳ አለቃ ደረጄ ሁሉንም እንደነገራቸው ሲገልፅላት ማልቀስ ጀመረች። ‹‹ያሳሳተኝ ራሱ ነው።›› አለች። ይሔኔ የምርመራ ቡድኑ አባላት በሙሉ የድል አድራጊነት ስሜት ተሰማቸው። ጥያቄያቸውን ሲቀጥሉ ጥሩነሽ ይህንን ድርጊት የፈፀሙት ሰለሞን በሚሊሻነት ጊዜው የተሰጠው ታጣፊ ክላሽን ለማግኘት ብቻ መሆኑን እና ሃምሳ አለቃ ደረጄ ክላሹን ሸጠን ብዙ ብር እናገኛለን በማለቱ ሰለሞንን እንደገደሉት አመነች። ብዙ ጊዜ ክላሹን ሸጥ ሲሉት እምቢ ስላላቸው እነርሱ ሸጠው ለመጠቀም በመፈለጋቸው ወንጀሉን ለመፈፀም መነሳታቸውንም በዝርዝር አስረዳች።

### ውሳኔ...

ፖሊስ የምርመራ ስራውን አጠናቆ መረጃውን አደራጅቶ ለፍርድ ቤት አቀረበ። በእነ ሃምሳ አለቃ አቅጣጫ አሳችነት ዛቻ ይሰነዝር ነበር በመባል በጥርጣሬ ተይዞ የሰነበተው ደምሴ ባንጃው ከነባለቤቱ ድርጊቱን እንዳልፈፀመ ተረጋግጦ በነፃ ተሰናበቱ። ሃምሳ አለቃ ደረጄ ብርሃኑ እና ጥሩነሽ ደስታ ግን እያንዳንዳቸው የሃያ አምስት ዓመት እስራት ተፈረደባቸው።

መዝናኛ

# ማረፊያ/ ትዝብት

## ታዛቢዎቹን ስንታዘባቸው

**ተገኝ ብሩ**

ሁነቶች ሲበረክቱ መታዘባችን ይበዛል።መታዘባችን ባልከፋ የምንታዘበውን በሚታዘቡት ልክ አለመሆኑ ነው እንጂ ክፋቱ። አንድ ጉዳይ ተመልክቶና ስህተቶችን ነቅሶ አውጥቶ እንዲታረም በማሰብ ትዝብት ማጋራት ጥሩ ነው፤ጥሩ የማይሆነው ግን የምንታዘብበት መንገድ በራሱ ትዝብት ላይ ሲጥለን፤ስለምንታዘበው ጉዳይ ምንም ሳይገባንና ሳናውቀው መሆኑ ነው።

አሁን አሁንማ በማይቀለደው እየቀለድን በማይሾፈው ቁም ነገር እያፌዝን ትልልቅ ጉዳዮች እንደዘበት ማለፍ ጀምረናል። ሰሞኑን ማህበራዊ ጉዳይ ላይ እጅጉን የምንታዘባቸው ትዝብቶች ተበራክተዋል። ከነገር ሁሉ የሚገርመው ጉዳይ ቢኖር የሚታዘቡት ትዝብት መታዘብ ነው።እርግጥ አንድ ጉዳይ ላይ በትዝብት መልክ ሀሳብ የሚሰጠው ነገሩን ለማረም ሆኖ ሳለ፤አሁን ላይ የተላመድነው ግን ቅጥ ያጣ ነቀፌታና ፌዝ ነው።

በጉዳዩ ላይ ሀሳብ ለመስጠት የሚያስብ ሰው እንዴት በጉዳዩ ላይ ምን ያህል እውቀት አለኝ አልያም ደግሞ ስለተባለው ጉዳይ በም መንገድ ሀሳብ ልስጥ ብሎ ቀድሞ ማሰብ ያቅተዋል ጎበዝ። ወገን ምንም ነገር ሳይገባንና ሳናውቅ መተንተን ምን የሚሉት መሳት ይሆን? ወሳኝና ደምዳሚ ያለ እውቀት አውቃለሁ ብሎ የሚዘረዝር በእርግጥ ተንታኝ በዝቷል።

ምንም ያህል መልካም ንግግር ብናደርር የቱን ያህል ጥሩ ሀሳብ ብንገልፅ ከዚያ መሀል ተመርጦ አንድ ስህተት አልያም አንድ የተለየ ሀሳብ ወቶ ዋንኛው የመነጋገሪያ ርዕስ ይረሳና እንደዘበት ያን ከመሀል መዞ አጀንዳ በማድረግ በሁሉም ዘንድ ይዟዟራል። ክፉ ልማድ ተፀናውቶናል። በእርግጥም አሳዛኝ ሆነናል። ድሮ ሰዎች አምሮባቸው ስናይ ከአይን ያውጣህ እንል ነበር ዘንድሮ ላይ ምንም ያህል የሚያምር ንግግር የሚያደርግ ሰውን ስናይ አልያም ስነሰማ ከነቀፌታ ይጠብቅህ ማለት መጀመራችን አይቀርም።

ከታዘብናቸው ትዝብቶች ውስጥ አንድ ምሳሌ እንጥቀስ ጎበዝ። በነገራችን ላይ ይህንን ትዝብ የምንታዘበው ሰው ምንም ነገር ላይ መታዘብ የለበትም በሚል እምነት ሳይሆን የሚታዘበው ነገር ጠንቅቆ አውቆ ምክንያታዊ የሆነ ትዝብቱን ያቅርብ በሚል መነሾ እንደሆነ ሊታወቅ ይገባል። በእርግጥ በትክክል እና ስርዓት ባለው መንገድ የምንተቻቸው ጉዳዮች ትክክል ናቸው። ጉዳዩን በጥልቀት ማሳየትና ሙያው አስተያየት መስጠትም ይገባል። እኛ እያነሳን ያለነው ማፌዝና ተገቢ ያልሆነ ትችት ላቅርብ የሚለውን ደፋሩን ነው።

አንድ ሰሞን በስፋት ይወራ የነበረው የዝናብ ማዝነብ ወይም ደመና ማበልፀግ ቴክኖሎጂ ምንነት ሳናውቅ የተለያዩ መገናኛ ብዙኃን ላይ የቀረቡ ዜናዎች ተመልክተን ነጋሪው አካል የረገምን፤ ዝናብ እንዲዘንብ ተደርጓል ያለን ወገን ያብጠለጠልን ብዙዎች ነበርን። ለዚህ ማሳያው በወቅቱ በማህበራዊ ሚዲያ ይሰጡ የነበሩ አስተያየቶችና ይህንን የሚተቹ ፅሁፎች ናቸው።ኧረ የምን ማህበራዊ መገናኛ ብቻ አንዳንድ ትልልቅ ስም አትርፈዋል የተባሉ ሬዲዮ ጣቢያዎችም ጭምር ላይ ታዛቢዎች በዚያው መንገድ ያለእውቀት የታዘቡትን ትዝብት ምልሰን እንድንታዘባቸው አድርጎናል።

ቆዩኝማ ስለ ደመና ማበልፀግ ቴክኖሎጂ ምንነትማወቅ ስለዚያ ከማብጠልጠል በፊት አይቀድምም ነበር ጎበዝ። ሳይንስ የትኛው ጥግ ላይ ደርሶ ተፈጥሮን በቁጥጥሩ ስር ለማድረግ እየሞከረ ባለበት በዚህ ወቅት እጅጉን ቀላል የሆነውና ከተተገበረ በዚህም ብዙ ለውጥ በታየበት ደመና የማበልፀግ ብሎም የተጠራቀመውን ደመና ወደ ውሀነት (ዝናብ) መለወጥ በሚችለው ቴክኖሎጂ መተግበር ሲነገረን አልያም ወሬው ሲወራ ብዙ እንላለን።

እንዲህ ነው፤ ቴክኖሎጂው በራሱ ዝናም የሚያመነጭ አይደለም ስለዚህ ድርቅ ሲከሰት ወይም ደመና ሳይኖር በፍፁም በዚህ ቴክኖሎጂ ዝናብን ማዝነብ አይቻልም። ነገር ግን ከፍ ብሎ የተጠራቀመው ደመና ቴክኖሎጂውን በመጠቀም ወደ ሌላ በንፋስ ከመበተኑ በፊት ቀድሞ ወደ ዝናብነት መቀየር ይችላል። እናም የሆነው ይህ ነው።

“ድርቅ ሲኖር ያላዘነባችሁ አሁን ፈጣሪ ሲሰጥ እኛ ሰጠን አላችሁ” እየተባለ ብዙ ተብሎ ነበር። በወቅቱ የተገለፀው ዜና ትክክል እንኳን ባይሆን ሊሆን የሚችል ጉዳይ አይደለም አልያም በፍፁም ሊሆን አይችልም ብሎ መሞገት ነው ክፋቱ። በእውቀት የተመሰረተ በመረጃ የታገዘ አስተያየት እኮ ገንቢ ነው። ከተስተካከለ ሥራም ላይ ስህተት አይጠፋምና እሱን ለማረም እጅጉን ጠቃሚ ነው። እኛ የጠላነው መለመዱን የምንኮንነው ያኛውን ነው።

አንድ እውነት አለ ብለን የተነገረውን እውነት የሚጣረስ ጉዳይ ከሆነ እዚያ እውነት ላይ ተቁሞ አሳማኝ በሆነ መልኩ መሞገት የእውነትነቱ ማስረጃዎች አቅርቦ በተሳሳተ መንገድ የቀረበበትን ሁኔታ ማስረዳት ሲቻል እንዴት ባልተጨበጠ ማስረጃ ስለተነገረው ጉዳይ መተቸት አልያም አስተያየት መስጠት ይቻላል?ወገን ምክንያት አልባነታችን አንዱ የታዘበውን ትዝብት እኛም ተቀባብለን ማራገባችን እጅጉን ያሳስባል፤ ሁኔታችን እጅጉን ያስተዛዝባል።

ሀሳብ ከማን መጣ ሳይሆን ሀሳቡ ምንድነው ብሎ መመርመርና ጠቀሜታው አልያም ፋይዳው ምን ላይ ነው የሚለው መመርመር ይገባል። ካልሆነ ሰውየውን አይተን አባባሉን መጥላት አልያም ግለሰቡን አይተን ተገቢው ባይሆን ያለው ልክ ነው ማለት ሁለቱም ስህተቶች ናቸው። ሁለቱም ትዝብቶች ለትዝብት ይዳርጋሉ። በተለይ በተለይ መራር ቀልድና መራር ትዝብት ላይ የሚጥል መታዘብ እውቀት አልባ የሆነ የመረጃ ክፍተት የሚታይበት ግልብ የሆነ አስተያየት ይመስለኛል በሚሉት መነሻ የሚቀርብ ትችት ነው።

በመፍትሄ መልክ የሚቀርቡልን የተለያዩ ምክሮች አልያም አስተያየቶችማ ዛሬ ላይ ማብጠልጠሉን ተክነንበታል። በወጉ እንኳን ጉዳዩን መግለጥ ሳንችል ነው ወደ ማብጠልጠላችን የምንገባው። እጅግ ደግሞ የሚገርመው በማህበራዊ ሚዲያ ላይ የሚዘዋወሩ ቅንጭብ ንግግሮች ተመርኩዘው የሚሰጡ አስያየቶችና ትዝብት መሰል ስላቆች የሚታዘበውን አካል አቅም ፍንትው አድርገው መግለፃቸው ነው።

ጉዳያችን ሁሉ በፌዝ ማሳለፍ ወይን ዋንኛ የምንላቸው የጋራ ጉዳዮቻችን ዘንግተን ፌዝና ቧልት ይሁነኝ ብለን መመላለሳችን የጤና ይሆን ? እንጃልን ያሳስባል። እንደው ምን ይሻለን ይሆን ወገን። ጉዳዮችን ሁሉ ምናይበት መነፅር የምንታዘብበት ሁኔታ ስለ ጉዳዩ አልያም ስለ ተግባሩ ያለን እይታ ትርጉም ሰጥተን ነው የምናወራው። ከማን ምን እንደምንጠብቅ እኛው መድበናል። አልያም ማን ምን ለማለት እንደፈለገ ከንግግሩ ተነስተን ማብራሪያ ከራሳችን እይታና አመለካከት አንፃር ለአባባሉ መስጠታችን ይገርማል።

እንዴት አንድ ማገናዘብ የሚችል ስለ ጉዳዮች መረዳትና ማሰላሰል የሚችል አካል አንድን የሌላን ወገን አባባል እንዲህ ነው ብሎ በራሱ አተያይ ሊገመግም ይችላል። ከመነሻው አንድን ጉዳይ ስንሰማ በሚዛን አስቀምጠን ካልሆነ በተዛባ መልኩ ካየነው የቀና መስሎ ሊታየን ፈፅሞ አይችልም። የሰዎችን ሀሳብ ነቀፋና ስላቅ ለማቅረብ ብቻ የምንከታተልም በርክተናል። ሲናገር መሳሳቱን የምንፈልግ በንግግሩ ካልተሳሳተም ለንግግሩ የተጣመመ ትርጓሜን የምናበጅ ጉደኞች እኮ ሆነናል።

ይህ ደግሞ ከትክክለኝነት እጅጉ እንድንርቅ ያደርገናል። ሰውየው ገና ከማውራቱ በፊት የምንጠብቀው ጉዳይ አለ። ያንን ጉዳይ ሳያነሳ ከቀረና እኛ ያሰብነውን ካልገለፀ የሰውየው ንግግር አይጥመንም። ምክንያቱም እኛ ስለሰውየው የምናስበውና ይላል ብለን የምንጠብቀው እኛ የምናስበው ስለሚሆን።ወገን ምክንያት አልባነት ከባድ ነው። ነገራችን ይጣፍጥ ዘንድ ጉዳያችን ይሳካ ዘንዳ የምናነሳውና የምንጥለውን በደንብ መለየት ይገባል። በተለይ የምንተቸውና የምንነቅፈው ጉዳይ መታረሙን አስበን ስለጉዳዩ የበለጠ አውቀንና ተረድተን ቢሆን ገንቢና ጠቃሚ ይሆናል። ለማንኛውም ለዛ ያለው ንግግር የምንናገር ከሚታዘቡዋቸው ታዛቢዎች ይጠብቃችሁ ማለትን ወደድኩ። ቸር ያሰማን፤አበቃሁ።

# ዓለም አቀፍ



## ሀንጋሪ ከአውሮፓ ህብረት ውሳኔ በማፈንገጥ በሩሲያ ሩብል ለመገበያየት ወሰነች

አዲስ አበባ፡- ሀንጋሪ የአውሮፓ ህብረት በሞስኮ ላይ የጣለውን የኃይል ማእቀብ ውድቅ በማድረግ የሩሲያን ነዳጅ በሩሲያ መገበያያ ገንዘብ ሩብል ለመግዛት ተስማምታለች።

የሀንጋሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ቪክቶር ኦርባን እንደተናገሩት፣ ሀንጋሪ ከሩሲያ ጋር በምታደርገው የነዳጅ ግብይት በሩብል ለመክፈል መስማማቷን ተናግረዋል።

የአውሮፓ ህብረት በነዳጅ እና በጋዝ ላይ የጣለው ማዕቀብ ሀገሪቱ የማትሻገረው ቀይ መስመር ነበር በማለት ተቃውሟቸውን የገለጹት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ ሀንጋሪ የነዳጅ ግብይቱ ሩሲያ በፈለገችው መንገድ በሩብል ለማከናወን ዝግጁ ናት ማለታቸውን ሲ ጂ ቲ ኤን ዘግቧል።

የሩሲያው ፕሬዚዳንት ብላድሚር ፑቲን በሞስኮ ለተጣለው የኃይል ማዕቀብ አጸፋ ምላሽ ለመስጠት አውሮፓውያን ከሩሲያ ጋር በሚያደርጉት የነዳጅ እና ጋዝ ግብይት በሩብል ካልከፈሉ ግብይት አይኖርም በማለት ማስጠንቀቃቸው ይታወሳል።



## ሱዳናውያን በአገሪቱ መንግሥት ላይ የሚያደርጉትን ተቃውሞ ቀጥለዋል

አዲስ አበባ፡- ሱዳናውያን በወታደራዊው መንግሥት ላይ የሚያደርጉትን ሰላማዊ ሰልፍ አጠናክረው ቀጥለዋል።

በሱዳን ወታደራዊ መንግሥት እና የሲቪል አስተዳደር የነበረው ውጥረት ባለመርገቡ ባለፈው ጥቅምት ወር የሱዳን ወታደራዊ ኃይል መፈንቅለ መንግሥት አካሂዷል።

ይህንን ያልተቀበሉት ሱዳናውያን ላለፉት 5 ወራት ተቃውሟቸውን በሰላማዊ ሰልፍ ሲገልፁ የቆዩ ሲሆን፣ በርካቶችም በፀጥታ አካላት ለጉዳት እና ለህልፈት ተዳርገዋል።

በትላንትናው እለትም በሺዎች የሚቆጠሩ ሱዳናውያን ወታደራዊ መንግሥቱን በመቃወም በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ሰላማዊ ሰልፍ አካሂደዋል።

በተካሄዱ ሰልፎች የሱዳን የፀጥታ ኃይሎች አስለቃሽ ጭስ በመልቀቅ ሰልፉን ለመበተን ሙከራ ሲያደርጉ እንደነበር አፍሪካ ኒውስ ዘግቧል።

ባለፈው ጥቅምት ወር የተካሄደው የጄኔራል አብዱልፈታህ አል ቡርሀን መፈንቅለ መንግሥት አገሪቱን ለከፋ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ቀውስ ዳርጓታል ነው የተባለው።

በሀገሪቱ ያለው የዋጋ ግሽበት ከ250 በመቶ በላይ የደረሰ ሲሆን፣ ከመፈንቅለ መንግስቱ ወዲህ የዳቦ፣ የመብራት እና የነዳጅ ዋጋ በከፍተኛ ደረጃ መጨመሩም ተመላክቷል።

እንደተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የቅርብ ጊዜ ሪፖርት፣ ከ45 ሚሊዮን ሱዳናውያን ግማሽ ያህሉ የምግብ ዋስትናቸው ያልተረጋገጠ መሆኑን መረጃዎች ያመለክታሉ።

ማህበራዊ

# መጋቢ አዕምሮ

# ይቅርታ አይቅር

**በአገልጋይ ዮናታን አክሊሉ**

የምናብ ታሪካችን ወደ ችሎት ይወስደናል:: ለመጀመሪያ ጊዜ በፍርድ ቤት ችሎት ለመገኘት የተገኙ እናትን በችሎት የተነገረ አስተያየትን:: እኒህ እናት ከዚህ ቀደም በተለያዩ ቦታዎች ላይ ስለ ብዙ ጉዳይ የሆነን ሰፊ ሰልፍ ተመልክተዋል:: ቀበሌ ሄደው ከሸማቾች ለመግዛት ተሰልፈዋል:: ዳቦ ለመግዛት ተሰልፈዋል:: አውቶብስ ወረፋ ለመያዝ ተሰልፈዋል:: ዛሬ ደግሞ ፍርድ ቤት መጥተው በሰው ጋጋታ ውስጥ ናቸው:: ፍርድ ቤትም የሰው ጋጋታ ይኖራል ብለው ፈጽሙውኑ አልጠበቁም:: የፍርድ ቤቱ መዝገብ ክፍል እጅግ ብዙ በሆነ መዝገብ ተሞልቶ ሲመለከቱ ግርምትን ፈጥሮባቸዋል:: በየችሎቱ ስማቸው እየተጠራ ለመግባት ጥሪ የሚጠብቁትን የሰዎችን ትርምስምስ ተመልክተው እርሳቸውን ለፍርድ ቤት በር የዳረጋቸውን ጎረቤታቸውን "ምን አደርኩህ ልጄ?" አሉት:: እርሳቸው የሚያውቁት እንደ ባህላችን በሽማግሌ ችግርን እየፈቱ በይቅርታም ሁሉም አሸናፊ እየሆኑ የሄዱበትን አግባብ ነው::

እማማ ከችሎት ያስገኛቸው ሁለት ተከራዮቻቸው እርስ በእርስ ተጣልተው አከራዮን እናት ምስክር ሆነው መጠራታቸው ነው:: እማማ በትርምሱ ውስጥ ሆነው ንግግራቸውን በመቀጠል "ልጆቼ እዚህ ሁሉ ነገር ውስጥ ከመግባት ምናለ በጓዳችን መክረን ችግራችንን ብንፈታ? እዚህ እንግልት ውስጥ በመግባት ጊዜያችሁን ገንዘባችሁን ለምን ታጠፋላችሁ? በመነጋገር ችግራችንን ፈተን በይቅርታ ብናልፈው አይሻልም?" አሉ:: ከሳሽ ተከራይም ለምስክርነት የጠራቸውን አከራዩን "እማማ በይቅርታ ችግሩን መፍታት ያሉት እንኳን ይቅር፤ ይቅርታ እያልን አንተም ተው አንተም ተው በሚል ነገሮች እየተባባሰባቸው ሄዱ እንጂ መፍትሔ አላመጣም:: ያለኝ አማራጭ በህግ ፊት መፋረድ ነው::" አላቸው::

እማማም "ይቅርታው እንኳን ይቅር" የሚለውን አገላለጽ መላልሰው እያሰቡ ብዙ በሃሳብ ሄዱ:: በይቅርታ በሕይወት ዘመናቸው ያለፉትን ትልልቅ ጥፋት እያሰቡ ከራሳቸው ጋር አወሩ:: ደም የተቃቡ ሰዎች እንኳን ነገራቸውን በሽማግሌ እግር ስር አስቀምጠው ችግርን እየፈቱ በኖሩበት ዘመን ውስጥ እንዲህ ቀላል ጉዳዮች ወደ አደባባይ ደርሰው ወረፋ ሲይዙም አስገረማቸው:: ይቅርታ ሲቀር አብሮ መኖር የማይቻልበት እርስ በእርስ በጎሪጥ እየተያዩ መመላለስን የሚያመጣ አንዱ አሸናፊ ለመሆን ሌላውም ላለመሸነፍ ሁሉም ተሸናፊ ሆኖ እንደሚኖር በመረዳት ከራሳቸው ጋር መከሩ::

ችሎቱ ድረሱ ባላቸው ሰዓት ቢደርሱም ችሎቱ በሰዓቱ ሊጠራቸው ባለመቻሉ የመድኃኒት ሰዓት ደረሰባቸው:: አዛውንቷ አከራይ ለጡረታቸው ብለው የሰሯቸውን የሰርቪስ ክፍል ቤትን በማከራየት ገቢ ያገኛሉ:: የተከራዮቻቸው ጸብ ወደ ችሎት አምጥቷቸው የመድኃኒት ሰዓታቸውን አዛባባቸው:: ይህም ችሎቱ የማይመዘግበው ወጪያቸው ነበሩ:: የችሎቱ ሰዓት ደርሶም ተጠሩ:: የምስክር ቃልም መሰማት ጀመረ እማማም ወደ ዳኛው እየተመለከቱ "ልጄ እኔ ምስክር ሆኜ የመጣሁት ያየሁትን ለመመስከር ነው:: እርሱንም አደርጋለሁ:: ነገር ግን የእናንተንም ሰዓት ላለመሻመት ሁሉንም ነገር ሰዎች እዚህ ይዘው ሲመጡ ለምን ትቀበላላችሁ? አንዳንዱን በአካባቢ ሽማግሌዎች በወጋችን ለምን አንፈታውም? አሁን እኔም የመድኃኒት ሰዓቴ ደርሶ እዚህ መምጣቴ አግባብ ነው? እንዴት ሰው ተነጋግሮ ይቅርታ በመጠያየቅ ውስጥ ያለውን ግሩም መፍትሔ ትቶ ይጠላለፋል?" አሉ:: የችሎቱ ዳኛም የችሎት ስርዓትን አላከበሩም ብሎ ከዚህ በላይ እንዳይናገሩ አስቆማቸው::

እማማም ዳግመኛ "እግሬን አላነሳም" እያሉ ከራሳቸው ጋር እያወሩ ምስክርነታቸውን አሰምተው ተመለሱ:: ሁለቱም ተከራዮች ወደ ሰፈር ሲመለሱ እማማን ማንገላታታቸው ያስቆጫቸው በመሆኑ እማማን ሽማግሌ አድርገው ነገራቸውን ለመፍታት ተስማሙ:: እማማ በሽምግልናቸው ካሳ ቢበይኑ ለመካካስ፤ ይቅርታም በቦታው ስራውን እንዲሰራም ተስማሙ:: እንደ እማማ አይነት የሚገስጽ ኖሩ ችግሮችን ወጪ ቆጣቢ በሆነ መንገድ መፍታት ቢቻል ምንኛ መልካም በሆነ ነበር:: አለመግባባትን በመቀነስ፤ ሲፈጠርም በአነስተኛ ዋጋ ለመፍታት በመስራት::

### አለመግባባት

የሰዎች ልጅ በረጅም ታሪኩ ውስጥ ግጭት በጉልህ የሚታይ ነው:: የሰው ልጅ ከግጭት ተፋቶ መኖር የማይችል ነው ብለን መደምደም እስክንችል ድረስ የሚያደርስ የግጭት ታሪክ በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ በጉልህ ይገኛል:: ሰው አጠገቡ ካለው ሰው ጋር የመወዳጀትም ሆነ የመጋጨትን ጊዜዎችን ሊያሳልፍ ይችላል፤ ደግሞም ነው:: አለመግባባት አድጎ ወደ ግጭት ሲያመራም ኪሳራው ይከተላል:: ኪሳራውም በቀላሉ የሚከፈል ወይንም ፈጽሞውኑ የማይከፈል ሆኖም ያልፋል:: የሰው ልጅ ሕይወት ፈጽሞውኑ የማይከፈል ኪሳራ ውስጥ ተመድቦ እናገኘዋለን::

ግጭት ክቡር የሆነውን የሰውን ልጅ እየቀጠፈ ባለበት በዚህ ጊዜ ስለግጭት ማስረዳት አንባቢውን ማሰልቸት ሊሆን ይችላል:: የግጭት መነሻ የሚሆንን አለመግባባትን ወደ መግባባት ለመቀየር ሊሰራ የሚገባው ስራ ካልተሰራ አለመግባባት ግጭትን እያበዛ የሚቀጥል መሆኑ አይቀሬ እንደሆነ መረዳት አስፈላጊ ነው::

አለመግባባት በተለያዩ ምክንያቶች ሊፈጠር የሚችል ሲሆን ዋናው ጉዳይ ግን አለመግባባት እንዳይፈጠር ለማድረግ መሞከር፤ ከተሞከረም ፍሬያማ በሆነ በአነስተኛ ዋጋ ሊፈታ የሚችልበትን መንገድ መፈለግ ነው:: አለመግባባት ወደ ውጤት እንዳይመጣ የሚያደርገው ኢፍትሃዊነት ዋናው ጉዳይ ነው:: አንድ አካል እኔ ብቻ የፈለኩትን ላድርግ አንተ ግን ፍላጎትህን አምቀህ ኑር ቢል ይህ ኢፍትሃዊነትን አለመግባባትን፤ አለመግባባትም ግጭትን ይፈጥራል::

ከትላንት ታሪካችን እንደ አገር መማር እንዳንችል በአብዛኛው አንዱ የሌላኛውን ጥፋት ለማሳየት የሚሄደውን ያህል ራሱ ምን ያህል ለችግር አስተዋጽኦ እንዳደረገ መመልከት አለመቻሉ ነው:: እያንዳንዱ ሰው የሚፈጥረውን ኢፍትሃዊነት ወደ ጎን አድርጎ ሌሎች የሚፈጥሩትን ኢፍትሃዊነት የምናጎላ ከሆነ ወደ መፍትሔ መድረስ ሳንችል ቀርተን በአለመግባባትና በግጭት አዙሪት እንከርማለን:: የመፍትሔ መንገዱ ብዙ ቢሆንም በዚህ ጽሁፍ የፍላጎት ልዩነትን ማጥበብንና የይቅርታን በር እንደ መፍትሔ እናነሳቸዋለን::

### የፍላጎቶች ልዩነት

በአካባቢያችን ያሉ ልጆችን ስንመለከት ከምንረዳቸው ነገሮች መካከል አንዱ እርስ በእርስ የሚኖራቸው ግጭት የሚነሳበት ዋና ምክንያት ይገኛል:: ልጆች አብረው ሲሆኑ ሲጫወቱ፣ ሲያጠኑ ወይንም ሲመገቡ በአጠቃላይ በሰላም ቆይተው በቅጽበት ድብልቅልቅ ያለ ጸብ ውስጥ ገብተው ልናገኛቸው እንችላለን:: ቅድም ደማቅ በሆነ ጨዋታ ውስጥ የነበሩት ልጆች እንዴት በቅጽበት ጨኸት ወደ በረከተበት ጸብ ሊያመሩ ቻሉ ብለን ብንጠይቅ ምላሹ ከመካከላቸው አንዱ ኢፍትሃዊነት የገጠመው መሆኑን እንረዳለን:: ልጆቹ በተስማሙበት ህግ መሰረት ጨዋታው ሳይሄድ ሲቀር፤ አንዱ ልጅ የእርሱን ድርሻ የተነጠቀ ሲመስለው ወዘተ ግጭት ይፈጠራል:: የቅድሙ ፍቅር በቅጽበት ወደ ጸብ ይቀየራል::

የሰው ልጅ በተፈጥሮው ኢፍትሃዊነትን መቀበል የማይችል በመሆኑ የፍላጎቶች ልዩነት መኖሩ የሚያመጣው አለመግባባት በቀላሉ የሚታይ አይደለም:: መፍትሄው ፍትሃዊነትን በማስፈን ፍላጎትን ማቀራረብ እንጂ አስቀድሞ የሆነውን በማድረግ የተለየ ውጤት መጠበቅ አይደለም:: ህጻናት ለመቀበል የሚቸግራቸውን ኢፍትሃዊነት አዋቂ ሰው በተለይም የእውቀት ነጻነት የመረጃ ፍሰት ከፍተኛ በመሆነበት ዘመን ሊቀበል የሚችልበት እድሉ አነስተኛ ነው:: በመሆኑም አለመግባባትን እየፈታን ሰላማዊ ህይወትን በግላችን፣ በቤታችን፣ በሥራቦታ ወዘተ መኖርን ስናስብ ልናስብ የሚገባው እውነት ፍላጎቶቹን የማቀራረብን ጥቅም ነው::

የዛሬ 28 አመት በሩዋንዳ ውስጥ በእያንዳንዱ ቀን ከአስር ሺ በላይ ሰዎች ይጨፈጨፉ ነበር:: ብሔርን ማእከል አድርጎ የተነሳው ግጭት ለሦስት ወራት ያህል ቀጥሎ ከአንድ ሚሊዮን የማያንሱ ሰዎችን ሕይወት ቀጥፎ ምድሪቱ በደም ጎርፍ ተመታ ነበር:: ከአንድ ሚሊዮን ሰዎች እንደ አንዱ ከሞት ጋር ፊት ለፊት እንደተገናኘ ሰው ሆነን ራሳችንን ስንመለከት ለሰላም የሚሰጥ ዋጋ ያለውን ቦታ እንረዳለን:: በጭንቅ ሰዓት የሰላም ትርጉሙ ከፍተኛ መሆኑን እንገነዘባለን:: ሰውን በግፍ ከመጨፍጨፍ መለስ በጥሞና ፍላጎቶችን ማቀራረብ ላይ መስራት ቅድሚያ ቢሰጠው ኖሮ በታሪክ ውስጥ አንካሳ ታሪክን ጥሎ ማለፍ ባልሆነ ነበር::

በመግቢያችን ላይ ያነሳነው የፍርድ ቤቶች መኖር ለሰላም ያላቸው አስተዋጽኦ ቀላል ባይሆንም ፍትህን ለማግኘት ውድ በሆነበት ሁኔታ፤ የፍትህ ስርዓቱም አሸናፊና ተሸናፊ ብሎ በሁለት ጎራ ከፍሎ መዝገቡ በሚዘጋበት ሁኔታ፤ ፍላጎትን አቀራርቦ ሁሉም አሸናፊ የሚሆንበት መንገድ ላይ መገኘትን አዳጋች ሊያደርገው ይችላል:: የፍላጎቶች ልዩነት በሰፋ ቁጥር ግጭት አይቀሬ መሆኑን ስንረዳ አንዳችን በሌላችን ጫማ ውስጥ የማሰብን የወርቃማውን ህግ መሰረታዊነት እንረዳለን::

### አንዳችን በሌላችን ጫማ

"ጎረቤቴ የሚለቀው ፍሳሽ ለጤናዬ እክል ሆነብኝ"፤ "ጎረቤቴ የሚሰማው ድምጽ ሰላም ነሳኝ"፣ "ከጎረቤቴ የሚመጣው ጭስ አላስተኛ አለኝ" ወዘተ ብለው ሰዎች ፍትህን ፍለጋ ወደሚመለከተው አካል ከመሄዳቸው በፊት በሌላኛው ጫማ ውስጥ ቢኬድ ጥሩ ይሆን ነበር::

አንዳችን በሌላችን ጫማ ሆነን ማሰብ በተሳነን ጊዜ ተጎድቼያለሁ የሚለው ሰው አለኝ በሚለው መንገድ ፍትህን ይፈልጋል ወይንም የሚፈልገውን ለማድረግ ጥረት ያደርጋል:: አንዳችን በሌላችን ጫማ ሆነን ስንገኝ የሰላም አየር አካባቢያችንን ይከበዋል:: በተፈጥሮ እናት ለልጆቹ አንዳች ጥቅምን ፈልጋ ብዙ እርቀት ትሄዳለች:: ሰው ሁሉ ይህን እርስ በእርሱ ማድረግ ባይችል እንኳን በሞራል ህግ ለእኔ እንዲሆን የምፈልገውን ለሌላው፤ በእኔ ላይ እንዲሆን የማልፈልገውን በሌላው ላይ ወዘተ ብለን ማሰብ ይኖርብናል::

ዋልት ዴዝኒ "አንድን ነገር ለመጀመር ዋናው ነገር ማውራትን አቁሞ የተግባር እርምጃን ማድረግ ነው" እንደሚለው አንዳችን በሌላችን ጫማን ለመተግበር የሚፈልገው የተግባር እርምጃን ብቻ ነው:: ግጭትን ለመፍታት በመሄድ ውስጥ አንዳችን በሌላችን ጫማ ውስጥ መሆናችን ጥቅሙ ለሁሉም ነው:: ይህም ሁሉ ሆኖ በሰዎች መካከል በተለያየ ምክንያት ግጭት ሊፈጠር ይችላል:: በተለይ ከእኛ የሚጠበቀውን ተወጥተን ነገር ግን አይቀሬ የሆነ ግጭት ውስጥ ስንገባ መፍትሔው አንዳችን በሌላችን ላይ ቢላ መሳል ሳይሆን ተነጋግሮ በይቅርታ ፋይሉን መዝጋት ነው::

ይቅርታ አይቅር ብለን የምናነሳው ነጥብም የዚህ ጽሑፍ ማጠንጠኛ የሆነበት ምክንያት በይቅርታ ውስጥ ያለውን መንፈሳዊም ሆነ ሥነ-ልቦናዊ ጥቅምን በማሰብ ነው:: ለእኛ እንዲሆን የምንፈልገው ስለሆነ:: የሰው ልጅ የጋራ ኑሮ ያለ ይቅርታ ትርጉም ሊኖረው ስለማይችል፤ ይቅርታ አይቅር ብለን ንባባችንን እንቀጥል::

### ይቅርታ አይቅር

ኔልሰን ማንዴላ የሕይወት ታላቁ ክብር "ፈጽሞ አለመውደቅ ሳይሆን በወደቅን ቁጥር መነሳት መቻል ነው" ማለቱ ከመውደቅ መነሳት ዋና በመሆኑ ነው:: ይቅርታ ደግሞ ከውድቀት የመነሻ አንዱ ነገር ነው:: ሩዋንዳን ያለፉት 28 አመታት የሚሊዮን ዜጎቿን ሕይወት የቀጠፈውን ታሪክ በየአመቱ እያስታወሰች ምን ሆነን ነበር ትላለች:: ምን ሆነን ነበር የሚለው ጥያቄ ያኔ የመጀመሪያው ቢላ ከሚሳልበት ቅጽበት በፊት ቢሆን ኖሮ ምንኛ ጥሩ በሆነ ነበር:: የሆነው ከሆነ በኋላ ግን ችግሩን በይቅርታ ለመፍታት የሄደችበት መንገድ አስተማሪ ነው::

በደቡብ አፍሪካም ታሪክ ውስጥ ለይቅርታ የተሰጠው ቦታ አስተማሪነቱ ብዙ ነው:: የከበደውን ቁስል ግን በይቅርታ በማለፍ አዲስን ምእራፍ በስምምነት የመከፈት ምእራፍ:: ይቅርታ ያለውን ትልቅ ቦታ የምንረዳው የግድ ጉዳዩ በአገር አቀፍ ደረጃ ባለ ጉዳይ ስለሆነ አይደለም:: ዛሬ ብዙሪያችን ካሉ ሰዎች ጋር ያለንን ሰላም መሆን መርምረን የይቅርታ ጉዞችንን መፈተሽ ይኖርብናል:: በመነጋገር እና ትላንትናን በእውነተኛ ይቅርታ በመዝጋት ወደ ውጤት ነገሮችን



ማምጣት ይቻላል:: ይቅርታ አይቅርም የምንለው ለዚህ ነው::

የይቅርታ በቦታው መገኘት እረፍቱ ለበዳይም ለተበዳይም መሆኑን ስንረዳ የሕይወታችን መገለጫ እናደርገዋለን:: በዳይ ጥፋቱን እንዲረዳ የሚያደርገው፤ ተበዳይም በሞራል ልእልና ውስጥ ገብቶ ነገሮን ትቶ የሰላምን ኑሮ እንዲኖር የሚረዳው ነው:: ግጭት የማይኖርበትን ጊዜ ምድር ላይ ከማለም ግጭት እንዳይፈጠርና ከተፈጠረም እንዴት ሊፈታ እንደሚገባ ማሰቡ የተሻለው ነው:: የተሻለውን መንገድ በእርግጥም የተሻለ መሆኑን የሚያስረዳው የይቅርታ አቅም ነው::

መጽሐፍ ቅዱስ ለይቅርታ የሚሰጠውን ቦታ ከፍ አድርጎ ማስቀመጡን የምንረዳው ተበዳይ ወደ በደለው ሰው ሄዶ ይቅርታን እንዲያደርግ የሚጠይቅ በመሆኑ ነው:: በዳይ ወደ ተበዳይ ወይንስ ተበዳይ ወደ በዳይ የሚለውን አንባቢ በጥንቃቄ እንዲያስተውል እጠይቃለሁ:: ምላሹ ተበዳይ ወደ በዳይ የሚል ነው:: በዳይ ወደ ተበዳይ መጥቶ የሚጠይቀውን ይቅርታ ሁላችንም የምናውቀው ቢሆንም በተቃራኒው ሲሆን ግን ግርታን የሚፈጥር ሊሆን ይችላል:: ይህ የሚያሳየው ለይቅርታ ሊሰጥ የሚገባው ቦታ ከፍተኛ መሆኑን ነው::

እያንዳንዳችን ለይቅርታ ያለንን ቦታ እንፈትሽ? በትዳር ሕይወታችን ውስጥ ይቅርታ ምን ያህል እየተጠቀምንበት ነው? በሥራ ቦታስ? በምንሳተፍበት የትኛውም አይነት ማህበራዊ መስተጋብርስ? ምናልባትም ከራሳችንስ ጋርስ? አንዳንዴ ግጭቱ ከራሳችን ጋር ይሆንና ለራሳችን ይቅርታን ማድረግ ተስኖን ራሳችንን ለመቅጣት የምንሄድበት መንገድ አለ:: ራሳችንን በመጣል የምንሄድበት መንገድ ራስን የመቅጫ መንገድ ሆኖ ሊታይ ይችላል::

ይቅርታ አይቅር ብለን ከራሳችን ተነስተን ወደ ውጭ ወጥተን ስንሄድ የምናየው የሰላም አየር ያልተለመደ ሆኖ እናገኘዋለን:: በሰላም ውስጥ፤ ነገሮች መስመር በያዙበት ሁኔታ ያልተፈታ ችግር በግጭት ውስጥ ሊፈታ የመቻል እድሉ አነስተኛ ነው:: ስለሆነም በጭንቅ ውስጥ ላለሽ አገሬ ይቅርታ አይቅር እላለሁ:: ለአንባቢው ለአንዱ ሰው:: ደግሞሙ ለሁሉም:: ፍላጎትን በማቀራረብ፣ አንዱ በአንዱ ጫማ ውስጥ በመሆን ይቅርታን ይዘን ወደ በደለን በመሄድ::

ይህ በሆነ ጊዜ ጎልማሶቹ ስራቸው ላይ የሚያተኩሩ፤ አዛውንቷን ለሽምግልና እንጂ ለማንገላታት ምክንያት የማይሆን፤ ታማሚዎች በአግባቡ አስታማሚ የሚያገኙ መድኃኒታቸውን በጊዜ የሚወስዱበት፤ ልጆች በሰላም ተጫውተው በሰላም ተጋጭተውና ታርቀው ተፈጥሮ ስራዋን በአግባቡ የምትሰራበት ይሆናል:: ይህ እንዲሆን ጣታችንን ወደ ሌላው ከመቀሰር ወደራሳችን አድርገን ይቅርታ አይቅር ብለን እንነሳ:: ታሪካችን ሁሉ እንዲህ እየሆነ ሌላ ምን ልንል እንችላለን?

ኢኮኖሚ

# ስኬት

# ከ120 ብር ደመወዝ ተከፋይነት ወደ ሚሊየነርነት

**ፍሬሕይወት አወቀ**

ኢትዮጵያ ያልተነካ በርካታና እምቅ የተፈጥሮ ሀብት ያላት ለመሆኑ መረጃዎች ያመለክታሉ:: ያላትን የሰው ኃይል እና የተፈጥሮ ሀብት መጠቀም አለመቻሏ ድህነቷን ካባባሱባት ምክንያቶች መካከል አንዱ እንደሆነ ይታመናል:: በሁሉም አቅጣጫ ገና ብዙ ያልተነካና ያልተሠራበት ዘርፍ ስለመኖሩም እንዲሁ:: ታድያ አገሪቷ ያላትን የተፈጥሮ ሀብት ሰፊ ቁጥር ካለው የሰው ኃይል ጋር በማቀናጀት ለውጥ ለማምጣትና ለበርካቶች የሥራ ዕድል በመፍጠር የተጠናወታትን ድህነት ከሥሩ መንግላ ማውጣት እንድትችል መንግሥት የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን ሲያደርግ ይስተዋላል::

ለአብነትም አገሪቷ ያላትን እምቅ ሀብት አውጥታ መጠቀም እንድትችል ትልቅ አስተዋጽኦ ያላቸውን ወጣቶች በተለያዩ የሥራ ዘርፎች ማሰማራት መቻል አንዱ ነው:: ለዚህም መንግሥት ወጣቶችን በየአካባቢያቸው በማደራጀት በፈለጉት የሙያ ዘርፍ ተሰማርተው መሥራት እንዲችሉ ሁኔታዎችን ሲያመቻች መቆየቱ ይታወቃል:: በተለይም አምራች ኢንተርፕራይዞችን በማደራጀት የማምረቻና የመሸጫ ቦታ እንዲሁም የሥራ ማስኬጃ የፋይናንስ ብድር እና ሌሎችንም ድጋፎች በማድረግ ወጣቱ የሥራ ዕድል እንዲፈጠርለት ሲያደርግ ቆይቷል:: መንግሥት ያደረገውን ድጋፍ በመጠቀም እራሳቸውንና አካባቢያቸውን መለወጥ የቻሉ እንዳሉ ሁሉ በርካቶችም መንግሥት ካስቀመጠው አቅጣጫ ውጪ ሆነው ለኪሳራ የተዳረጉ አልታጡም::

በዛሬው የ‹‹ ስኬት ›› አምዳችን እንግዳ ያደረግነው ያለውን ዕውቀት ተጠቅሞ ከመንግሥት ባገኘው የመሥሪያ ቦታ በዶሮ እርባታ ውጤታማ ስለሆነው ግለሰብ ነው:: ግለሰቡ ተወልዶ ባደገበት ቢሾፍቱ ከተማ ውስጥ የአስረኛ ክፍል ትምህርቱን አጠናቅቋል:: ከትምህርት በኋላም ሥራ መሥራት እንዳለበት በማመን ቢሾፍቱ በሚገኝ አንድ የዶሮ እርባታ ድርጅት ውስጥ ከመኪና ረዳትነት አንስቶ ሾፌር ሆኖ አገልግሏል:: አለፍ ሲልም የመኪና ሾፌርና ረዳት ሆኖ ባገለገለበት ትልቅ የዶሮ እርባታ ድርጅት ውስጥ ለሥራ ካለው ፍላጎትና ጉጉት የተነሳ በዶሮ እርባታ ዘርፉ ውስጥም ቆይቷል::

ቢሾፍቱ ከተማ ሥራን ‹‹ሀ›› ብሎ በመኪና ረዳትነት የጀመረው እንግዳችን አቶ ሰለሞን ጌታቸው ዛሬ ላይ ታዋቂ ለሆኑ ሆቴሎችና ሬስቶራንቶች እንዲሁም ሱፐርማርኬቶች የዶሮ ሥጋ አቅራቢ ከመሆኑ አስቀድሞ የ120 ብር ደመወዝተኛ እንደነበር አስታውሶናል:: በ120 ብር ደመወዝም መንጃ ፈቃድ አውጥቶ ወደ መኪና ማሽከርከር ማደግ ችሏል:: በዚህም የፍሪጅ መኪና ከቢሾፍቱ ወደ አዲስ አበባ ተበልቶ የተዘጋጀ የዶሮ ሥጋና እንቁላል ጭምር እያጓጓዘ ለደንበኞች ተደራሽ የማድረግ ሥራ ሰርቷል:: ይህም አካባቢንና ሰዎችን የመተዋወቅ እድል ፈጥሮለታል:: እንዲህ እንዲህ እያለ ለስምንት ዓመታት በድርጅቱ ሲቆይ ካገኘው የሥራ ልምድና ዕውቀት በበለጠ አሁን ለደረሰበት ደረጃ ትልቅ አቅም የሆነው ደንበኞችን ማግኘት መቻሉ እንደሆነ ይናገራል::

ተቀጥሮ ሲሰራበት በነበረው የዶሮ እርባታ ድርጅት ውስጥ ያገኘውን እውቀት ተጠቅሞ የግሉን የዶሮ እርባታ ሲጀምር የገበያ ችግር ያልገጠመው አቶ ሰለሞን መነሻ ካፒታል 15 ሺ ብር አስመዝግቦ እንደ ጀመረ ያስታውሳል:: በወቅቱ አምስት መቶ ጫጩቶችን በመግዛት ዘርፉን ሲቀላቀል አንድ ኪሎ ዶሮ 62 ብር ሂሳብ በመግዛት ነበር:: ለአምስት ሺ ጫጩቶችም 40 ሺ ብር አካባቢ ወጪ ያደረገው መሆኑን ያስታወሰው አቶ ጌታቸው፤ ካፒታሉን ያገኘውም ከጓደኞቹና ከቤተሰቡ በብድር መልክ ነበር::

‹‹የትምህርት ደረጃዬ 10ኛ ክፍል በመሆኑ ይህን ብሰራ ያን ብሰራ ብዬ ማማረጥ አልችልም›› የሚለው አቶ ሰለሞን ፤ ነገር ግን ከመቀጠር ይልቅ በግል መሥራት አዋጭ እንደሆነ ለማወቅና ለመረዳት ጊዜ አልወሰደበትምና በቀላሉ ዘርፉን መቀላቀል ችሏል::



አቶ ሰለሞን ጌታቸው

ሥራው አዋጭ ለመሆኑም በድርጅቱ የነበረው ቆይታ ከበቂ በላይ ዕድል የሰጠው በመሆኑ ወደ ሥራው ሲገባ ለአዋጭነቱ ሙሉ ዕምነት ነበረው:: በተለይም ተቀጥሮ በሚሰራበት ወቅት የሚያውቃቸውን ደንበኞች ቀዳሚ የገበያው መዳረሻ ማድረግ መቻሉ በአጭር ጊዜ ውጤታማ እንዲሆን አስችሎታል::፡

ከመነሻ ካፒታሉ በላይ ለበርካታ ሥራ ፈጣሪ ወጣቶች ፈተና የሆነው የማምረቻ ቦታ ጥያቄውን መንግሥት የመለሰለት ሲሆን፤ በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ በመደራጀት የማምረቻ ሼድ አግኝቷል:: ከመንግሥት ባገኘው ሼድ ውስጥም የዶሮዎቹን ምግብ በአግባቡ መግቦና ጤናቸውን ጠብቆ ለ45 ቀናት በማቆየት የሥጋ ዶሮን እያረባ ለገበያ ማቅረብ ዋና ሥራው ሆነ:: በዋናነት የሥጋ ዶሮን በማርባት አዲስ አበባ ከተማ ለሚገኙ የተለያዩ ሆቴሎችና ሬስቶራንቶች እንዲሁም ሱፐርማርኬቶች ያቀርባል::

ዶሮዎቹ አስፈላጊው እንክብካቤ ከተደረገላቸውና ጤናቸው ተጠብቆ ምግባቸውን በአግባቡ ካገኙ የሚፈለገውን ውጤት ማግኘትና ተጠቃሚ መሆን እንደሚቻል ያጫወተን አቶ ሰለሞን ጌታቸው፤ የሚያረባቸው የሥጋ ዶሮዎች ለገበያ የሚያቀርባቸው በእርባታ ቦታው ላይ ታርደውና ተበልተው እንደሆነም ይናገራል:: ደንበኞች በሚፈልጉት መንገድ የሚዘጋጀው የዶሮ ሥጋ ሙሉ ዶሮውን ለሚፈልግ ሙሉ ዶሮው የሚዘጋጅለት ሲሆን የዶሮዎቹን የተለያየ ክፍል የሚፈልገውም የፈለገውን አካል በማዘጋጀት ያቀርባል:: የዶሮ ሥጋ በብዛት የሚጠቀሙት በርገር ቤቶች እንደመሆናቸው አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ለሚገኙት ታዋቂ በርገር ቤቶች ያቀርባል::

ለዶሮ እርባታ ሥራ የፍሪጅ መኪና ወሳኝ ነው የሚለው አቶ ሰለሞን ጌታቸው፤ ካለፍሪጅ መኪና የዶሮ እርባታ የማይታሰብ ሥራ እንደሆነም ይናገራል:: ታድያ ቀደም ሲል ይህን ለሥራው ወሳኝ የሆነው መኪና ከግለሰቦች ተከራይቶ ሲሰራ ከቆየ በኋላ በአሁኑ ወቅት ግን የግሉን ባለፍሪጅ መኪና መግዛት ችሏል:: ከጊዜ ወደ ጊዜ የማምረት አቅሙን እያሳደገ በመምጣትም በአሁኑ ወቅት በሳምንት እስከ ሶስት ሺ የሥጋ ዶሮዎችን አምርቶ፣ አርዶና በልቶ ለደንበኞቹ ያከፋፍላል:: ከዚህም በተጨማሪም አዲስ አበባ ወሎ ሰፈር አካባቢ በሚገኘው የመሸጫ ሱቅ ከፍቶ የሥጋ ዶሮዎቹ ይሸጣሉ::

በዋናነት ከተሰማራበት ሥራ በተጨማሪ ወተትና የወተት ተዋጽኦዎችን በመሸጫ ሱቅ ያቀርባል። በአማራ ክልል ጎጃም አካባቢ የሚገኙ አርብቶ አደሮች የሚያመርቱትን ወተትና የወተት ተዋጽኦ ለገበያ ማቅረብ እንዲችሉ ዕድል ፈጥሮላቸዋል::

በከፍተኛ የዶሮ እርባታ ድርጅት ውስጥ በመሥራቱ በዘርፉ የመሰማራት ዕድሉን አስፍቶ ዛሬ ላይ ከግለሰቦች ጀምሮ ትላልቅ ለሆኑ ድርጅቶች ጭምር ምርቱን በትስስር ለገበያ የሚያቀርበው አቶ ሰለሞን ጌታቸው፤ በዘርፉ 10 ለሚደርሱ ሰዎች የሥራ ዕድል መፍጠር ችሏል:: በቋሚነት ከፈጠረው የሥራ ዕድል በተጨማሪ ጫጩቶችን በሚረከብበት ጊዜም ጊዜያዊ ሠራተኞችን ይቀጥራል::

ዘርፉን ፈታኝ ከሚያደርጉት ተግዳሮቶች መካከል ጫጩቶቹ ከውጭ አገር በውጭ ምንዛሪ የሚገቡ በመሆናቸው በስፋት ለማምረት አስቸጋሪ እንደሆነና በተለይም ጫጩቶቹ በተወሰኑ አስመጪዎች እጅ መሆኑ ፈታኝ ያደርገዋል:: ምንም እንኳን በዘርፉ ከፍተኛ ዕውቀትና ልምድ ያካበተ ቢሆንም ቅሉ ጫጩቶቹን ከውጭ አገር ለማስገባት ከፍተኛ ካፒታል ሊያውም የውጭ ምንዛሪ መጠየቁ ሥራውን በሚፈልገው መጠን ማስኬድ እንዳላስቻለው አቶ ጌታቸው ይናገራል::

ከውጭ የሚገቡት እንቁላል ጣይ ጫጩቶቹ ሲገቡ ከአንድ ጊዜ በላይ እንዳይባዙ ተደርገው መሆኑ የዘርፉ ትልቅ ችግር ነው:: እንቁላል ጣይ ዶሮዎቹ ከውጭ ሲገቡ አንድ እንቁላል አንድ ጊዜ ብቻ ከጣለች በኋላ በቀጥታ ወደ ሥጋነት ተሸጋግራ አገልግሎቷን ታበቃለች:: ዋጋውም ቢሆን አንድ ጫጩት በአንድ መቶ ብር የሚገዛ ሲሆን ጫጩቶቹ ይደጉም አይደጉም አይታወቅም። እንዲሁም ከዘርፉ ችግሮች አንደኛው ከውጭ የሚገቡት ዶሮዎች የሚራቡ አለመሆናቸው እንደሆነና ለዚህም መንግሥት በቻለው አቅም ድጋፍ ቢያደርግ በዘርፉ ያለውን ችግር ማቃለል የሚቻል መሆኑን ይናገራል ::

ጫጩቶቹ ከፍተኛ ጥንቃቄን የሚፈልጉ ሲሆን፤ ከምግባቸው ጀምሮ ህክምናቸውንና አጠቃላይ የሚያስፈልጋቸውን እንክብካቤ በማድረግ በ45 ቀናት ውስጥ ዶሮዎቹ ለሥጋ ይደርሳሉ በማለት ከአበሻ ዶሮዎች ጋር ሰፊ ልዩነት ያላቸው መሆኑን የገለጸው አቶ ሰለሞን ጌታቸው፤ አንድ የሀበሻ ዶሮን ለሥጋ ለማድረስ ከሶስት እስከ አራት ወራት የሚቆይ በመሆኑ የሀበሻ ዶሮዎችን ማርባት አዋጭ አለመሆኑን በማስረዳት በአጠቃላይ የሥጋ ዶሮ በአገር ውስጥ ማርባት የማይቻልና ከውጭ የሚገባ መሆኑን ተናግሯል::

በሥራ ዓለም ውስጥ በቀዳሚነት የተዋወቀውን የዶሮ እርባታ ተቀላቅሎ እራሱንና ቤተሰቡን መለወጥ የቻለው አቶ ሰለሞን ጌታቸው፤ በ40 ሺ ብር የጀመረው ሥራ በአሁኑ ወቅት ከመኪናውና ከተለያዩ ንብረቶች ውጭ በጥሬ ገንዘብ ብቻ ስምንት ሚሊዮን ብር ካፒታል መድረስ ችሏል:: መንግሥት ዜጎች በጥቃቅንና አነስተኛ ተደራጅተው በተለያየ የሥራ ዘርፍ መሰማራት እንዲችሉ በሰጠው እድል ከተደራጁ ኢንተርፕራይዞች መካከል አንዱ የሆነው አቶ ሰለሞን ጌታቸው፤ መንግሥት ባስቀመጠው አሰራር መሰረት በአምስት ዓመታት ውስጥ ሥራውን አሳልጦ፣ ሀብት አፍርቶና ውጤታማ መሆን በመቻሉ ከጥቃቅንና አነስተኛ ወደ መካከለኛ ኢንተርፕራይዝ ሽግግር ማድረግ ችሏል::

መንግሥት ከጥቃቅንና አነስተኛ ወደ መካከለኛ ያሸጋገራቸውን ኢንተርፕራይዞች በቀጣይ የማምረቻ ቦታ ለመስጠት ቃል የገባ መሆኑን የጠቀሰው አቶ ሰለሞን ጌታቸው፤ መንግሥት በገባው ቃል መሰረት መሬት ማቅረብ ከቻለ በቀጣይ የሥጋ ዶሮዎችን በስፋት ለማቅረብ ዝግጁ መሆኑን በመግለጽ በአሁኑ ወቅት ያለውን ሙሉ አቅም አሟጦ እየተጠቀመ ሲሆን መንግሥት ደግሞ ባለው አቅም ላይ ሌላ አቅም መፍጠር ከቻለ የበለጠ አምርቶ የሥራ ዕድል በመፍጠር ተጠቃሚ መሆን እንደሚቻል አስረድቷል::

በቅርቡም የሚከበሩ በዓላትን አስመልክቶ አጠቃላይ ለበዓሉ የሚያስፈልጉ የዶሮ ሥጋ እንዲሁም ወተትና የወተት ተዋጽኦዎችን በስፋት ለገበያ ለማቅረብ ዝግጁ መሆኑን የገለጸው አቶ ሰለሞን ጌታቸው፤ ደንበኞቹ በፈለጉት አይነት በማዘጋጀት ያስረክባል:: ሙሉውን ዶሮ የሚፈልግ እንዳለ ሁሉ እግር፣ መላላጫ፣ ታፋና ሌሎችንም እንደ ደንበኛው ፍላጎት የሚሸጥ ሲሆን የዶሮ እግር ማለትም ጥፍሮቹን ቻይናውያን አብዝተው የሚፈልጉት እንደሆነም አጫውቶናል::

ከሀበሻ ዶሮዎች ይልቅ የበለጠ ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚያስፈልጋቸው የውጭ ዶሮዎች እንደሆኑ የሚናገረው አቶ ሰለሞን ጌታቸው፤ በዘርፉ ረዘም ላለ ጊዜ በመቆየቱ በሽታ ከያዛቸው እንደሚሞቱና ኪሳራ ውስጥ እንደሚገባ ጠንቅቆ በማወቁ አስፈላጊውን እንክብካቤ ሁሉ ያደርጋል:: በመሆኑም ከ2008 ዓ.ም ጀምሮ በተሰማራበት የዶሮ እርባታ እስካሁን ይህ ነው የሚባል ችግር ያልገጠመው ቢሆንም ጫጩቶቹ በውስን ሰዎች እጅ ውስጥ ብቻ መሆናቸው ለዘርፉ ዕድገት ማነቆ እንደሆነ ተናግሯል::

በአገሪቱ የዶሮ እርባታውን ጨምሮ በተለያየ ዘርፍ የተሰማሩ ኢንተርፕራይዞች ገበያን ከማረጋጋት ባለፈ በአገር ኢኮኖሚ ላይ የጎላ ድርሻ ያላቸው በመሆኑ መንግሥት የጀመረውን የማበረታታትና የመደገፍ ሥራው አጠናክሮ ቢቀጥልና ተኪ ምርቶችን በስፋት መጠቀም መልካም ነው:: በማለት አበቃን::

ኢኮኖሚ

# መሠረተ ልማት

# ማምረት የናፈቀው የኦሞ ኩራዝ የስኳር ልማት ፕሮጀክቶች

መላኩ ኤርሴ

የስኳር ልማት ኢንዱስትሪ በሀገራችን ከግምሽ ምዕተ ዓመት በላይ ያስቆጠረ አንጋፋ ኢንዱስትሪ ነው። ሆኖም ኢንዱስትሪው እድሜውን በሚመጥነው ልክ እድገት አላሳየም ። ኢንዱስትሪው በሚፈለገው ፍጥነት ባለማደጉም የስኳር ምርት እጥረት በሀገር ውስጥ እንዲከሰት አንዱ ምክንያት ሆኗል ። ዘርፉ በሚፈለገው ልክ ካለማደጉም ባሻገር በአፍሪካ በህዝብ ቁጥር ሁለተኛ በሆነችው ሀገራችን እየተመዘገበ ያለው ከፍተኛ የህዝብ ቁጥር እድገት እና ስኳርን በግብዓትነት የሚጠቀሙ ኢንዱስትሪዎች ቁጥር መበራከት የሀገሪቱ የስኳር ፍላጎት ከጊዜ ወደ ጊዜ እንዲጨምር አስገድዷል።

የአቅርቦት እና ፍላጎት አለመጣጣም ከጊዜ ወደ ጊዜ ችግር እየሆነ መጥቷል ። ችግሩን ለመቅረፍ መንግሥት ከዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አንድ ጀምሮ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ ከሰራባቸው ዘርፎች አንዱ የስኳር ኢንዱስትሪ ልማት ነው ። ዕቅዱ ከተጀመረ ወዲህ የሀገሪቱ የስኳር ኢንዱስትሪ ለማስፋፋትና ለማዘመን ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶ ሲሰራ ቆይቷል። ከታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ቀጥሎ ከፍተኛ መጠን ያለው ገንዘብ ወጪ የተደረገበት ዘርፍ ነው።


በዚሁ መሰረት በሀገሪቱ በተለያዩ አካባቢዎች ስኳር ልማት ፕሮጀክቶች ግንባታ ተካሂዷል ። አንዳንዶቹ ተጠናቀው አገልግሎት መስጠት የጀመሩ ሲሆን አንዳንድ ፕሮጀክቶች በተለያዩ ምክንያቶች መጓተት ታይቶባቸዋል ። በአጠቃላይ ሲታይ በስኳር ልማት ዘርፍ ለማሳካት የታቀደውን ግብ ማሳካት አልተቻለም ። በተለይም የኩራዝ ስኳር ልማት ፕሮጀክቶች ለማሳካት የተያዘውን ግብ ካላሳካቱ ፕሮጀክቶች አንዱ ነው ።

የሀገሪቱን የስኳር ፍላጎት ከማሟላት አልፎ ለሀገሪቱ ገቢ ያስገኛል ተብሎ ግብ ተቀምጦለት ነበር ። ከዚያ ባሻገር የሥራ እድል በመፍጠር እና በአካባቢው የሚኖረውን የአርብቶ አደር ማህበረሰብ ህይወት ለመለወጥ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል ተብሎ ተስፋ ተጥሎበት የነበረ ቢሆንም የተቀመጠለትን ግብ ሳይመታ ቀርቷል ።

ሳይጠናቀቁ የቆዩት ላይ መንግሥት ጥናት በማካሄድ ግንባታቸው ተጠናቆ ምርት ወደ መስጠት እንዲሸጋገሩ ለማስቻል ጥረቶች ተደርገዋል ። የለውጥ አመራር ወደ አመራር ከመጣበት ማግስት ጀምሮ የፕሮጀክቶችን ችግሮች ለመለየትና ለችግሮቹ መፍትሄ ለመስጠት ጥረት ተደርጓል ። ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በተወሰዱት እርምጃዎች አንዳንድ የስኳር ፕሮጀክቶች ተጠናቀው ወደ ሥራ ገብተዋል ። ከረጅም ጊዜ መጓተት በኋላ በመንግሥት በተወሰዱት ቆራጥ እርምጃዎች ወደ ምርት ከተሸጋገሩት መካከል የበለስ ስኳር ልማት ቁጥር አንድ ፕሮጀክት እና የኦሞ ኩራዝ ሁለት እና ሶስት ፕሮጀክቶች ተጠቃሽ ናቸው ።

ሆኖም እስካሁን ተጠናቀው ምርት ወደ ማምረት ያልገቡ የስኳር ልማት ፕሮጀክቶችም አሉ፤ ከእነዚህም መካከል ፕሮጀክቶች በደቡብ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል በደቡብ ኦሞ ዞን የሚገኙ የስኳር ልማት ፕሮጀክቶች ተጠቃሽ ነው ። እነዚህ የስኳር ልማት ፕሮጀክቶች የሀገሪቱን ስኳር እጥረት ለመቅረፍ እንዲሁም ሥራ እድል በመፍጠር ረገድ ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ ተብሎ ተስፋ የተጣለባቸው ነበሩ ። ከነዚህ ፋብሪካዎች መካከል በዞኑ በሰለማጎ ወረዳ የሚገኘው ኦሞ ኩራዝ ስኳር ልማት ፕሮጀክት አንድ በቀን 24 ሺህ ቶን አገዳ እንዲፈጭ ታቅዶ ነው ወደ ግንባታው የተገባው።

ግንባታውን ብረታ ብረትና ኢንጂነርንግ ኮርፖሬሽን (ሜቴክ) ነበር ሲያከናውን የነበረው። ሜቴክ የፋብሪካውን ግንባታ 84 በመቶ ካደረሰ በኋላ ግንባታው ቆሟል ። ግንባታው የቆመው ደግሞ የፋብሪካውን ወሳኝ እና ቴክኒካል የሆነውን ክፍል ቡድን መገንባት ባለመቻሉ ውሉ መቋረጡን ጠቁሟል። ሆኖም ውሉ ከተቋረጠ ወዲህ ምንም አለመሰራቱን በፌዴራል የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የደቡብ ኦሞ



ፕሮጀክቱ የሚገነባበት ቦታ ርቀት እና የትራንስፖርት መሠረተ ልማት እጦት ግንባታው በተያዘለት ጊዜ እንዳይጠናቀቅ አንዱ ምክንያት ሆኗል ፤

አካባቢ ተወካይ በየካቲት 15 /2014 ዓ.ም በተካሄደው ሶስተኛው አስቸኳይ የፓርላማ ስብሰባ ላይ ለጠቅላይ ሚኒስትር አብይ አህመድ የኦሞ ኩራዝ አንድ እና አምስት ስኳር ፕሮጀክቶቹን ለማጠናቀቅ የተያዘውን እቅድ አስመልክቶ ጥያቄ ባነሱበት ወቅት ገልጸዋል ።

ፕሮጀክቱ በተያዘላቸው ጊዜ ካለመጠናቀቁም ባሻገር መንግሥት የፕሮጀክቱን ችግር በጥናት ከለየ በኋላ ራሱ የፕሮጀክቱ ግንባታ ሊካሄድ አለመቻሉ እና የአካባቢው ህዝብና ሀገሪቱ ከፕሮጀክቱ ማግኘት ያለባቸውን ጥቅም ማግኘት አለመቻላቸው እንደ ሀገር ኪሳራ መሆኑን ነው ያነሱት።

ሌላኛው በደቡብ ኦሞ ዞን በኛንጋቶም ወረዳ የኦሞ ስኳር ፕሮጀክት ቁጥር አምስት የግንባታ ሥራ JJIEC በተሰኘ የቻይና ኩባንያ ከህዳር ወር 2009 ዓ.ም ጀምሮ ሲከናወን የቆየ ሲሆን በቀን 24 ሺህ አገዳ ይፈጫል ተብሎ ታቅዶ ነው ሲገነባ የነበረው። ኩባንያው የፋብሪካውን ግንባታ 25 በመቶ ብቻ ሰርቶ ግልጽ ባልሆነ ምክንያት ቆሞ እንደሚገኝና ይህም ሀገርና የአካባቢውን ህዝብ ከፕሮጀክቶቹ ማግኘት ያለበትን ጥቅም ማግኘት እንዳይችል ማድረጉን የአካባቢው የህዝብ እንደራሴ በቅርቡ በፓርላማ ተናግረዋል ።

የኦሞ ኩራዝ ቁጥር አምስት የዋና ፕሮጀክቱ ግንባታው ከመቆሙ ባሻገር የፕሮጀክት የመስኖ ካናል ግንባታው የፌዴራል ውሃ ሥራዎች ግንባታ ድርጅት ጀምሮ የነበረ ሲሆን የመስኖ ካናል ግንባታም ቆሟል። የኦሞ ኩራዝ አንድና አምስት እንዲሁም የመስኖ ካናል ባለመጠናቀቁ ፕሮጀክቱን ተከትሎ የሰፈሩ የኛንጋቶችምና የሰለማጎ ወረዳዎች ነዋሪዎች የቅሬታ ምንጭ እየሆነ መምጣቱን የህዝብ እንድራሴው ጠቁመዋል ።

የነዚህ ፕሮጀክቶች መጠናቀቅ በአንድ በኩል እየጨመረ ያለውን የሀገሪቱን የስኳር ፍላጎት ለማሟላት ፋይዳው ከፍ ያለ ሲሆን በሌላ በኩል ለዜጎች የሥራ እድል የሚፈጥር ስለሆነ ትኩረት ሊሰጣቸው እንደሚገባ ጠቁመዋል።

ከአካባቢው ህዝብ ተወካይ ለተነሳው ጥያቄ ጠቅላይ ሚኒስትር አብይ አህመድ በወቅቱ እንደተናገሩት፤ በርካታ የስኳር ፋብሪካዎች በተመሳሳይ ጊዜ መጀመሩ ፕሮጀክቶቹ በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ እንዳይጠናቀቁ ምክንያት ሆኗል።

የለውጥ ኃይሉ ወደ አመራር ከመጣ ወዲህ በተለያዩ ምክንያቶች ተጓትተው የነበሩ ፕሮጀክቶችን በማጠናቀቅ ሥራ ማስጀመር መቻሉን ጠቁመዋል ። በለስ ፣ ኦሞ ሁለትና ሶስት አልቆ ሥራ ጀምረዋል ። ይህ እንደ ትልቅ ድል የሚወሰድ ነው። አንድና አምስት በፋይናንስ ምክንያት መጓተቱን ጠቅሰው ግንባታውን ለማጠናቀቅ የፋይናንስ ችግሩ መቀረፍ አለበት ብለዋል ። ፕሮጀክቱ ተጠናቆ የአካባቢው ህዝብና ሀገሪቱ ተጠቃሚ እንድትሆን መንግሥት ጥረት ማድረጉን እንደሚቀጥል ነበር ያስገነዘቡት ።

ኦሞ ኩራዝ አንድ እና አምስት ለማጠናቀቅና ወደ ምርት ለማስገባት እየተደረገ ያለውን ጥረት አስመልክቶ ከአዲስ ዘመን ጥያቄ የቀረበላቸው የስኳር ኮርፖሬሽን ቃል አቀባይ አቶ ደመቀ ረታ እንደተናገሩት ፤ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልል ሊገነቡ ከታቀዱ አራት ስኳር ፋብሪካዎች መካከል ሁለቱ ማለትም ኦሞ ኩራዝ ቁጥር ሁለት እና ሦስት ስኳር ፋብሪካዎች ግንባታቸው ተጠናቆ ወደ መደበኛ ምርት የገቡ ቢሆንም፤ የቀድሞው ብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን (METEC) የኦሞ ኩራዝ ቁጥር አንድ ስኳር ፋብሪካ ግንባታን ለማከናወንና በ18 ወራት አጠናቆ ለማስረከብ በ2004 ዓ.ም ከስኳር ኮርፖሬሽን ጋር ውል ቢፈጽምም በታየው ከፍተኛ የግንባታ መጓተት ሳቢያ ውሉ በ2010 ዓ.ም እንዲቋረጥ ተደርጓል። ውሉ በመቋረጡ በአሁኑ ወቅት ለኩራዝ ቁጥር አንድ ስኳር ፋብሪካ ለምቶ የነበረ የሸንኮራ አገዳ ለኦሞ ኩራዝ ቁጥር ሁለት እና ሦስት ስኳር ፋብሪካዎች እየቀረበ ይገኛል።

በሌላ በኩል በሁለት ምዕራፍ የሚገነባውና ግንባታው ሙሉ በሙሉ ሲጠናቀቅ በአጠቃላይ በቀን 24 ሺህ ቶን አገዳ ይፈጫል ተብሎ የሚጠበቀው የኦሞ ኩራዝ ቁጥር አምስት ስኳር ፋብሪካ የግንባታ ሥራ JJIEC በተሰኘ የቻይና ኩባንያ ከህዳር ወር 2009 ዓ.ም ጀምሮ ሲከናወን የነበረ ቢሆንም ባጋጠመው የፋይናንስ ዕጥረት ምክንያት ግንባታው ሊቋረጥ ችሏል። የፋብሪካው የመጀመሪያ ምዕራፍ የግንባታ ሥራ በተቋረጠበት ወቅት አፈጻጸሙ የአካባቢው የህዝብ እንድራሴ በፓርላማ ከጠቀሱት በላይ መሆኑን ያነሳሉ። ግንባታው 27.1 በመቶ ደርሶ እንደነበርም ጠቁመዋል ።

በአሁኑ ወቅት የፋብሪካ ግንባታቸው ተቋርጦ የሚገኘውን የኦሞ ኩራዝ ቁጥር አንድ እና ቁጥር አምስት ስኳር ፋብሪካዎችን ግንባታና ሌሎች ተያያዥ ሥራዎችን ለማጠናቀቅ በመንግሥት ድጋፍ አማካይነት ከተለያዩ ምንጮች ፋይናንስ ለማግኘት ጥረት እየተደረገ ነው ። እስካሁን ድረስ ግን በተለያዩ ምክንያቶች የፋይናንስ ምንጭ ማግኘት እንዳልተቻለ ተናግረዋል ። በመሆኑም ፕሮጀክቶቹን ለማስቀጠል የሚያስፈልግ ፋይናንስ መገኘት እንደተቻለ ሥራዎች እንደሚቀጥሉ አብራርተዋል።

በኦሞ ኩራዝ ፋብሪካ ላይ የተደረጉ ጥናቶች እንደሚያሳዩት ፕሮጀክቶቹ በተያዘላቸው ጊዜ እንዳይጠናቀቁ ያደረጉ ከፋይናንስ በተጨማሪ ሌሎች ችግሮችም አሉ። የኩራዝ ስኳር ልማት ፕሮጀክት በኢትዮጵያ 'ጣፋጭ ራዕይ' እና ተግዳሮቶች መካከል የሚገኘው ፕሮጀክት በሚል ርዕስ በቤኔዲክት ካሚስኪ በተሰኘ ምሁር ተፅፎ ታንዲፍ ኦንላይን በተሰኘ ድረገጽ ላይ የታተመው የጥናት ውጤት እንደሚያሳየው ፤

በታችኛው የኦሞ ሸለቆ የሸንኮራ አገዳ ልማት እና የስኳር ልማት ላይ የታዩት ችግሮች የተለያዩ ምክንያቶች ሊጠቀሱ ይችላሉ ። ፕሮጀክቱ የሚገነባበት ቦታ ርቀት እና ተያያዥ የትራንስፖርት መሠረተ ልማት እጦት ፕሮጀክቱ በተያዘለት ጊዜ እንዳይጠናቀቅ አንዱ ምክንያት ሆኗል ።

በተጨማሪም ኮርፖሬሽኑ በቂ የቅድመ ዝግጅት ሳያደርግ በመንግሥት ግፊት የመጀመሪያ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አንድ ላይ ግቦችን ለማሳካት ተብሎ መጀመሩ ለፕሮጀክቱ መጓተት ሌላኛው ምክንያት ሆኗል። በመሆኑም ደካማ እቅድ፣ የተሳተፉት ቁልፍ እቅድ አውጪዎችና ተቋራጮች ልምድ አነስተኛ መሆን በፕሮጀክቱ ላይ በመጠን እና በማቀነባበር አቅም ላይ ከፍተኛ ማሻሻያዎች እንዲደረጉ ምክንያት ሆኖ ነበር። በተጨማሪም ግንባታው ከተጀመረ በኋላ በውጭ አማካሪዎች ምክር መሰረት መቀየር ያለባቸው ነገሮች ስለነበሩ እነዚህን መቀየር ተጨማሪ ወጪ እና ጊዜ መጠየቁን ጥናቱ ያሳያል።

ከዚያ ባሻገር በመጀመሪያው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዘመን ለስኳር ፕሮጀክቶች መንግሥት የሰጠውን አይነት ልዩ ትኩረት በሁለተኛው እድገትና ትራንስፎርሜሽን አለመስጠቱ ፕሮጀክቶቹ እንዲጓተቱ መንስኤ መሆኑን ጥናቱ ያሳያል። በሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ዘመን የመንግሥት ስትራቴጂክ ትኩረት ወደ ኢንዱስትሪ ፓርኮች በመሸጋገሩ የስኳር ኢንዱስትሪው ዝቅተኛ ትኩረት ተሰጥቶታል ። የመንግሥት ትኩረት መቀነሱ ለፋይናንስ እጥረቱ አንዱ መንስኤ ነው።

መንግሥት የኦሞ ኩራዝ ሁለት እና ሶስት ፕሮጀክቶችን እንዲሁም የበለስ ስኳር ፕሮጀክቶችን ከገባበት ቅርቃር በማውጣት ወደ ምርት እንዲሸጋገር የወሰደውን አይነት ቆራጥ እርምጃዎች በመውሰድ ቁጥር አንድ እና አምስትን በማጠናቀቅ ወደ ምርት ለማሸጋገር ቆራጥ እርምጃዎችን ሊወስድ ይገባል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## በዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ጥበቃ ሥም የወጡ ሪፖርቶች የአሸባሪውን ሕወሓት ገበና የመሸፈን ተልዕኮን ያነገቡ ናቸው!

ለመግደል ተደራጅቶ በሰው ልጆች ላይ ሲፈጽም ያሳለፋቸውን ተጨባጭ ተግባራት ከግምት በማስገባት ነበር ሕወሓት አሸባሪ ተብሎ እአአ 1983 በዓለም አቀፍ የሽብርተኝነት መዝገብ ስሙ የሰፈረው፡፡ ግብሩና ፍረጃው በወጉ የተጣመሩለት ይህ ቡድን ታዲያ የአሸባሪነት ስያሜውን በግብር እየገለጠ "ሰይጣን እንኳን ይቀናበታል" በተባለለት ድርጊቱ ላለፉት 40 እና ከዚያ በላይ ዓመታት በኢትዮጵያውያን ላይ በሕግ ይቅር የማይባል፤ በታሪክ ፈጽሞ ሊረሳ የማይችል ግፍና በደል ፈጽሟል፡፡

ይሁን እንጂ አሸባሪ የሚል ተቀጥላው ከልብ ሳይሆን ለማስመሰል ያህል የተሰጠው፤ አልያም ከትዕዛዝ የማፈንገጥ አዝማሚያ ካሳየ መቅጫ የሚሆን የቅድመ ዝግጅት ስያሜ ስለመሆኑ ብዙም መከራከር የማያስፈልገው ሀቅ ነው፡፡ ምክንያቱም ሽብርተኛን አሳድዶ የሚቀጣው የምዕራቡ ዓለም አሸባሪ ተብሎ የተከተበውን ሕወሓትን ከማሳደድ ይልቅ የማገዝና የማጎልበት ሂደት ነበር የተስተዋለው፤ አሁንም በኢትዮጵያ ፓርላማ ይሄው የሽብርተኛ ስያሜው ከጸደቀለት ማግስት እየሆነ ያለው ይሄው ነው፡፡

እናም "ጣት ገማ ተብሎ ተቆርጦ አይጣልም" እንዲሉ፤ ለተልዕኮ ፈጥረውታልና ተልዕኮውን ከግብ ሳያደርስ በአጭር እንዲቀር አልፈለጉም፡፡ ለዚህ ደግሞ በቀጥታ ከሚደረግለት ድጋፍ በተጓዳኝ በሰብዓዊነት እና ዴሞክራሲ ስም የተደራጁ ተቋማትን በገፍ ወደ ኢትዮጵያ እንዲገቡ በማድረግ በተለያየ አግባብ መደገፍም፣ መቅጣትም የሚችሉበትን መንገድ እንዲያደላድሉላቸው እድል ፈጠሩ። አምስቲ ኢንተርናሽናል እና ሂዩማን ራይትስዎች ደግሞ ከእነዚህ ተቋማት መካከል ተጠቃሾቹ ናቸው፡፡

እነዚህ ተቋማት ደግሞ አሸባሪው ሕወሓት ከጫካ እስከ ቤተ መንግስት ባለው ጉዞው፤ በተለይም በቤተ መንግስት ባለው የ27 ዓመታት ቆይታ ከፍ ያለ ድጋፍ ሲያደርጉለት ቆይተዋል፡፡ ሕዝብ ሰብዓዊ መብቴ ተጣሰ፣ ታሰርኩ፣ በግፍ ተደበደብኩ፣ በጅምላ እየተፈረጅኩ ተጨፈጨፍኩ እያለ የሰብዓዊ መብቱ ስለመጣሱ ድምጹን ሲያሰማ፤ እነዚህ ተቋማት ምንም እንዳልተፈጠረ፣ ይልቁንም ሕወሓት መራሹ መንግስት ለሰብዓዊ መብቶች መከበር በሕገመንግስቱ ጭምር በበርካታ አንቀጾች በማካተት እየሰራ ስለመሆኑ ከሹማምንቱ የሚሰጡ መግለጫዎችን ይቀባበላሉ፡፡ ሕዝቡ ድምጼ ታፈነ፣ የመናገር፣ የመደራጀትና ሌላም ዴሞክራሲያዊ መብቴ ተገፈፈ ሲል፤ እነሱ ከዚህ በተቃራኒው የሚነገርን የሕወሓት እንደራሴዎች ልሳን ደግመው ያስተጋባሉ፡፡

ለዚህም ነው በአሸባሪው ሕወሓት የስልጣን ዘመን ዜጎች ሲሰደዱ፣ ሲታሰሩ፣ ሲገደሉ፣ እምነታቸውን በነጻነት መከወን ሲቸገሩ፣ በማንነታቸው ሲሳደዱ፣ በጅምላ ተጨፍጭፈው በጅምላ ሲቀበሩ፣ ሲኮላሹ፣ ሴቶች በቡድን ሲደፈሩ፣ በማህጸናቸው ስለትና የተለያየ ባዕድ ነገር ሲከተት፣ እና ሌሎችም አሰቃቂ ግፎች በሥርዓቱ አቀንቃኞች ሲፈጸምባቸው እንዳላየና፣ እንዳልሰማ ማለፋቸው፡፡ ለምን ቢባል፣ ይሄን ካጋለጡ ሕወሓት በሕዝብ ሊገፋ ዓለም አቀፍ ጫናም እንዲፈጠርበት መንገድ ይከፍታል። ይህ እንዲሆን ደግሞ አይፈለግም፤ የሚፈለገው ቡድኑ በስልጣን ላይ ቆይቶ የሕዝብን ሳይሆን የውጭ ኃይሎችን ጥቅም እንዲያስጠብቅ ነው፡፡ እነ አምንስቲ ደግሞ ከስማቸው በተቃራኒ የሕዝብን እውነትና ብሶት አፍኖ የቡድኑን ገጽታ መገንባት የተሰጣቸው የፖለቲካ አስፈጻሚነት ተልዕኮ ነው፡፡



እናም ኢትዮጵያን ለማጠልሸት የሚሄዱበት ርቀት፤ በተዛባ የጥናት ዘዴ የተቀናበረ ሪፖርት የማቅረብ ተደጋጋሚ ሂደት፣ ጊዜ እየጠበቁ ኢትዮጵያ የምትሰራቸውን መልካም ተግባራት የማጠልሸት፣ የምታጋልጣቸውን ውሸቶች ለመሸፈን የሚያደርጉት ሩጫ ዛሬም ድረስ ዘልቋል፡፡ ይህ ደግሞ የፖለቲካ ጉዳይ አስፈጻሚነታቸው መገለጫ ነው፡፡ ለዚህም ነው እነርሱ ለአርባ ዓመታት አፍነው የሸሸጉትን እውነት ከሰሞኑ የጎንደር ዩኒቨርሲቲ በትናት ታግዞ ባጋለጠ ማግስት ይሄን እውነት ለማፈን ሼልፍ ላይ ከደረደሯቸው የከፉ ጊዜ መጠባበቂያ ሪፖርት መሰል መሳሪያዎች ስበው ያወጡት፡፡ የዘነጉት ጉዳይ ግን በተለይ ከሕግ ማስከበር እርምጃው ማግስት የአካባቢው ማህበረሰብ በነጻነት መኖር በጀመረበት ወቅት ይሄን አይነት ሪፖርት ይዞ መውጣት እውነትነቱ በእጅጉ ትዝብት ላይ የሚወድቅ፤ የተቋማቱ የሰብዓዊና የዴሞክራሲ ጉዳይ ተሸካሚነት በትልቅ ጥያቄ ውስጥ የሚገባና ጭምብላቸውን የገለጠ መሆኑን ነው፡፡

በዚህ ሪፖርት ሌላው የተገለጠው ግብራቸው፤ ሕዝቦች እርስ በእርስ እንዳይተማመኑና እንዲጠላሉ ብሎም በቂም በቀል ስሜት እንዲኖሩ የሚያደርጉ መርዛማ የፖለቲካ ተልዕኳቸውን ማስፈጸሚያ ቃላትና ሐረጋትን በስፋት መጠቀማቸው፤ እነዚህም አጽንዖት እንዲያገኙ በየገጾቻቸው የግርጌ ላይ ያሰፍሯቸዋል፡፡ ለምሳሌ፣ በሰሞንኛው ሪፖርት ለዚህ ዓላማ ከተጠቀሙበት ሀረግ መካከል "WE WILL ERASE YOU FROM THIS LAND/ ከዚህ ምድር እናጠፋችኋለን" የሚለው ተጠቃሽ ሲሆን፤ ይህ ሀረግ ይሁነኝ ብለው ኢትዮጵያን እንደ አገር ገጿን ለማጠልሸት፤ መንግስትን እንደ መንግስት ለመኮነን፤ ኢትዮጵያውያንንም እንደ ሕዝብ እሴቶቻቸውን አጠልሽተው የነገ አብሮነታቸው በማያባራ ግጭት ውስጥ እንዲዘልቅ ማስቻልን ታሳቢ ያደረገ ነው፡፡

ከዚህም በላይ እንዲህ አይነት ይሁነኝ ተብለው ተመርጠው የሚሰነቀሩ ቃላትና ሀረጋት ለምዕራባውያኑ ጫናና ማዕቀብ ተፈጻሚነት እንደ ግብዓት ሆነው እንዲያገለግሉ፤ ለምን ብሎ ለሚጠይቅ አካልም ለሰብዓዊና ዴሞክራሲ ጉዳዮች የሚሰሩ ተቋማት የምርመራ ግኝትን መነሻ አድርገን ወሰንን ብለው እንደ ማስረጃ እንዲያቀርቡት በተጠና መልኩ የሚከወን ነው፡፡ ማጠቃለያው የአምነስቲም ሆነ የሂዩማራይትስዎች መግለጫዎች የሽብር ቡድኑን የመጠበቅ ተልዕኮ መገለጫ ነው!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ
- ዘላለም ግርማ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


**ነፃ ሃሳብ**

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ለሕግ መከበር ቅድሚያ ይሰጥ

**ምሕረት ሞገስ**

አንድን አገር አዘቅት ውስጥ ከሚከቱ ዋነኛ ምክንያቶች መካከል አጠቃላይ የሕግ መከበር እና ማስከበር ችግር ዋነኛው ነው፡፡ አጠቃላይ ሕዝብ ህግ ማክበር አለበት፡፡ ተገልጋይም ሆነ አገልጋይ፣ ሰባኪውም ሆነ ምዕመኑ፣ መምህሩም ሆነ ተማሪው የፓርቲም ሆነ የመንግስት ባለስልጣን ሁሉም ከህግ በላይ ከሆነ ነገር ተበላሸ ማለት ነው፡፡ ሕግ ተገቢውን ሥፍራ ካላገኘ መባለግን እንደተራ ጉዳይ አይቶ ማለፍ ከተበራከተ፤ የአገር ህልውና ፈተና ውስጥ መውደቁ የማይቀር ነው፡፡

በአንዳንድ ቦታ ላይ የሚታዩ ጋጠ ወጥነቶች ለጊዜው ባለጌውን እየጠቀሙ ያሉ ቢመስልም፤ ውሎ አድሮ ሁሉንም መጉዳቱ የማይቀር ነው፡፡ ከሰሞኑ አንድ ዜና ተሰማ፡፡ የአፋሯ ዱብቲ ከተማ ሕብረተሰቡ ውሃውን ከቆጣሪ ውጪ ከዋናው መሥመር ጋር እያገናኘ መጠቀም በመጀመሩ፤ የከተማዋ የውሃና ፍሳሽ አገልግሎት ከፍተኛ ኪሳራ እንደገጠመው እና ለሠራተኞቹ ደመወዝ መክፈል እንደተሳነው ተገልጿል፡፡ በመጨረሻ ተቋሙ ለከተማው ሕዝብ አገልግሎት መሥጠት የማይችልበት ደረጃ ላይ ደረሰ፡፡

ይህ ብቻ አይደለም፡፡ በሌሎችም አንዳንድ ክልሎች የተሰበሰቡ ወጣቶች ኢንቬስተርን እና ባለሃብትን፣ ከባለሃብት አልፎ ተራውን ሕዝብ ሳይቀር እያስፈራሩ እየዘረፉ አልፈው ተርፈው እየገደሉ ስለመሆኑ ይወራል። እነዚህ ወጣቶች ሕግ አይገዛቸውም፡፡ በህግ ተከራክሮ ማስጠየቅም ሆነ ማስቀጣት ዘበት ነው፡፡

አንዳንዴ መኪና ለማሳለፍ የኮቴ የሚያስከፍሉ አልፈው ተርፈው ሰዎችን በየመንገዱ አለፍ ሲልም ቤት ድረስ ሔደው እያስገደዱ ገንዘብ የሚቀበሉ ቡድኖች ‹‹ሸኔ ናቸው›› ተብሎ ቢወራም በቅርብ ርቀት ተጠግተው ወንጀል እስከ መስራት የደረሰ ድፍረት በሸኔ የተፈፀመ ነው ለማለት ያዳግታል፡፡ እርግጥ ነው፤ ኦነግ ሸኔ ብዙ ጥፋት አስከትሏል፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠላት ለሆኑ አካላት ተላላኪ በመሆን በወንጀል ሥራ ላይ በመሠማራት ብዙዎች እንባቸው እንዲፈስ አድርጓል፡፡ ነገር ግን ደግሞ በኦነግ ሸኔ ስም ጥፋት ላይ የተሠመሩ እንደማይጠፉም ተጎጂዎች እየገለፁ ነው፡፡

መንግስት ሸኔን ማጥፋት፤ በመንግስት መዋቅር ሥር ተሰግሥገው አገር እያመሱ እያተራመሱ፤ ገንዘቡንም እያፈሱ ያሉትን ህግ ፊት በማቅረብ ተጠያቂ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ‹‹አለባብሰው ቢያርሱ በአረም ይመለሱ›› እንደተባለው ሸፋፍኖ መሾም፤ ሕግን ከማስከበር ይልቅ ጥፋት ማድረሳቸው እየታወቀ፤ በመረጃ እና በማስረጃ እየተረጋገጠ እንዲሁ በለሆሳስ ማለፍ ሕዝብን ያሳዝናል፡፡ ያው እንኳን የሕዝብ ማዘን የግለሰብ ሀዘንም ቢሆን ለታዘነበት አካል የሚበጅ አይደለም፡፡ እንግዲህ ዘመን ተገልብጦ ታሪክ የሚቀየርበት አጋጣሚ ይፈጠራል፡፡ ያኔ ለጥጋበኛው ማዘን የግድ ይሆናል፡፡

መንግስት ትናንት ከነበረው በመማር ማንም ቢሆን ሕግ እንዲያከብር ማስገደድ አለበት፡፡ ለዚህም ሁኔታዎችን የማመቻቸት ሥራ ካልሠራ ምኑን የተሻለ መንግስት ሆነ የሚል ወቀሳን ያስከትላል፡፡ መንግስት ባለበት በዚህች ትልቅ አገር ውስጥ በሰላም ወጥቶ መግባት እንደትልቅ ጉዳይ ታይቶ በአጀንዳነት ሊቀርብ አይገባም። በመንግሥት የተሾመ ባለሥልጣን ዝርፊያ ውስጥ ገብቶ ኃላፊነቱን በብቃት መወጣት እና በእርግጥም ሠላም ለማስፈን የሚያስችል ሁኔታን ማመቻቸት ከተሳነው እሹሩሩ ማለት አስፈላጊ አይደለም፡፡ በመዋቅር ውስጥ የተሰገሰገው ኃይል ከህግ በላይ አለመሆኑን ማወቅ አለበት፡፡

ባለሥልጣንም ሆነ ባለሙያ ተገልጋይም ሆነ ማንኛውም ቡድን እና ግለሰብ ከሕግ በላይ ልሁን ብሎ ጥፋት ከፈፀመ፤ በጥፋቱም የማይጠየቅ ከሆነ እና ፍትሕ ከተደፈጠጠች የሕዝብ ጥላቻ እንደ ሰደድ እሳት እየተስፋፋ ኢትዮጵያ አገር ሆና መቆም የማትችልበት ደረጃ ላይ መደረሱ የማይቀር ነው፡፡ አገር ከፈረሰ ባለስልጣን፣ ወጣት ብሔርም ሆነ ጎሳ እንዲሁም ሃይማኖት ብሎ ነገር አይኖርም፡፡ ኢትዮጵያ የምትባለው አገር በእግሯ መቆም ካልቻለች በአፍ እየተለፈፈ ያለው እና ብዙዎች ውስጥ ሥር እየሰደደ ለውጥ ያመጣል የሚባለው አንድነት ብሎ ነገርም አደጋ ያንዣብብበታል። አንድነት ቀርቶ መፈረካከስ ግድ ይሆናል፡፡ ለእዚህ ዋነኛው መፍትሔ ማንም ሆነ ማን በሕግ አደብ እንዲገዛ ማድረግ ብቻ ነው፡፡

በሥልጣን መባለግም ሆነ ሥርዓተ አልበኝነት አሁኑኑ በመንግሥት አሠራር እንዳይኖሩ መከላከል ያስፈልጋል፡፡ ለእዚህ መፍትሔው ተቋማትን ማጠናከር ነው፡፡ ሕዝብ የሚፈልገውን አገልግሎት ለመስጠት፣ ከሕዝብ ወቀሳ ለመዳን ግልጽና ተጠያቂነት ያለበት አሠራርን መዘርጋት ይገባል፡፡ ተቋማት ከማህበረሰቡ ፍላጎት እና ከዘመኑ ጋር የሚመጥን ዕድገት እንዲኖራቸው በአመራር፣ በባለሙያ፣ በቴክኖሎጂና በተለያዩ ግብዓቶች ማደራጀት የግድ ነው፡፡

ነገር ግን አመራሩም ሆነ ባለሙያው የብቃት ችግር ኖሮበት፤ ያለበትንም የብቃት ችግር ሳይረዳ መፍትሔ ከማመላከት ይልቅ የሕዝቡን ሥቃይ የበለጠ ማባባስ ላይ ከተሠማራ አደጋው የከፋ ይሆናል፡፡ ይህንን ችግር ለማቃለል አመራሩም ሆነ ባለሙያው በሕይወቱ ስኬታማ ኑሮን እንዲመራ ራሱንም ሆነ አገሩን እንዲጠቅም በሚችለው ሥራ ላይ እንዲሠማራ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ሌላው ቢቀር ራሱን የሚያሻሽልበትን ሥልጠና መስጠት ላይ ትኩረት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በእዚህ በኩል እርምጃ ለመውሰድ ነገ ዛሬ ማለት አይገባም፡፡

አመራር ሲመሰገን እንጂ ሲወቀስ መስማት የለበትም። ሙሉ ለሙሉ ሁሉም ያመሰግነው ለማለት ቢያዳግትም ሁሉም ተገልጋይ ወቃሽ ከሆነ እርሱ እየሔደበት ያለው መንገድ እና እየሰጠ ያለው አገልግሎት ትክክል ነው ብሎ ቢያምንም ብዙ ሕዝብ አልስማማም ካለ ራስን መፈተሽ ይገባል፡፡

በመንግስት በኩል የሕዝቡን ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ማፈን ነፃ ሃሳባቸውን የሚያስተላልፉን ማሰር፣ ማሳደድና መግደል ቆሟል ቢባልም ቡድኖች የሚፈፅሙትን ዘግናኝ ተግባር በጊዜ መቆጣጠር ከልተቻለ ሕግ ካልተከበረ ዞሮ ዞሮ አደጋው መንግስት ላይ አልፎ ተርፎም ሕዝብ ላይ መፈጠሩ የማይቀር ነው፡፡

ኢትዮጵያ ሰፊ መሬትና ትልቅ የውኃ ሀብት ለዛውም ሊሠራ ከሚችል ወጣት ኃይል ጋር የታደለች በመሆኗ ይህንን ዕድል መጠቀም ያስፈልጋል፡፡ ይህን ሃብት በተገቢው መንገድ መጠቀም ከተቻለ ከልመና ተላቃ በአፍሪካ አህጉር በነፃነት ፋና ወጊነቷ የምትታወቀዋ አገር በዓለም ተፅዕኖ ፈጣሪ መሆን የምትችልበት ደረጃ ላይ መድረስ አይሳናትም፡፡ ለእዚህ ግን መነሻውም ሆነ መድረሻው የሕግ የበላይነት ነው፡፡

ይህ እንዲሆን ደግሞ የእዚህ ዘመን ትውልድ ትልቁቱን ለነገው ትውልድ ለማስተላለፍ ከትዕቢት፣ ከማናለብኝነት፣ ከዘረፋ እና ከወንጀል ድርጊት ራሱን ማራቅ አለበት፡፡ ይህ ብቻ አይደለም በትጋት በመሥራት ለራሱ እና ለቤተሰቡ ብቻ ሳይሆን ለአገሩ እና ለዓለም የሚሆን በረከትን በመሥራት የተፈጠረበትን ዓላማ ማሳካት ላይ ትኩረት ሊሰጥ ይገባል፡፡ ለእዚህ ዋነኛ መነሻውም ሆነ መድረሻው አሁንም ህግ አክባሪነት ነው፡፡ በትክክልም ሕዝቡ ህግ አክባሪ መሆን አለበት። ወጣቱን ጨምሮ አጠቃላይ ሕዝቡ ሕግ እንዲያከብር መንግስት በተለይም በፀጥታ ሃይል በኩል ያሉ አመራሮች ሃቅ ላይ ተመስርተው ዘመድ ባዳ ሳይሉ ህግ የማስከበር ኃላፊነታቸውን ሊወጡ ይገባል፡፡

# እንዲህም ይኖራል

**ሕይወት ፈርጀ ብዙ ገጽታዎች አሏት፤ መውጣት እንዳለ ሁሉ መውረድም ይኖራል። ከመውረድ ውስጥም በትጋት መውጣት ይቻላል። አግኝቶ ማጣት እንዳለ ሁሉ አጥቶም ይገኛል። ይህ የህይወት እውነታ ነው፤ በጥቂቶች የህይወት መውጣትና መውረዶች ውስጥ ብዙዎች ይማራሉ። የህይወትን ፈተናዎችም ያውቃሉ። በከፍታ ውስጥ የሚገኙት ‹‹እንዲህም ይኖራል እንዴ?›› ብለው ራሳቸውን ይጠይቃሉ። ለተቸገሩት ያዝናሉ፤ ካላቸው ቀንሰው የሌሎችን ችግር ይካፈላሉ፤ በተጨማሪም ችግር ብልሃትን ያስተምራል እንዲሉ ከችግር ጋር ተላምዶ ከመኖር ይልቅ ለመፍትሄ የሚታትሩትንም ያበረታታሉ። በመሆኑም ‹‹እንዲህም ይኖራል›› ብለን በከፈትነው አምዳችን ህይወትን በየፈርጁ ታስተውሉበት፤ ^አስተውላችሁም ትማሩበት ዘንድ ጋበዝናችሁ። ለአስተያየቶቻችሁ፤ ለመሰል ታሪኮች ጥቆማችሁ እንዲሁም ለድጋፋችሁ የዝግጅት ክፍላችን አድራሻ ትጠቀሙ ዘንድ ጋበዝናችሁ።**

## ኑሮና በሽታን አሸንፎ ራስን የማሰንበት ግብግብ

**ሰላማዊት ውቤ**

ዓለማችን በተቃራኒ ነገሮች የተሞላች ነች። ዛሬ ብታስደስተን ነገ ታሳዝነናለች። እነዚህን ተቃራኒ ነገሮች መሰረት ያደረገው ኑሮም መቼም ቢሆን ጎዶሎ አያጣም። ዛሬ ቢሞላ ነገ መጉደሉ አይቀርም። በመሆኑም በራሱ የሰው ልጅ ፈተና ነው። ህመም ሲታከልበትም ጫናው የበለጠ ይከብዳል። ሆኖም ጫናውን ለማሸነፍ የሚፍጨረጨሩ ሰዎች አይጠፉም። የዛሬ እንግዳችን አንዱ ናቸው።

እንግዳችን ማቲዎስ አላሮ ይባላሉ። በሙያቸው ወታደር ነበሩ። ወታደር ማቲዎስ እንዳወጉን ታዲያ ያኔ በዘመነ ደርግ 503 ነበልባል በሚባለው የጦር ግብረ ኃይል ባልደረባነት ለመጀመሪያ ጊዜ መከላከያ ሠራዊትን በቅጥር ሲቀላቀሉ የ20 ዓመት አፍላ ወጣት ነበሩ። ወታደር ማቲዎስ የውትድርናውን ዓለም በመቀላቀል ለመጀመሪያ ጊዜ በሥራ ገበታ ላይ የተሰማሩትም በዚሁ በ20 ዓመት አፍላ የወጣትነት ዕድሜያቸው ነበር።

ይሄ ዕድሜ የወጣትነት ከወጣትነትም የአፍላ ወጣትነት ወቅት እንደመሆኑ ፈታኝ ነው። ወቅቱ ችኩልነት፣ ስሜታዊነት፣ ትዕግስትና እርጋታ በደምሳሳው የማመዛዘን አስተውሎት ያንሰዋል። በዚህ ዕድሜ ክልል ያለ ሰው ፍላጎቶችም ዘርፈ ብዙና የተለያዩ ናቸው። አወዳደቁ እንዲያምርና ሕይወቱ በስኬት ጎዳና እንድትጓዝ የግድ የሚመራና ምክሩን የሚለግሰው ሰው ሁሉ ሊያስፈልገው ይችላል። ሆኖም እሳቸው ወደ ውትድርና ሙያ ሲገቡ ይሄ አልነበራቸውም። ‹‹ሆኖም በውትድርናው ዓለም ከገባሁ በኋላ ከወታደራዊ ስነስርዓት ጀምሮ አጠቃላይ ሕይወቴን በስርዓት ልመራበት የሚያስችለኝ ዕውቀት ቀስሜያለሁ›› የሚሉት ወታደር ማቲዎስ ከዚህ ጎን ለጎን አፍላው የወጣትነት ዕድሜያቸው ገፋፍቶና አሸንፏቸው ዘና ፈታ ከሚያደርጉ ነገሮች አጋልጧቸው እንደነበርም አጫውተውናል። ተጋላጭነቴን እንዳላስተውል የወጣትነት አፍላ ዕድሜዬ ዓይኔን ጋርዶኝ ነበር ማለት እችላለሁ›› ሲሉም የወጣትነት ዕድሜ ክልልን ጫናና ክብደት ገልፀውልናል። ይሁን እንጂ፣ ፈጣሪ የወጣትነት ዕድሜያቸው ለገዳዩ ኤች አይቪ/ኤድስ በሽታ ካጋለጣቸው በኋላ የሚገጥማቸውን የሕይወት ውጣ ውረድ ግብግቦች በሙሉ ታግለው ሕይወታቸውን የሚያሰነብቱበት ዕውቀት አልነፈጋቸውም።

እንግዳችን እንደ አንዳንዶቹ በኤች አይቪ ኤድስ በሽታ የተያዙ የሕብረተሰብ ክፍሎች በቫይረሱ መያዛቸውን ለመጀመሪያ ጊዜ ሲሰሙ አልደነገጡም። ደንግጠውና ተስፋ ቆርጠውም የአልጋ ቁራኛ ሆነው አልቀሩም። ሕይወታቸውን ለማጥፋትም አልተነሳሱም። ይልቁኑም ቀጣይ የሕይወት ዘመናቸውን እንዴት አድርገው ማሰንበት እንዳለባቸው መንገድ ቀየሱ። የመጀመሪያው ከቦታ ቦታ በመዘዋወር ራሳቸውን ገልጠው ሕብረተሰቡ ለበሽታው እንዳይጋለጥ ግንዛቤ መፍጠር ነበር። ሁለተኛው በዚህ አጋጣሚ የሚያገኟቸውን የትኞቹንም ዓይነት ሥራዎች መሥራትና ገቢ ማግኘት ነበር። ይሄኛው ሥራቸው በበሽታው ምክንያት አልጋ ላይ የዋሉትን የሕብረተሰብ ክፍሎች ጥንቃቄ በተሞላበት ሁኔታ መንከባከብንም ያካትታል። ‹‹ምንም ገቢና አቅም የሌላቸውና ከነፃ እንክብካቤ ጀምሮ ድጋፍ የሚሹ የኤች አይቪ/ኤድስ ሕሙማን እንዳሉ ሁሉ ገንዘብ ኖሯቸው የሚደግፋቸው ወገን አጥተው አልጋ ላይ የዋሉ የቫይረሱ ሕሙማን አሉ›› የሚሉት ወታደር ማቲዎስ ምንም ገቢ ለሌላቸው በነፃ ከሚያደርጉት እንክብካቤና ምክር ባሻገር ገንዘብ ላላቸው ህሙማን እቤት ለቤት ከሚያደርጉት ምክርና እንክብካቤ ድጋፍ ገቢ እንደሚያገኙም ነግረውናል። በተረፈ ከቦታ ቦታ እየተዘዋወሩ ግንዛቤ ማስጨበጡና ህሙማኑን መንከባከቡ ፋታ አይሰጣቸውም እንጂ፣ ፋታ ካገኙ ከጉልበት ሸከማ ጀምሮ የሚያገኟቸውንና ሌሎች የሕብረተሰብ ክፍሎችን በንክኪ ለበሽታ የማያጋልጡ ሌሎች ሥራዎችንም ይሰራሉ።

ወታደር ማቲዎስ በሽታን አሸንፈው ሕይወታቸውን


ፎቶ ዳኜ አበራ

**ወታደር ማቲዎስ አላሮ**

ለማሰንበት በሚያደርጉት ጥረት ከሚያገኙት ገቢያቸው ወጣ ስንል የፀረ-ኤች አይቪ/ኤድስ ህክምና መድኃኒት ተጠቃሚ በመሆናቸው በአሁኑ ወቅት ጤንነታቸው በጥሩ ሁኔታ ላይ ይገኛል። ቫይረሱ በደማቸው ውስጥ እንዳለ ያወቁት በ1990 ዓ.ም መጀመሪያ አካባቢ ሲሆን ቀደም ብሎ በበሽታው ምክንያት ሕይወቱን ያጣውና ‹‹በእኛ ይብቃ ትውልድ ይዳን›› በማለት የራሱን ተሞክሮ እያቀረበ ጭምር ሕብረተሰቡ ከቫይረሱ ራሱን እንዲጠብቅ ሲያስተምር የነበረው “የዘውዱ ኢኒሼቲቭ” ቫይረሱ በደማቸው ውስጥ የሚገኝ ወገኖች ማህበር አባል ናቸው።

የፀረ-ኤች አይቪ/ኤድስ ህክምና መድኃኒት ተጠቃሚ ከሆኑ 11ኛ ዓመታቸውን አገባድደዋል። ቫይረሱ በደማቸው ውስጥ መኖሩን አውቀው ውስጣቸው ይሄንኑ አምኖና ተቀብሎ ራሱን በማረጋጋት ሌላውን የማዳን ተልዕኮ ካስታጠቃቸው ጀምሮ በማህበራቸው አማካኝነት በአራቱም ማእዘን የአገሪቱ አካባቢዎች እየተዘዋወሩ ሕብረተሰቡን ግንዛቤ ማስጨበጥ የጀመሩት በ2000 ዓ.ም ነው። ለአብነት ‹‹በእኛ ይብቃ ትውልድ ይዳን›› የሚለውን የሕይወት መርህ አንግበው ወደ ወሎ፣ ሳይንትና ላሊበላ ተጉዘው ግንዛቤ ያስጨበጡበትን ሁኔታ ይጠቀሳል።

የኤች አይቪ በሽታን ገዳይነት ቀበሌ፣ ወረዳና ዞን ዘልቀው ብዙዎች በበሽታው መርገፋቸውን ጠቅሰውና በዱር በገደሉ እየዞሩ እራሳቸውን ዋቢ በማድረግ እዚህ ቀውስ ላይ እንዳይወድቁ በመምከርና በመዘከር ሲያስተምሩ ቆይተዋል። በዚህ ተግባራቸው ከተማሪ እስከ አርሶ አደር ያውቃቸዋል።

እኛም ያገኘናቸው በዚሁ ከተቀደሰ ስራቸው አንዱ በሆነው ተግባር ላይ እያሉ ነው። በተለይ የኤች አይቪ/ኤድስ ቀን በሚከበርበት ወቅት የራሳቸውን ተሞክሮ ዋቢ አድርገው ለበዓሉ ተሳታፊዎች ግንዛቤ የሚያስጨብጡበት ጊዜም ብዙ ነው።

ወታደር ማቲዎስ እኛ ባገኘናቸው ወቅት እንዳወጉን ታዲያ ቋሚ የሚባል አድራሻዬ ነው ብለው የሚናገሩት ቂርቆስ ክፍለ ከተማን ቢሆንም በክፍለ ከተማው በስማቸው ተመዝግቦ የቤት ቁጥር የተሰጠው መኖሪያ ቤት የላቸውም። እየኖሩ ያሉት ዛሬ አንዱ ቤት፣ ነገ አንዱ ቤት በማደር ነው። በአብዛኛው ወደ ተለያዩ የአገሪቱ ክልሎች እየተዘዋወሩ ህብረተሰቡን በማስተማራቸው አዲስ አበባ ላይ እምብዛም አለመቀመጣቸው ጠቅሟቸዋል። በእርግጥ እንዲህ ባለው ሁኔታ መኖር እንኳን ለህሙማን ለጤናማም ሰው ይከብዳል።

ይሄ የአኗኗር ሁኔታቸው መድኃኒታቸውን ሳያቋርጡ በመውሰድ ጤናቸውን እንዲጠብቁ ለማድረግ ብዙም የሚያመቻቸው እንዳልሆነም አጫውተውናል። በየቀኑ ጠዋት አንድ ማታ አንድ እንክብል ፀረ-ኤች አይቪ/ኤድስ መድኃኒት ይወስዳሉ። በእርግጥ ቀንና ሰዓቱ እንዳይስተጓጎልባቸው በአውቶብስ፣ በባቡርና በእግር እየተጓዙ ባሉባቸው መንገዶች ላይ ጭምር የሚወስዱበት ሁኔታ አለ። እንደሚናገሩት በአሁኑ ወቅት ቫይረሱ በደማቸው ውስጥ አለ። ይሁን እንጂ፣ ግንኙነት ቢያደርጉ ለሌላ ሁለተኛ ሰው በማያስተላልፉበት ሁኔታ ነው። ነገር ግን ሕዝብን በተለይም አገር ተረካቢውን ዜጋ ከሞት ለመታደግ እንደመዝመታቸው እንደ አንዳንድ ቫይረሱ በደማቸው ውስጥ ያለና በሽታው እንዲስፋፋ አስተዋጾ የሚያደርጉ ኃላፊነት የጎደላቸው ግለሰብ ወገኖች ከተቃራኒ ጾታ ጋር ግንኙነት እንደማያደርጉ እንዲሁም እንዴት በቫይረሱ እንደተያዙ በዝርዝር አጫውተውናል።

ያጫወቱን ከወጣትነት ዘመናቸው ጀምረው ነው። የወጣትነት ዕድሜ ዘመናቸው ታዲያ በተሰለፉበት የጦርነት አውደ ግንባር ማሸነፍን ብቻ ሳይሆን መዝለል፣ መጨፈርና፣ ከዚያችም ከእዚችም ጋር መዝናናትና መውጣትን ወይም አንሶላ መጋፈፍንም እንደ ጀብድ ይቆጥሩት ነበር።

በተለይ የእረፍት ቀናቶች በሆኑት ቅዳሜና እሁድ መጠጥ በመጠጣት አንሶላ ተጋፈው ገደብ የሌለው የወጣትነት የወሲብ ፍላጎታቸውን ለማርካት በየጉዟቸው መካከል የሚያገኟቸው እንደነ ሽሬ፣ ሽራሮ፣ አክሱም፣ ዓድዋ ... ውስጥ የሚገኙ ትንንሽ ከተሞች አልበቃ ብሏቸው እስከ መቐለ ድረስ በመዝለቅ ከጓደኞቻቸው ጋር “ዓለማቸውን ይቀጩ” እንደነበር ዛሬ ላይ በቁጭት ያስታውሳሉ።

ብዙዎቻችሁ ያውም በወጣትነት ዘመን እንደ ወታደር ማቲዎስ ዘና ማለት ያስደስታል እንጂ ምን ያስቆጫል ትሉ ይሆናል። ነገር ግን ያውም በዓለማችን ምንም ዓይነት መድኃኒት ባልተገኘለት ኤች አይቪ/ኤድስ በሽታ ዘመን እንዲህ ዓይነቱ መዝናናት መዘዙ ብዙ ነው ብቻም ሳይሆን ለተዝናኘው እጅግ አስጊና አሳሳቢም ነው። በተለይ ወደ ኋላ ላይ መብላትና መጠጣቱ፣ እየጨፈሩና እየተዝናኑ መደሰቱ፣ መሳቅ፣ መጫወቱ፣ ይሄ ቀራት የማይሏትን ለግላጋና ውብ ወጣት በየደቂቃው በዓይነ ህሊና በመሳል ማየቱና ማስታወሱ ለዛው እየደበዘዘና መልኩ ወደ አስፈሪ አውሬነት እየተለወጠ ትዝታው ቢረግፍ እንኳን በፍፁም ማስታወስ በማይፈልጓቸው ሁኔታዎች እየተተካ አያሌ ቁጭቶችንና ፀፀቶችን ይፈጥራል።

31ኛውን ክፍለ ጦር በመወከል በተለያዩ አውደ ግንባሮች በተካሄዱ ታላላቅ ጦርነቶች ተካፍለው ዓይናቸው ሳይጠፋና አንድም የአካል ክፍላቸው ሳይጎድል በአፍላ ዕድሜቸው ድልን በድል ላይ ደራርበው ይቀዳጁ የነበሩት ወታደር ማቲዎስም ዛሬ ላይ በውስጣቸው የተፈጠረባቸው ይሄው ዓይነት ስሜት ነው።

ደርግ ወድቆ ኢህአዴግ ስልጣን ቢይዝም አፍላው የወጣትነት ጉልበታቸው ባለመንጠፉ ወታደር ማቲዎስ በሠራዊቱ ውስጥ አገራቸውን በሙያቸው ከማገልገል አልተገደቡም። በእዚህ መካከል በእረፍት ጊዜያቸው ወጣ እያሉ ከጓደኞቻቸው ጋር የለመዱትን መዝናናትና መጨፈርም አልተውም።

እንዳጫወቱን በተለይ በ1990ዎቹ ዓ.ም አካባቢ አንዳንድ ትናንሽ የህመም ስሜቶች ይሰሟቸው ጀምረው ነበር። እነዚህ ስሜቶች ቀስ በቀስ ወደ የሰውነት ክብደት መቀነስና ድካም ተለውጠው የነበሩ መሆናቸውንም ያስታውሳሉ። ቀስ በቀስም ህመሙ እየፀናባቸው ድካሙ እየባሰባቸው መጣ። አልፎ አልፎም አልጋ ላይ ያውላቸው ጀመር። በእዚህ ሁኔታ ያውም እንደ ደራሽ ውሃ ድንገት አንድ ዕለት ግዳጅ በሚሰጥበት የወታደር ቤት በሆነው መከላከያ ሠራዊት ውስጥ መኖር ደግሞ አይታሰብም። እንደውም ወታደር ማቲዎስ ለእዚሁ ሰግተው ህመማቸውን ምስጢር አድርገውና ቻል አድርገው በውስጣቸው ይዘውት ነው እንጂ ውሎ ማደርም አይቻልም። እናም በእዚሁ አጋጣሚ እዛው ሠራዊቱ ውስጥ እያሉ ተመርምረው ቫይረሱ በደማቸው ውስጥ መኖሩን አወቁ።

‹‹በእርግጥ ያኔ ምንም ሥራዬን ባውቀው ውጤቱን አምኜ መቀበል አልቻልኩም ነበር›› የሚሉት ወታደር ማቲዎስ ድንጋጤው ህመሙን አባብሶባቸውና ረዘም ላለ ጊዜ ለአልጋ ቁራኛነት ተዳርገው እንደነበርም ያስታውሳሉ። በእዚሁ ምክንያትም ከሠራዊቱ በክብር ለመሰናበት በቁ። ነገር ግን ሲሰናበቱ የተሰጣቸቸው አምስት ሺህ ብር ለአንድ ሳምንትም አልበቃቻቸውም።

ቫይረሱ በደማቸው ውስጥ መኖሩን ካረጋገጡ በኋላ ለአንዴ እንኳን ወደ ሆስፒታል በመሄድ ሕክምና አላገኙም። እናም ውሎ ሲያድር አንድም ሕክምና አለማግኘታቸው፤ ሁለትም የገንዘብና ገንዘብ ሊገዛው የሚችለው የተመጣጠነና የበለፀገ ምግብ ማጣታቸው ህመማቸውን በማባባስና ሰውነታቸውን በማሰልሰል የበለጠ ገዘገዘው። ሲዲፎራቸው ወደ 21 አሽቆልቁሎ በመውረድ ለቃሬዛ እንዲበቁም አደረጋቸው።

ወታደር ማቲዎስ እንዳወጉን ታዲያ በሰው ሸክም የሄዱበት ሆስፒታል ውስጥ ያገኟት የጤና ባለሙያ የኤች አይቪ/ኤድስ የደም ምርመራ ልታደርግላቸው ፈቃደኝነታቸውን ጠየቀቻቸው። እሳቸው ግን ቫይረሱ በደማቸው ውስጥ እንዳለባቸው በለሆሳስ ነገሯትና የፀረ-ኤች አይቪ/ኤድስ ሕክምና መድኃኒት መውሰድ ጀመሩ። የቫይረሱ ሎድ ምርመራ አድርገው እንዳረጋገጡት መድኃኒቱን ሳያቋርጡ በመውሰዳቸው አሁን ላይ የሲዲፎራቸው መጠን ከ21 ወደ 900 ማደግ ችሏል። የጤንነት ሁኔታቸውም በጥሩ ሁኔታ ላይ ይገኛል። ይሄ ሊሆን የቻለው ራሳቸውን አሳምነው ኑሮና በሽታን ተቋቁመው ራሳቸውን ለማሰንበት በሚያደርጉት ጥረት እንደሆነም ምክራቸውን ይለግሳሉ።

**መልካም ንባብ!**

# ስፖርት

## ለዓለም ቻምፒዮናው ተሳትፎ ቅድመ ዝግጅት

**ብርሃን ፈይሳ**

በአትሌቲክስ ስፖርት ይህ ወቅት የቤት ውስጥ ውድድሮች ተጠናቀው የውጭ መም ውድድሮች የሚጀመሩበት ነው። ዛሬ በሁሉም አህጉራት በ12 ዙር የሚደረገው የአህጉር አቀፍ የአትሌቲክስ ውድድር በቤርሙዳ ሲከፈት፤ በቀጣዩ የፈረንጆቹ ወር አጋማሽ ደግሞ የዳይመንድ ሊግ ውድድሮች ይጀመራሉ። ከሶስት ወራት በኋላ ደግሞ በስፖርቱ ታላቅና ለአትሌቶችም የላቀ ክብር የሚያጎናጽፈው ውድድር የዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና ለ18ኛ ጊዜ ይካሄዳል። የተለመደው የውድድሩ መርሃ ግብር ከኦሊምፒክ አስቀድሞ የሚካሄድ ቢሆንም የመላው ዓለም ስጋት በነበረው የኮቪድ ስርጭት ምክንያት ከአንድ ዓመት መራዘም በኋላ ነው ለማካሄድ ቀን የተቆረጠለት።

በአሜሪካ አፈር ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ የሚካሄደው ይህ ውድድር በዓለም አትሌቲክስ ባለቤትነት ለአስር ቀናት በአጭርና ረጅም ርቀት የመም፣ በጎዳና ውድድሮች እንዲሁም በሜዳ ላይ ተግባራት አገራትን ያወዳድራል። 214 አገራት የአትሌቲክስ ብሔራዊ ቡድኖቻቸውን በሚሳተፉበት በዚህ ውድድር ላይ 49 ውድድሮች ይከናወናሉ። በስፖርቱ ከፍተኛ ደረጃ የደረሱ አትሌቶች የሚፎካከሩበትና ያሉበትን ደረጃም ለሚፈትሹበት ለዚህ ውድድር አገራት አስቀድመው ዝግጅት እንደሚያደርጉ ይታወቃል። ውድድሩ በኦሊምፒክ ማግስት፤ ከዓለም የቤት ውስጥ ቻምፒዮና መልስ የሚካሄድ መሆኑን ተከትሎ በቶኪዮና ቤልግሬድ የታዩ ድንቅና እውቅ አትሌቶች ራሳቸውን ለውድድሩ ዝግጁ ማድረጋቸውን የዓለም አትሌቲክስ በድረ ገጹ አስነብቧል።




በኦርግጥ ኢትዮጵያዊያኑን አትሌቶች ጨምሮ በርካታ የኦሊምፒክ ተሳታፊ የነበሩ አትሌቶች በወራት ልዩነት በቤት ውስጥ ቻምፒዮናው ድንቅ አቋማቸውን አሳይተዋል። በቀጣይም አብዛኛዎቹ በአህጉር አቀፉ የዙር ውድድር እንዲሁም በዳይመንድ ሊጉ ተሳታፊ እንደሚሆኑ እርግጥ ነው። ይህም የውድድር መደራረብ አትሌቶቹን ለጫና የሚያጋልጣቸው እንደሚሆን ቢገመትም፤ የዓለም ቻምፒዮናው ግን እንደቀደመ ክብሩ እንደሚካሄድ ይጠበቃል። ከጉዳት አገግመው በቻምፒዮናው ደግም ወደ ውድድር የሚመለሱትን ጨምሮ በዓመቱ አስደናቂ አቋም ላይ ያሉ አትሌቶች ክብረወሰኖችን በማሻሻልና ፈጣን ሰዓት በማስመዝገብ እንደሚያደምቁት ይጠበቃል።

ከነዚህም መካከል በቶኪዮ ኦሊምፒክ ስኬታማ የሆኑ አሜሪካዊ አትሌቶች በአዓጊው ቻምፒዮና ላይም የበላይነቱን ለመውሰድ ተዘጋጅተዋል። በአፍሪካም በአትሌቲክስ ስፖርት ታዋቂ ከሆኑት የምስራቅ አፍሪካ አገራት መካከል በውጤታማነቷ ተጠቃሽ የሆነችው ኬንያም ከምትሳተፍባቸው ርቀቶች መካከል በተወሰኑት የሚሳተፉትን አትሌቶች ማንነት አሳውቃለች። በዚህም መሰረት ረጅሙ የአትሌቲክስ ስፖርት ውድድር በሆነው ማራቶን ቡድኗ በወንዶች ጄዮፍሪ ካምዎረር፤ በሴቶች ደግሞ ሩት ቼፕጌቲች የሚመሩ ይሆናል። በርቀቱ ሰባት አትሌቶች የሚሳተፉ ሲሆን፤ አራቱ ሴቶች መሆናቸውም ታውቋል።

በስፖርቱ በተለይ በረጅም ርቀት ውድድሮች ስኬታማ የሆነችው ሌላኛዋ የምስራቅ አፍሪካ አገር ኢትዮጵያ፤ በአትሌቶቿ አማካኝነት በርካታ ክብሮችን ካስመዘገበችባቸው መድረኮች መካከል አንዱ የዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና ነው። በቅርቡ በዓለም የቤት ውስጥ ቻምፒዮና በሰበሰበቻቸው የወርቅ ሜዳሊያዎች ብዛት አንደኛ ሆና ማጠናቀቋ የሚታወስ ሲሆን፤ ይኸውም በዓለም ቻምፒዮናውም ብርቱዎቹ አትሌቶቿ እንዲጠበቁ ምክንያት ሆኗል። በመሆኑም ለውድድሩ አስቀድሞ ዝግጅት በማድረግ ወደ ኦሪገን ለመጓዝ እየተደረገ ያለው መሰናዶ ምን ይመስላል የሚለውን ጥያቄ አዲስ ዘመን ጋዜጣ ለኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን አቅርቧል።

በፌዴሬሽኑ የተሳትፎና ውድድር የስራ ሂደት መሪ አቶ አስፋው ዳኜ፤ ለቻምፒዮናው ቅድመ ዝግጅት በማድረግ ላይ እንደሚገኙ ገልጸዋል። በዚህም መሰረት በውድድሩ የሚሳተፉ አትሌቶች እየተመረጡ ሲሆን፤ ውድድሩ የራሱ የሆነ ዓለም አቀፍ የመወዳደሪያ መስፈርት (ሚኒማ) አለው። ይህንንም ተከትሎ በተቀመጠው ጊዜና መስፈርት መሰረት መሳተፍ የሚያስችላቸውን ሚኒማ የሚያሟሉ አትሌቶች በቻምፒዮናው አገራቸውን የሚወክሉ ይሆናል። የቅድመ ዝግጅት ጊዜው ከአንድ ወር እስከ አንድ ወር ከአስራ አምስት ቀን ይጠናቀቃል በሚል ይጠበቃል። አትሌቶች በቻምፒዮናው ተካፋይ ለመሆን በራሳቸው በዝግጅት ላይ የሚገኙ ሲሆን፤ በተያዘው የጊዜ ገደብ ብሔራዊ ቡድኑ ታውቆ ወደ ልምምድ የሚገባ መሆኑን የስራ ሂደት መሪው ጠቁመዋል።



# Beeksisa Gita Hojii Duwwaa

**Korporeeshiniin Misooma Paarkiwwan Industirii Oromiyaa Gita hojii duwwaa qabu irratti ulaagaalee armaan gadii guutan qacaree hojjachiisuu ni barbaada.**

| Lakk | Waamama gita hojii | Baay 'ina | Sadarkaa Gita Hojii | Mindaa | Gosa Barnootaa | Sadarka Barnootaa fi Muuxannoo hojii | Dandeettii daba-lataa | Ibsa |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | Hojii Gaggeessaa Bulchiinsa Paarkii Industirii Qonnaa Qindaa'aa | 1 | XVI | 18,152.00 | Saayinsii Bulchiinsaa, Bulchiinsa Daldalaa, Saayinsii Gabaa, Saayinsii diinagdee. Bulchiinsa Industirii fi hidhata kan qabu | Digirii 1ffaa ykn 2ffaa ykn 3ffaa Muuxannoo hojii waggaa 8/6/4 | Muuxannoo hooggansaa wag-gaa 2 ol kan qabu | Dandeetii afaan Oromoo Dubbachuu, dhagahuu, dubbisuufi barreessuu kan danda'u |

**Hubachiisa;-**

1. Beeksisi kun guyyaa maxxanfamee eegalee guyyaa hojii walitti aanan guyyaa kudhaniif Wiixataa hanga Jimaataatti sa'aa dura 02:00-6:00tti sa'aa booda 7:00 hanga 11:00tti sanbata duraa sa'aa 2:00 hanga 6:00tti galmaa'uu ni dandeessu,
2. Iyyattoonni ragaa barnootaa fi muuxannoo hojii akkasumas ragoolee barbaachisan hunda maxxansa duraa (original) fi koppii kan hin deebine fi suura tokko qabattanii dhiyaachuu qabdu,
3. Muuxannoon hojii mana mootummaa ala dhufu gibira hojii kaffaluu keessan kan ibsu ta'uu qaba.
4. Muuxannoon hojii gita hojii baheen kallaattiin ta'uu qaba,
5. lyyattoonni sadarkaa barnootaa gaafatameen ol qaban galmaa'uun dorgomuu ni danda'u.

6 Haala qacaraa:- Dhaabbiin

7 Bakka galmee:- Finfinnee, Bakkanniisaa naannoo buufata Taaksii ta'ee gamoo S.SARA TOWER darbii 5ffaa Daayirektoreetii B/Mis/Qabeenya Namaa korporeeshinichaatti dhihaattanii galmaa'uu ni dandeessu

8. Bakka hojii :-Paarkii Industirii Qonnaa Qindaa'aa Bulbulaa

9. Yeroon qormaataa beeksisa keessaa fi bilbilaan kan ibsamu ta'a

## Korporeeshinii Misooma Paarkiwwan Industirii Oromiyaa